

የኢትዮጵያ የፍትህ ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን

(መሠረታዊ ለዉጥ) መነሻ ጽሁፍ

ግንቦት 2015

አዲስ አበባ

ማዉጫ

ማውጫ

ምዕራፍ አንድ 4

የኢትዮጵያ የፍትህ ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን (መሠረታዊ ለዉጥ)፡ መነሻ ጽሁፍ 4

መግቢያ 4

1.1 አስፈላጊነት 5

1.2 ዓላማ 7

1.2.1 ዋና ዓላማ 7

1.2.2 ዝርዝር ዓላማዎች፡- 7

1.3 መርሆዎች 7

1.4 እሴቶች፡- 9

1.5 የሚጠበቅ ዉጤት 10

1.6 የሪፎርም ሥራዉ ወሰን 10

ምዕራፍ ሁለት 11

የፍትህ ዘርፍ ማሻሻያ ስራዎች ዳሰሳ 11

2.1 በ1950ዎቹ የተደረጉ የፍትህ ዘርፉ ማሻሻያዎች፡ ዘመናዊነትን ፍለጋ 11

2. የ1966 አብዮት እና የህብረተሰብዓዊነት ምዕራፍ 13

3. ድህረ 1983፡ የሕግ ስርዓቱን ፌዴራላዊ የማድረግ ሂደት 14

4. የሁሉ-አቀፍ የፍትህ ዘርፍ ማሻሻያ ፕሮግራም 15

5. ድህረ-2010 የሕግ እና ፍትህ ማሻሻያ 17

6. ሊወሰዱ የሚገባቸው ትምህርቶች 21

7. ለትራንስፎርሜሽን የፍትህ ዘርፉ የጋራ ፍኖተ ካርታ አስፈላጊነት 25

8. ያለንበት ነባራዊ ሁኔታ፡ ተግዳሮቶች እና መልካም አጋጣሚዎች 26

ምዕራፍ ሶስት 28

በፍትህ ዘርፍ ተቋማት ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶች አጭር ዳሰሳ 28

1. የጥናቶቹ ዋና ዋና ግኝቶች 30

1.1. በአውንታዊ የተጠቀሱ ዋና ዋና ግኝቶች 30

1.2. በአሉታዊ የተጠቀሱ ዋና ዋና ግኝቶች 31

2. የመፍትሄ ሀሳቦች 40

ምዕራፍ አራት 44

የፍትህ ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን፤ ለፍትህ ዘርፍ ማሻሻያ አዲስ አቅጣጫ 44
1. ትንስፎርሜሽን ወይስ ማሻሻያ፤ ከቃላት ጨዋታ በላይ 44
2. የተለዩ ማሻሻያ እርምጃዎች እና የትራንስፎርሜሽን አምዶች 45
2.1. የመሰረተ-ማህበረሰብ የፍትህ አገልግሎት 45
2.2. የፍትህ ዘርፍ አመራሮችና ባለሙያዎችን ማጥራት 46
2.3. ያደገ እና ውጤታማ የኢንፎርሜሽን ኮሚውኒኬሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም 48
2.4. የወንጀል፣ የአስተዳደርና ፍትሐብሔር ፍትህ ስርዓት ፕሮግራም፡ በአዲስ አስተሳሰብ 49
2.5. የተጠናከረ ንቃተ-ሕግ እና የሕግ ድጋፍ 51
2.6. ዘመናዊ አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓቶችን ማስፋፋት 52
2.7. የተሻለ የተዋረድ እና የጎንዮሽ ቅንጅት፣ መማማርና የጋራ ፍኖተ ካርታ 53
2.8. የፌዴራል የፍትህ አካላት ተቋማት በክልሎች ያላቸው ተደራሽነትን ማሳደግ 54
2.9. ተገቢና ዉጤታማ የኅብረተሰብ ተሳትፎ 54
2.10. የፍትህ ዘርፍ ተቋማት አደረጃጀትን ማስተካከልና ዘርፉን ሳቢና ታማኝነት የተቸረዉ ማድረግ 54
3. የአፈጻጸም አቅጣጫዎች 55

ምዕራፍ አንድ

የኢትዮጵያ የፍትህ ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን (መሠረታዊ ለዉጥ)፡ መነሻ ጽሁፍ

መግቢያ

ባለፉት ጊዜያት የኢትዮጵያን የፍትህ ዘርፍ[1] ለማሻሻል የተለያዩ የማሻሻያ ስራዎች የተሰሩ ቢሆንም ዜጎች ከፍትህ ዘርፉ የሚጠብቋቸውን መልካም ውጤቶች በበቂ ሁኔታ ማምጣት አልተቻለም። አሁንም የፍትህ ዘርፉ ፍትህን በሚያሰፍንበት ሂደት እና በውጤቱ ላይ ከህብረተሰቡ የሚሰሙ እሮሮዎች በፍትህ ዘርፉ ላይ ያለውን የአመኔታ እና የእርካታ እጦት የሚያመላክቱ ናቸው። ይህ ዘርፍ ከህብረተሰቡ የሚጠበቅበትን ውጤት ለማምጣት በሚያስችለው ልክ የማደስ ስራ እጅግ አድካሚ እና ፈታኝ ተልዕኮ ነው።

ይህንን ፈታኝ የሆነ ተልዕኮ ከዳር ለማድረስና አጠቃላይ የፍትህ ስርዓቱ በተለይም ደግሞ የፍትህ ዘርፍ ተቋማት ጋር ተያይዞ ያሉትን ሁኔታዎች እና በሚፈለገው መልኩ ለውጥ ለማምጣት ማነቆ የሆኑ ችግሮችን መለየትና ተገቢ የሆነ መፍትሄ በማስቀመጥ ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊነቱ አያጠያይቅም። በፍትህ ዘርፍ ተቋማት ላይ ያሉትን ሁኔታዎች ለመረዳት፣ ችግሮቹን ለማወቅ እና የመፍትሄ አቅጣጫሞችን ለማስቀመጥ ይረዳ ዘንድ የተለያዩ ጥናቶች በተለይም በፍትህ አገልግሎት፣ የፍትህ ፍላጎት፣ መልካም አስተዳደር፣ የወንጀል ጉዳዩች መጓተት መንስኤዎች እና የፍትህ ስርዓት ማሻሻያ ፕሮግራሞች ላይ የተደረጉ ጥናቶችን በዚህ ሰነድ እንደመነሻ ተወስደዋል።

ይህ መነሻ ጽሁፍም የፖሊሲ አመንጪዎች እና የፍትህ ዘርፉ ተዋንያን በዘርፉ ሊመጡ ስለሚገባቸው የማሻሻያ ስራዎች መዋቅራዊ አቅጣጫን ለማመላከት ታስቦ የተዘጋጀ ነው። መነሻ ጽሁፍ በአምስት ዋና ዋና ክፍሎች የተዋቀረ ሲሆን በመጀመሪያው ክፍል ላይ ባለፉት አስርት አመታት በፍትህ ዘርፉ ላይ የተደረጉ ዋና ዋና የማሻሻያ ስራዎች በአጭሩ የሚዳሰሱበት ይሆናል። በሁለተኛው ክፍል የፍትህ ዘርፍ ተቋማት ያሉበትን አሁናዊ ሁኔታ፣ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው የተለያዩ ጥናቶችን መሰረት በማድረግ የሚዳሰስበት ነው። ሶስተኛው ክፍል ደግሞ ከእነኚህ የማሻሻያ ስራዎች ሊወሰዱ የሚገባቸው ትምህርቶች የሚዳሰሱ ሲሆን በአራተኛው ክፍል ደግሞ አጠቃላይ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ነባራዊ ከባቢ ዳሰሳ የሚቃኝበት ሲሆን ከእነኚህ አመላካቾች አንጻር በፍትህ ዘርፉ ሊደረግ የሚገባው የለውጥ እና ማሻሻያ ስራ በአዎንታዊ እና አሉታዊ ተጽዕኖዎቹ የሚመዘን ይሆናል። በመጨረሻም አምስተኛው ክፍል ላይ የፍትህ ዘርፉን በተመለከተ ሊወሰዱ የሚገባቸው የለውጥ እና የማሻሻያ እርምጃዎች አላማ፣ አካሄድ እና አግባብ የሚተነተኑበት ይሆናል።

[1] ለዚህ ሰነድ ዓላማ የፍትህ ዘርፍ የሚለዉ ፍርድ ቤቶችን፣ ፍትህ ሚኒስቴር፣ ፖሊስ ኮሚሽን፣ ማረሚያ ቤት ኮሚሽን እና የህግ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን የሚያካትት ሲሆን የዘርፉ ተቋማትም በፌዴራልና በክልል ደረጃ የሚገኙ እነዚህን ተቋማት ማለት ነዉ።

1.1 አስፈላጊነት

የፍትህ ዘርፍ ተቋማት ለኅብረተሰቡ የሚሰጧቸዉ የተለያዩ አገልግሎቶች በተፈጥሮአዊ ባህሪያቸዉ ከባድና የተወሳሰቡ ሆነዉ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጣቸው ሚገቡ ናቸው፡፡ አገልግሎቶቹ ከግለሰቦች ጀምሮ ንግድ ድርጅቶችና ማህበራት እንዲሁም መንግሥትን ጭምር የሚመለከቱ ሲሆን በተለይም ከህብረተሰቡ አንጻር ሲወሰድ ከአነስተኛ የንብረት መብት ጀምሮ እስከ ከፍተኛና ግዙፍ ሀብቶች እንዲሁም ከዜጎች የመንቀሳቀስ መብትና ሕይወት ድረስ የሚመለከቱ ናቸው፡፡ በዘርፉ ተቋማት አገልግሎት የዜጎች በህይወት የመኖር፣ የመንቀሳቀስ፣ የንብረት እና ሌሎችም መብቶች በሕግ አግባብ የሚገደብበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የዘርፉ ተቋማት የሚያስተናግዷቸው ተገልጋዮች በአብዛኛው በተለያዩ መንገዶች ጥረት ተደርጎ ለመግባባት ያልቻሉ ሰዎች ሲሆኑ የባላንጣነት ወይም የጠላትነት መንፈስን ያዳበሩ ናቸው፡፡ ከዚህም የተነሳ በመካከላቸው ያለውን ያለመግባባት በሕግና በፍርድ አደባባይ ለመዳኘት በመፈለግ በጣም በርካታ ተገልጋይ የሚመጣባቸው ተቋማት ናቸው፡፡

የዘርፉ ተቋማት ተገልጋዮች ለአገልግሎት በሚመጡባቸው የፍትህ ዘርፍ ተቋም ውስጥ በመካከላቸው የተፈጠረው ያለመግባባት በሕግ በተቀመጠው ሥርዓት ጊዜንና ጉልበትን በቆጠበ መንገድ በአነስተኛ ወጪ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲፈታ ይፈልጋሉ፡፡ በተጨማሪም ተገልጋዮች በዘርፉ ተቋማት የሚሰጠው አገልግሎት ከአድልኦ፣ ከጉቦና ሙስና እንዲሁም ሌሎች የሥነ-ምግባር ጉድለቶች በጸዳ በቅንነት ፍትህ የሚሰፍንበትን ሁኔታ ይፈልጋሉ፡፡ ከዚህ አንጻር በሀገራችን የፍትህ ዘርፍ ተቋማት ተገልጋዮችን የአገልግሎት እርካታን በተመለከተ በተለያዩ ጊዜያት የተደረጉ ጥናቶች እንዲሁም በተለያዩ አጋጣሚዎች በሚፈጠሩ የህዝብ መድረኮች የሚሰነዘሩ አስተያየቶች የሚያሳዩት በዘርፉ የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት፣ የአገልግሎት ጥራት፣ ሥነ-ምግባር፣ … ወዘተ ከፍተኛ የሆነ የሕብረተሰቡ ሮሮና ስሞታ መኖሩን ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ በዘርፉ ተቋማት ላይ ያለው የህብረተሰቡ አመኔታ የተሸረሸረ መሆኑን መገንዘብ አዳጋች አይሆንም፡፡ በመሆኑም የፍትህ ዘርፍ ተቋማት ውስጥ የሚታዩ ችግሮችን በመቅረፍ የኅብረተሰቡን ፍላጎት ለማርካት ጠንካራና የማያዳግም መሠረታዊ የሆነ የለውጥ ሥራ ማካሄድን አስፈላጊ ያደርጋል፡፡

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በሀገራችን በተለያዩ አካባቢዎች በሚነሱ ግጭቶችና የፀጥታ መደፍረስ ምክንያት ያለመረጋጋቶች ሲከሰቱ እነዚህ ሁኔታዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሁኔታ የፍትህ ዘርፍ ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥና ውጤታማነት ላይ ቀጥተኛም ሆነ ቀጥተኛ ያልሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድረዋል፡፡ በአንድ ሀገር የፀጥታ መደፍረስ እንዳይከሰትም ሆነ ሲከሰት ለመቆጣጠር ጠንካራ የሆነ ተቋም ሊኖር ይገባል፡፡ ከግጭትና የጸጥታ መደፍረስ ጋር ተያይዞ የሚመጡ የተለያዩ ሁኔታዎች ጠንካራና ውጤታማ የሆኑ የፍትህ ዘርፍ ተቋማት ባሉበት ሀገር እጅግ የከፋ ጉዳትና መመሳቀል ሳይፈጠር መቆጣጣር የሚቻልበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ በሌላ ጎኑ ተቋማቱ ጥንካሬያቸዉ የላላ በሆነበት ሀገር ከፍተኛ ጉዳትና መመሰቃቀል ከማስከተሉም በላይ ሀገርን የማፍረስ ዉጤት ሊያስከትል ይችላል፡፡ በሀገራችን አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ የፍትህ ዘርፍ ተቋማት ግጭቶችንና የጸጥታ መደፍረስ ሁኔታን ቀድሞ ከመቆጣጠርም ሆነ በሚከሰትበት ጊዜ ፈጥኖ ከማክሰም አኳያ ሲታይ እስካሁን

የተሰሩትና የተገኙት ዉጤቶች እንደተጠበቁ ሆነው ገና የሚቀራቸው በመሆኑ ይህንን ነባራዊ ሁኔታ በመቀየር ተቋማቱ በሚጠበቀው ደረጃ ሆነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉ እንዲሆኑ በዘርፉ የትራንስፎርሜሽን ሥራ አስፈላጊ ይሆናል።

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረዉ የፍትህ ዘርፍ ተቋማት አገልግሎት በባህሪው ለየት ያለና ገለልተኝነትን፣ ፍትሀዊነትን፣ ብቃትን፣ ሥነ-ምግባርን፣ ...ወዘተ የሚጠይቅ ሲሆን ሕብረተሰቡ ተቋማቱ በየጊዜዉ ችግሮቻቸውን በመቅረፍ የተሻሻለና የተለወጠ አገልግሎት ሲጠብቅ ለውጥ የማይታይበት ሲሆን ተስፋ መቁረጥ እና ይህን ተከትሎ የቅሬታዎች መስፋፋት ያስከትላል። አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ በየቦታው ከሚከሰተው ግጭትና የሠላም መደፍረስ እንዲሁም ሌሎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጫናዎች በተጨማሪ የፍትህ ዘርፍ ተቋማት አገልግሎት የቅሬታና የምሬት ምንጭ ሆኖ ሲቀጥል በኅብረተሰቡ ውስጥ ተጨማሪ የቀውስ ማቀጣጠያ መሆኑ አይቀርም። ይህ በሚሆንበት ጊዜ የዘርፉ ተቋማት አገልግሎት ጥራትም ሆነ ተደራሽነት ለቀውስ ማቀጣጠያና መነሻ በመሆን በሀገሪቱ የፖለቲካ ያለመረጋጋትን ሊያስከትል ይችላል። ይህንን አስቀድሞ ለመከላከል በፍትህ ዘርፍ ተቋማት ውስጥ የትራንስፎርሜሽን ሥራን ከወዲሁ መሥራት የግድ ይላል።

1.2ዓላማ

1.2.1 ዋና ዓላማ

በፍትህ ዘርፍ ተቋማት የሚካሄድ ማሻሻያ/ሪፎርም ዋና ዓላማ በተቋማቱ እስካሁን የተሠሩ ጠንካራ ጎኖችን የበለጠ በማጠናከር በድክመቶች ላይ ተገቢውን እርምጃ በመውሰድና በማረም በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነትና ተአማኒነት ያለው ጠንካራ ተቋም በመፍጠር የተገልጋዩን እርካታ ማሳደግ ነዉ።

1.2.2 ዝርዝር ዓላማዎች፡-

የሪፎርም ሥራው ዝርዝር ዓላማዎች፡-

- በዘርፉ ተቋማት የእስካሁን ማሻሻያ ሥራዎች ጥንካሬዎችና ድክመቶችን በአግባቡ መለየት፣
- ጥንካሬዎችን ለበለጠ ትምህርት በመጠቀም በድክመቶች ላይ ጠንካራና መራራ ትግል በማድረግ ማረም፣
- የዘርፉን ተቋማት የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ማሳደግና አገልግሎቶችን ማሳለጥ፣
- በዘርፉ ተቋማት ጠንካራና ቁርጠኛ የሆነ አመራርና የአመራር ሥርዓት መፍጠር፣
- የዘርፉ ተቋማት ሠራተኞችና ባለሙያዎች በሙያ ብቃታቸዉና በሥነ-ምግባራቸው ምሉዕ ሆነው ተገልጋዩን

የሚያረኩ ማድረግ፣

- የዘርፉን ተቋማት አደረጃጀትና አሠራር እንዲሁም የሰዉ ኃይልና የሀብት ፍላጎት በማሻሻል የተጣለባቸዉን ተልዕኮ በአግባቡ የሚወጡ ጠንካራ ተቋማት ማድረግ፣
- በዘርፉ ተቋማት መካከል ቅንጅታዊ አሠራርን በማጠናከር ዘርፉን ዉጤታማ ማድረግ፣

1.3 መርሆዎች

- **ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌዎችንና ሥርዓቶችን ማክበር፡-** የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ-መንግሥት የፍትህ ዘርፍ ተቋማትንም ሆነ ሌሎች ተቋማትን የሚመለከቱ በርካታ መሠረታዊ መርሆዎችንና ድንጋጌዎች የያዘ ነዉ። የሕግ የበላይነት፣ የዳኝነት ነጻነትና ገለልተኝነት፣ የሥልጣን ተዋረድና ክፍፍል ከነዚህ መካከል የሚጠቀሱ ናቸዉ። በመሆኑም የፍትህ ዘርፉ ተቋማት ሪፎርም ከሚመራባቸዉ መርሆዎች አንዱ የሕገ-መንግሥቱን ድንጋጌዎችና መርሆዎችን ባከበረ መልኩ መተግበር ሲሆን ይህም ማለት በሕገ-መንግስቱ የተደነገገውን የዳኝነት ነጻነትና ገለልተኝነት፣ የተቋማት ነጻነት፣ የሥልጣን ተዋረድና ክፍፍል ባከበረ መልኩ ይፈጸማል ማለት ነዉ።

- **ከአጠቃላይ የሀገረ-መንግሥት ግንባታ አቅጣጫዎችና ማዕቀፎች አንጻር የተቃኘ፡-** በኢትዮጵያ የሀገረ-መንግስት ግንባታ የተለያዩ ሥራዎችን የሚጠይቅ ሲሆን እስካሁንም የተሠሩትን ያጠቃልላል። በፍትህ ዘርፍ ተቋማት የሚከናወኑ የሪፎርም ሥራዎች ኢትዮጵያዊያን ሕግ አክባሪ፣ ለፍትህ ቀናዕ እና ለዜጎች ያላግባብ መበደል የሚቆረቆሩ ዜጎች ሆነዉ እንዲቀረጹ ለሚደረገዉ ጥረት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ። ዜጎች በሕጋዊነት እና ፍትሐዊነት ተኮትኩተዉ በሚያድጉበት ጊዜ ሐገሪቱ ከሥርዓተ-አልበኞች የተጠበቀችና ሁሉም ዜጋ በአንድነትና በጋራ ለሕግ መከበር እንዲሁም ለተገቢዉ ፍትህ መስፈን ይቆማል። ስለሆነም የፍትህ ዘርፍ ተቋማት የሪፎርም ሥራ ከአጠቃላይ የሀገረ-መንግሥት ግንባታ አቅታጫዎችና ማዕቀፍ ጋር የተሰናሰለ ሆኖ በዚያዉ አንጻር የተቃኘ መርህን የተከተለ ይሆናል።

- **የኅብረተሰቡን ጥያቄዎችና ፍላጎቶች ያማከልና አመኔታን መፍጠር፡-** የፍትህ ዘርፍ ተቋማት አገልግሎት ዋነኛ ግብ የተገልጋዩን ኅብረተሰብ የፍትህ ፍላጎት ማርካት ነዉ። የዘርፉ ተቋማት ሪፎርም ሲታሰብ በዋናነት የተገልጋይ ህብረተሰቡን ጥያቄዎችና ፍላጎቶች ማዕከል ያደረገ መፍትሔ ሰጪ የሪፎርም ሥራ ሊሆን ይገባል። የፍትህ ዘርፉ ተቋማት አገልግሎት ከተገልጋዩ ኅበረተሰብ ፍላጎትና

ጥያቄ ጋር የማይጣጣም በሚሆንበት ጊዜ ተቋማቱ ከኅብረተሰቡ የሚነጠሉበት ሁኔታ ከመፈጠሩም በላይ የተቋማቱ መኖር ትርጉም-አልባ የሚሆንበት ሁኔታ ይፈጠራል። በሌላ ጎኑ ተቋማቱ የኅብረተሰቡን ጥያቄዎችና ፍላጎቶች በማዳመጥ ፈጣን ምላሽ በሚሰጡበት ጊዜ ከጊዜ ወደ ጊዜ ኅብረተሰቡ በተቋማቱ ላይ የሚኖረዉ መተማመንና አመኔታ እየጨመረና እየጎለበተ ከመሄዱም በላይ ተቋማቱ ከፍተኛ የሆነ የኅብረተሰብ ድጋፍ የማግኘት ዕድላቸዉ ይሰፋል። በመሆኑም አንዱ የሪፎርም ስራዉ የሚመራበት መርህ የኅብረተሰቡን ጥያቄዎችና ፍላጎቶች ያማከለና አመኔታን መፍጠርን ነዉ።

- **ሁሉን አቀፍ የሆነ ሪፎርም፦** አሁን ባለዉ የሐገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የፍትህ ዘርፍ አገልግሎት በፌዴራል ደረጃ በዋናነት በአራት ተቋማት እንዲሁም በተመሳሳይ በክልሎችም እንደዚሁ በአራት ተቋማት የተከፋፈለ ነዉ። እነዚህ ተቋማት የየራሳቸዉ አደረጃጀት፣ ነጻነትና ገለልተኝነት እንደተጠበቀ ሆኖ አንዱ ተቋም ከሌላዉ ጋር የተሰናሰለ ሲሆን የአንዱ ተቋም የሥራ ውጤት ለሌላዉ ተቋም ስራ ግብአት በመሆን የሚያገለግል ነዉ። ከዚህም በተጨማሪ ተቋማቱ በበህሪያቸዉ የሚቀራረቡ እንደመሆናቸው መጠን የጋራ የሆኑ ችግሮች ያሏቸዉ ናቸው። በመሆኑም የዘርፉ የሪፎርም ሥራ ውጤታማ ሊሆን የሚችለዉ በተናጠል በመሥራት ሳይሆን ሁሉን አቀፍ በሆነ መንገድ ማለትም በፌደራልም ሆነ በክልል ባሉ የዘርፉ ተቋማት እንዲሁም በሁለቱም የአስተዳደር እርከኖች የሚገኙ ተቋማት በጋራ ባቀፈ መንገድ ሲሠራ ነዉ። ስለሆነም አንዱ መከተል የሚገባዉ መርህ ሁሉ-አቀፍ የሆነ የሪፎርም ሥራ ነዉ።

- **ያሉ መልካም ጎኖችን በማጠናከር በችግሮች ላይ አትኩሮ መሥራት፦** የፍትህ ዘርፍ ተቋማት ከዚህ በታች እንደተቀመጠው በተለያዩ ጊዜያት የተደረጉ የተለያዩ የማሻሻያ ሥራዎች የነበሩ ሲሆን በነዚያ የተመዘገቡ መልካም ውጤቶችም እንዲሁም በሂደቱ የታዩ ክፍተቶችም አሉ። ቀጣይ የሚታሰበው የሪፎርም ሥራ ካለፉ በጎ ሥራዎች ልምድ ከመውሰድም በላይ እነዚያን በማጠናከር በችግር በተለዩት ላይ በመረባረብ ማስተካከል ላይ ያተኮረ ሊሆን ይገባል። የነበረውን ሁሉን በመናድ ከአዲስ ለመጀመር ጥረት ማድረግ ለበርካታ ኪሳራ ከመዳረጉም በላይ ከንቱ ልፋት ይሆናል። በመሆኑም በሪፎርም ሥራው መከተል ከሚገቡ መርሆዎች አንዱ ያሉ መልካም ጎኖችን ማጠናከርና ማጎልበት፤ ችግሮችን በቁርጠኝነት በመታገል ማስተካከልና ማረም ይሆናል።

1.4እሴቶች፡-

- ግልጽነት
- ታማኝነት
- ተደራሽነት
- እኩልነት
- ነፃነት እና ተጠያቂነት
- ውጤታማነት
- ታማኝነት
- እውቀት እና ውጤታማነት
- በህዝቦች የበላይነት እና በህግ የበላይነት ላይ ጠንካራ እምነት
- አሳታፊ የስራ ዘዴ
- የቡድን መንፈስ ባህል
- የመንግስት ሀብቶችን እና ንብረቶችን በአግባቡ መጠቀም
- ለለውጥ ቁርጠኝነት

1.5 የሚጠበቅ ውጤት

በሪፎርም ሥራዉ የሚጠበቅ ዉጤት በፍትህ ዘርፉ ተቋማት ዉስጥ የሚታዩ የአደረጃጀት፣ የአሠራር እንዲሁም የሰው ኃይልና ሀብት ችግሮችን በመቅረፍ በጎብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነትና ተአማኒነት ያለው ጠንካራ ተቋም በመፍጠር የተገልጋዮችን እርካታ ማሳደግ ነዉ።

1.6 የሪፎርም ሥራዉ ወሰን

ይህ የሪፎርም ሥራ በፍትህ ዘርፉ ከረጅም ጊዜያት ጀምሮ ሲካሄዱ በነበሩ የማሻሻያ ሥራዎች የተገኙ ውጤቶችንና ስኬቶችን እንደመነሻ በመውሰድ ጠንካራ ጎኖችን የበለጠ በማጠንከር የሚቀጥል ይሆናል። በዘርፉ የሚታዩ ክፍተቶች ላይ ጠንካራና የማያዳግም ትግል በማድረግ ለመለወጥና የህበረተሰቡን የፍትህ ፍላጎት የማርካት ሥራ ላይ ያተኩራል። በመሆኑም ይህ ሪፎርም ቀድሞ የነበረዉን በመናድ ሁሉንም ነገር ከአዲስ የሚጀምር ሳይሆን

በዘርፉ ያለዉን ወረት እንደ ስንቅ በመያዝ ክፍተቶችን በማሻሻል ላይ የተወሰነ ይሆናል።

ምዕራፍ ሁለት

የፍትህ ዘርፍ ማሻሻያ ስራዎች ዳሰሳ

ባለፉት አስርት አመታት የኢትዮጵያን የፍትህ ዘርፍ ለማሻሻል በርካታ ሙከራዎች ተደርገዋል። እነኚህን የማሻሻያ ሙከራዎች የተለሙት እና በባለቤትነት እውን ያደረጉት አካላት መነሻ የሆኗቸው አላማዎች በወቅቱ ገዢ የነበሩ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እሳቤዎች ነበሩ። በዚህም ሳቢያ እነኚህ የማሻሻያ ሙከራዎች የራሳቸው የሆነ ስኬት እና ድክመት የነበራቸው ናቸው። ከእነኚህ ስኬቶች እና ድክመቶች በቀጣይ ለሚደረጉ የማሻሻያ ትልሞች እና ስራዎች በርካታ ትምህርት መውሰድ እንደሚቻል በማመን በዚህ የጽሁፉ ክፍል ያለፉ የማሻሻያ ሙከራዎችን በአጭሩ ለመዳሰስ ይሞከራል።

2.1 በ1950ዎቹ የተደረጉ የፍትህ ዘርፉ ማሻሻያዎች፡ ዘመናዊነትን ፍለጋ

በ20ኛው ክፍለዘመን አጋማሽ በወቅቱ የነበረው ዘውዳዊ ስርዓት ኢትዮጵያን የማዘመን ተልዕኮውን አጠናክሮ የቀጠለበት ወቅት ነበር። ይህን የማዘመን ተልዕኮ ለማሳካት ይቻል ዘንድ ከተወሰዱ የዘመናዊነት እርምጃዎች መካከል አንዱ መጠነ ሰፊ የሆነ የሕግ ስርዓት ማሻሻያ ስራ ይገኝበታል። በዚህ የማሻሻያ ሂደት ተጠቃሽ እና ዋነኛ መገለጫ የሆነው እንደ የፍትሐብሔር ሕግ መድብል፣ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መድብል፣ የንግድ ሕግ መድብል፣ የፍትሐብሔር ሕግ ስነስርዓት መድብል፣ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነስርዓት መድብል እና የባህር ሕግ መድብል መጽደቃቸው እና ስራ ላይ እንዲውሉ መደረጉ ይገኝበታል። ከዚህ ጋር በተያያዘ በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የሆነው የሕግ ትምህርት ቤት በወቅቱ በነበረው የቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዩንቨርሲቲ የተከፈተውም በዚሁ ተመሳሳይ የሕግ ስርዓት ማሻሻያ አውድ እና ወቅት ነበር። የሕግ መድብሎቹ መጽደቅ እና በስራ ላይ መዋል የሀገሪቱን የሕግ ስርዓት በወቅቱ ከነበረው በሀገር በቀል ልማዳዊ ሕጎች እና ሀይማኖታዊና ዓለማዊ ቅልቅል ባህርይ በነበረው የፍትሐ ነገስት ሕግ በማውጣት በአብዛኛዉ በአውሮፓ አህጉራዊ የሕግ ስርዓት ቅኝት በተዘጋጁ ሕጎች ወደ መተዳደር ያሸጋገረ ነበር። እነኚህ የሕግ መድብሎች በወቅቱ በሙያቸው አለም አቀፍ እውቅና በነበራቸው እንደ ፈረንሳዊው

የንጽጽር ሕግ ምሁር ሬኔ ዳቪድ ባሉ ባለሙያዎች የተዘጋጁ ሲሆን የእነኚህ መድብሎች መዘጋጀት፣ መጽደቅ እና ወደስራ መግባት ዘመናዊ የሕግ ስርዓትን ወደ ኢትዮጵያ በማስገባት እና ሀልዮታዊ ቢሆንም በመላው ሀገሪቱ ዘመናዊ የሕግ ስርዓትን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ጉልህ ጅማሮን የሚያሳይ ነው።

በወቅቱ የነበረው ዘውዳዊ ስርዓት እነኚህን ዘመናዊ የሕግ መድብሎች ያስተዋወቀው እና የመጀመሪያውን የሕግ ትምህርት ቤት ለመመስረት ዋነኛ ምክንያት የሆነው የሕግ ስርዓቱን ለማዘመን በሚል ሳይሆን ይህንን የሕግ ስርዓት በመጠቀም መላውን ማህበረሰብ ለማዘመን በሚል ነው። እነኚህ ሕጎች በንግድ ስርዓቱ፣ በሕግ ማስከበሩ፣ በግል እና በቤተሰብ ጉዳዮች ሁሉን አቀፍ የሆነ ዘመናዊነት እንዲያመጡ በሚል መነሻ ተቀባይነት ያገኙ ነበሩ። እነኚህ ሕጎች ኢትዮጵያ ወደ “ሰለጠኑ ሀገራት” ማህበር ለመቀላቀል ያላትን ቁርጠኝነት ለማሳየት የታለሙ ነበሩ። በተያያዘም እነኚህን ሕጎች በማርቀቅ ሂደት የተሳተፉ የወቅቱ እውቅ አውሮፓዊ የንጽጽር ሕግ ምሁራን የተመረጡት የሚወጡት ሕጎች በወቅቱ አለም የደረሰበትን የህግ ሳይንስ እሳቤ እና እድገት ያማከሉ የላቀ ደረጃ ያላቸው መድብሎች ለማዘጋጀት በማሰብ ነው። በአብዛኛው በውጭ ሀገር ምሁራን የተዋቀረው የወቅቱ የሕግ ትምህርት ቤት መክፈት ያስፈለገበት ምክንያትም በወቅቱ ለኢትዮጵያ የሕግ ስርዓት የተዋወቁትን ዘመናዊ ሕጎችን እና የሕግ ስርዓትን በአግባቡ ለመዘወር የሚችሉ የሕግ ባለሙያዎችን ለማፍራት እና በእውቀት ለማብቃት ነበር።

ይህ የኢትዮጵያን የሕግ ስርዓት የማዘመን ሙከራ የራሱ የሆኑ ተጠቃሽ አዎንታዊ ስኬቶች የነበሩት ሲሆን ከእነኚህ መካከልም እጅግ ዋነኛ ተብሎ የሚጠቀሰው ለዘመናዊ የሕግ ስርዓት እድገት መሰረት የጣለ መሆኑ ነው። በዚያ ወቅት የጸደቁ አብዛኞቹ ሕጎች አሁንም ድረስ በስራ ላይ የሚገኙ ሲሆን የተሻሻሉትም ቢሆኑ እነኚህን መድብሎች እንደ ትልቅ መነሻ ወስደዋል። በዚያ ወቅት የተመሰረተው የሕግ ትምህርት ቤት ለሶስት አስርት አመታት ያክል ብቸኛ የሕግ ትምህርት ተቋም ሆኖ ያገለገለ ሲሆን ከዚያ በኋላም በሀገሪቱ ለተቋቋሙ የሕግ ትምህርት ቤቶች እንደ እርሾ በመሆን አገልግሏል። በአጠቃላይ በ1950ዎቹ የተከናወኑት የኢትዮጵያን የሕግ ስርዓት የማዘመን ተግባራት በአሁን ወቅት ያለውን የሕግ ስርዓት ቅርጽ በማስያዝ የፈጠሩትን ተጽዕኖ በመመልከት ዘመን አይሽሬ ውጤት ነበራቸው ቢባል ከማጋነን አይቆጠርም።

ምንም እንኳን ከላይ በተገለጸው አግባብ አዎንታዊ ውጤቶችን ያመጣ የሕግ ማሻሻያ በ1950ዎቹ የተደረገ ቢሆንም የራሱ የሆነ ደካማ ጎኖችም ነበሩት። በዚህ ረገድ በቅድሚያ የሚነሳው ጉድለት የሕግ ስርዓት ማሻሻያ ጥረቶች መነሻ ባደረጉት እሳቤ ምክንያት በወቅቱ በሰፊው ተግባራዊ ይደረጉ ለነበሩ ልማዳዊ ህጎች ምንም ቦታ ያልሰጠ መሆኑ ነው። የውጭ ሀገር የሕግ ስርዓትን በጅምላ በመቀበል የተዘጋጁት የሕግ መድቦሎች ለአብዛኛው ኢትዮጵያዊ በቀላሉ የሚረዳቸው ሆነው ባለመገኘታቸው ምክንያት በማህበረሰቡ ውስጥ ሰርጸው ለመግባት እና ቅቡልነትን ለማግኘት ሳይችሉ ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ ባዕድ ሆነው እንዲቆዩ ምክንያት ሆኗል። ምንም እንኳን እነኚህ የሕግ መድብሎች ማህበረሰቡን ለማሻገር እና ለማዘመን ታስበው የተዘጋጁ ቢሆንም በአብዛኛው የሀገሪቱ

ክፍል በተለይ ደግሞ በገጠሩ አካባቢ እነኚህ መድብሎች እና ዘመናዊ ተቋማት እጅግ አነስተኛ ተደራሽነት እና ተጽዕኖ እንዲኖራቸው ምክንያት ሆኗል። ይህም ሁኔታ የአንድ ማህበረሰብ ሕግን ወደሌላ ፍጹም የተለየ ማህበረሰብ በቀጥታ ገልብጦ መውሰድ እና ተግባራዊ ለማድረግ መሞከር የውድቀት ሁሉ መጀመሪያ ስለመሆኑ በዘርፉ በተጻፉ ጽሁፎች እና በሚደረጉ ክርክሮች ለሚነሳው ሀሳብ ተጨባጭ ምሳሌ ያደርገዋል።

2.2 የ1966 አብዮት እና የህብረተሰብዓዊነት ምዕራፍ

ዘመናዊ የሕግ መድብሎች ለሀገሪቱ ከተዋወቁ 15 ከሚጠጉ አመታት በኋላ በኢትዮጵያ አብዮታዊ አመጾች ተቀሰቀሱ። በዚህም ምክንያት የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ በኋላም የኢትዮጵያ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሆነው ስልጣን ከዘውዳዊ ስርዓቱ በመንጠቅ በማርክሲስታዊ ርዕዮተ አለም የተቃኙ የግል ንብረት፣ የንግድ ስራን እና የመሬት ይዞታ አስተዳደርን የሚመለከቱ ስር ነቀል የሆኑ ተከታታይ ሕጎችን በማውጣት የሀገሪቱን የጉዞ አቅጣጫ ለወጠ። በዚህም በእነኚህ የሕግ መድብሎች የግል ንብረትን፣ የንግድ ስራን እና የመሬት ስሪትን በሚመለከት ተካተው የነበሩ የሕግ ድንጋጌዎች ዋጋ እንዳይኖራቸው አድርጓል። ከዚህ በተጨማሪ በአብዮቱ የተፈጠረው ግለት እና እርሱን ተከትሎ የተንሰራፋው መንግስታዊ የሀይል ድርጊት የወንጀል ፍትህ አስተዳደሩን በሚመለከት የወጡ መድብሎችን ትርጉም አልባ እንዲሆኑ እስከማድረግ ደርሷል። በአብዮቱ የተፈጠረው ንዝረት ጨቅላ በነበረው ዘመናዊ የሕግ ስርዓት ላይ ያደረሰው ጉዳት በዚህ ብቻ የተወሰነ አልነበረም። በወቅቱ ብቸኛ የነበረውን የሕግ ትምህርት ቤት ሲያገለግሉ የነበሩ ፕሮፌሰሮች አገር ለቀው በመውጣታቸው ምክንያት የሕግ ትምህርት እና የመማር ማስተማር ሂደቱ እንዲቀጭጭ አድርጎታል። ምንም እንኳን የወቅቱ የአገዛዝ ስርዓት በወቅቱ የነበረውን የሕግ ስርዓት በህብረተሰባዊ አስተሳሰብ በተቃኘ አዲስ ስርዓት ለመለወጥ ፍላጎት ያለው ስለመሆኑ ምልክቶች የነበሩት ቢሆንም በዚህ ረገድ ተጨባጭ እና ሁሉ አቀፍ የሆነ ለውጥ ሳያደርግ ቀርቷል።

በዚህ ምዕራፍ የሕግ ስርዓት ማሻሻያን በተመለከተ በልዩ ሁኔታ ሊጠቀስ የሚችለው ስኬት ኢ-ፍትሀዊ እና በዝባዥ የነበረውን የመሬት ስሪት ስርዓት በአዲስ የመሬት ስሪት ስርዓት በሕግ መቀየሩ ነው[2]። ምንም እንኳን የዚህ አዲስ የመሬት ስሪት ስርዓት እጥረቶች እና ክፍተቶች ለክርክር ክፍት ቢሆኑም ቀደም ሲል ከተካው የመሬት ስሪት ስርዓት ባሰፈነው አንጻራዊ ፍትሐዊነት ምክንያት በአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ዘንድ የነበረው ተቀባይነት ጥርጣሬ ውስጥ የሚወድቅ አይደለም። ይህ እርምጃ ህግ ማህበረሰባዊ ለውጥን ለማምጣት አይነተኛ ሚና ሊጫወት እንደሚችል ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ነው። ይህ ወቅት በአንጻሩ የፍትህ ስርዓቱ በጉልህ ትርጉም አልባ እንዲሆን ያደረጉት ከህግ ውጪ ሰዎችን የመግደል ተግባርን ጨምሮ ከህግ ውጪ የሚወሰዱ እርምጃዎች በስፋት ሲፈጸሙ የቆዩበት ወቅትም ነበር። ለፖለቲካ ስልጣን ቅድሚያ የሚሰጥ አምባገነናዊ አገዛዝ የነበረ በመሆኑ ምክንያት ለሕግ እና ሕጋዊ ስርዓቶች የሚሰጠውን ዋጋ የሸረሸረ፣ የፖለቲካ ስልጣን በሕጋዊ ስርዓት እንዳይገደብ ያደረገ ስርዓት ነበር። ከዚህ በተጨማሪ የሕግ ሰርዓቱን ከርዕዮተ-አለማዊ እሳቤ እና ፖሊሲ ጋር ማስተሳሰር

[2] አዋጅ ቁጥር 31/1967 (የገጠር መሬትን የህዝብ ለማድረግ የወጣ አዋጅ)፣ አዋጅ ቁጥር 47/67 (የከተማን ቦታና ትርፍ ቤት የመንግሥት ንብረት ለማድረግ የወጣ አዋጅ)፣ የኢ.ህ.ዲ.ሪ. ሕገ-መንግሥት፣

ባለመቻሉ ምክንያት በሀገሪቱ እስከ 1980ዎቹ ድረስ በሕግ አስተሰተሳሰብ እና ፍልስፍና ረገድ ለነበረው ቀውስ ምክንያት ሆኗል።

2.3 ድህረ 1983፡ የሕግ ስርዓቱን ፌዴራላዊ የማድረግ ሂደት

ድህረ 1983 ከፍተኛ የሆነ ምንአልባትም አብዮታዊ ሊባል የሚችል ለውጥ የተከናወነበት ወቅት ነው። በተለይም የፌዴራል ስርዓተ መንግስት የተዋወቀበት በዚህም የየራሳቸው ሕግ የማውጣት እና የመተርጎም ስልጣን ያላቸው የክልል መንግስታት የተመሰረቱበት ወቅት ነው። በዚህ ዘመን እውን የሆነው አዲሱ ህገ-መንግስታዊ ስርዓት ከአማርኛ ውጪ ሌላ የስራ ቋንቋ ያላቸውን ክልሎች ጨምሮ በቋንቋ እና ብሔር ላይ የተመሰረቱ ክልሎችን ያስተዋወቀ ነው። በዚህ ወቅት እውን የሆነው ያልተማከለ ፖለቲካዊ ስልጣን የራሳቸውን ሕግ የሚያወጡ እና የራሳቸውን ብቻም ሳይሆን የፌዴራል መንግስቱ የሚያወጣውን ሕግ የሚተረጉሙ የየራሳቸው የሕግ አውጪ እና ሕግ ተርጓሚ ያላቸው ክልሎችን የያዘ አዲስ የሕግ ስርዓትን አስተዋውቋል። ይህ የመንግስት ስልጣንን ወደክልሎች የማከፋፈል ሂደት በአንድ ማዕከል ማለትም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብቻ በመጀመሪያ ዲግሪ ደረጃ ይሰጥ የነበረውን የሕግ ትምህርት በተለያዩ ክልሎች በሚገኙ ዩንቨርሲቲዎች መስጠት እንዲቻል በማድረግ ረገድ አዎንታዊ አስተዋጽኦ ነበረው። በተጨማሪም በዚህ ወቅት ፓርላሜንታዊ ዲሞክራሲያዊ የመንግስት ስርዓትን ያስተዋወቀ እና ሰፊ የሰብዓዊ መብት ዝርዝርን የያዘ አዲስ ህገ መንግስት ጸድቆ ተግባራዊ መደረግ መጀመሩ እንዲሁም በርካታ የአለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶች በዚህ ወቅት መጽደቃቸው ለህዝብ ነክ ሕጎች (Public Laws) የሚሰጠው ትኩረት እንዲያድግ ምክንያት ሆኗል። እነዚህ በሕግ ስርዓቱ ላይ የተስተዋሉ ለውጦች በፖለቲካ መዋቅሩ ላይ በኢህአዴግ አማካኝነት የተደረጉ ለውጦች አካል ናቸው።

እነኚህ የሕግ ማሻሻያዎች የሕግ ስርዓት ብዝሀነትን ለሀገሪቱ በማስተዋወቅ ረገድ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል። ከዚህ በተጨማሪ ብዝሀ-ልሳን የሕግ ስርዓት እንዲያድግ ብሎም በክልል ደረጃ ለሚደረግ የፈጠራ እና ሙከራ ስራ ምቹ ሁኔታን የፈጠረ ነው። ከዚህ ባሻገር እነኚህ ለውጦች ለህዝብ ነክ ሕጎች የሚሰጠውን አትኩሮት ክፍ ያደረጉ ሆነው የተገኙ ሲሆን በዚህም በአጠቃላይ በሕግ ሰርዓት፣ በዲሞክራሲ፣ ፌዴራሊዝም እና ሰብዓዊ መብት ላይ የሚደረግ ምሁራዊ ጥናት እና ክርክር ከምንጊዜውም በላይ እንዲያድግ የራሱን አስተዋጽኦ አበርክቷል።

ከላይ የተዘረዘሩት ለውጦች የነበሩ ቢሆንም በወረቀት ላይ ያለው ለውጥ በተጨባጭ ከመጣው ለውጥ ጋር የሚጣጣም አልነበረም። የክልል መንግስታት የሕግ ብዝሀነት ይዞት የመጣውን እድል በአግባቡ ለመጠቀም ሳይችሉ ከመቅረታቸውም ባሻገር ለስሙ የፌዴራል መንግስት ስርዓትን የሚከተል ነገር ግን የማዕከላዊ መንግስቱ ጠንካራ የተማከለ አስተዳደር በተግባር የነበረ በመሆኑ ምክንያት በክልል ደረጃ ሊደረግ ይችል የነበረው የሙከራ እና የፈጠራ እድልን በአግባቡ ለመጠቀም አልተቻለም። ከዚህ በተጨማሪ ለዴሞክራሲያዊ አስተዳደር መስፈን የነበረው ትልም እና ለመሰረታዊ መብቶች መከበር የነበረው ህገ-መንግስታዊ ፍላጎት በተጨባጭ በመሬት ላይ ከነበረው እውነታ ጋር የማይጣጣም ነበር። ከፌዴራላዊ ሰርዓቱ ባህርይ እና ከህገ-መንግስቱ አጸዳደቅ ሂደት ጋር

በተያያዘ የነበሩ ውዝግቦች በህገ-መንግሰቱ ቅቡልነት ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖን ፈጥሯል። ከዚህ በተጨማሪም የክልሎችን የህግ ስርዓት ከፌዴራል መንግስቱ ህገ መንግስት ጋር የማጣጣም ስራም እምብዛም አልተኬደበትም። በዚህ ረገድ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ-መንግስት ከጸደቀ አንስቶ በ1952 በወጣው የፍትሐብሔር ሕግ ተካትቶ የነበረውን የቤተሰብ ሕግ ከማሻሻል እና በ1949 ወጥቶ የነበረውን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ከማሻሻል ያለፈ ይህ ነው የሚባል ሁሉ አቀፍ የሆነ የሕግ ማሻሻያ ስራ አልተሰራም።

2.4 የሁሉ-አቀፍ የፍትህ ዘርፍ ማሻሻያ ፕሮግራም

በ1994 ዓ.ም መጠነኛ የሆነው የፍትህ ስርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም ስራ ላይ እንዲውል ተደርጎ የነበረ ሲሆን በኋላም በ1997 ዓ.ም ሁሉ-አቀፍ የሆነ የሁኔታዎች መነሻ ጥናትን መሰረት በማድረግ ሁሉ-አቀፍ የፍትህ ዘርፍ ማሻሻያ ፕሮግራም በስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል[3]። ይህ ሁሉ-አቀፍ የፍትህ ዘርፍ ማሻሻያ ፕሮግራም በአይነቱ እና በጥልቀቱ ከቀድሞዎቹ የማሻሻያ ፕሮግራሞች የተለየ ሲሆን መንግስት የህዝባዊ አገልግሎት ዘርፍን ለማሻሻል የነደፈው የማሻሻያ ፕሮግራም አንድ አካል ሆኖ ከረጂ ወይም ደጋፊ ተቋማት ጋር በትብብር የተዘጋጀ ነው። ለዚህ የማሻሻያ ፕሮግራም መነሻ የሆነው የሁሉ-አቀፍ የሁኔታዎች መነሻ ጥናት የተከናወነው ከውጭ ሀገር በመጣ የተለየ ልምድ ባለው ተቋም (ዓለም አቀፍ የሕግ ትብብር ማዕከል) አማካኝነት ሲሆን በጥናቱም ከዩንቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ቤቶች አንስቶ እስከ ማረሚያ ተቋማት ድረስ መዳሰስ ተችሏል። ይህ ጥናት በማጠናቀቂያው ተጨባጭ የሆኑ እና የፍትህ ዘርፉን ከስሩ መለወጥን የሚጠይቁ ምክረ-ሀሳቦችን አስቀምጧል። ከእነኚህም ምክረ-ሀሳቦች መካከል አብዛኞቹ በተለይም ደግሞ የሕግ ትምህርትን እና በፍትህ ስርዓቱ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ረገድ የተሰነዘሩት ምክረ-ሀሳቦች ተቀባይነትን አግኝተዋል። ምንም እንኳን በጥናቱ የተጠቆሙት ምክረ-ሀሳቦች በርካታ እና ሁሉን አቀፍ የነበሩ ቢሆንም በተግባር ግን እነኚህ ምክረ-ሀሳቦችን ተቀብሎ ስራ ላይ በማዋል ረገድ ሰፊ ክፍተት እንደነበር ለማስተዋል ይቻላል። ለዚህ የትግበራ ክፍተት ዋነኛ ምክንያት ተደርገው ሊወሰዱ ከሚችሉ ጉዳዮች መካከል ደግሞ አንዱ ምርጫ 97ን ተከትሎ በወቅቱ በነበረዉ መንግሥት በኩል የማሻሻያ ጥናቱ በኒዮ ሊበራሊዝም ቅኝት የተካሄደ በመሆኑ ከአብዮታዊና ልማታዊ ዲሞክራሲ አስተሳሰብ ጋር ሊጣጣም አይችልም የሚል እምነት መያዙ ነዉ። ሁለተኛዉ በወቅቱ የፍትህ ዘርፉን ለማሻሻል በመንግስት በኩል የነበረው ቁርጠኝነት ይገለጽበት የነበረው የአቅም ግንባታ ሚኒስቴር መፍረስ እና ይህ ቁርጠኝነት ተቋም ላይ የተንጠለጠለ እንጂ የመንግስት የፖለቲካ ቁርጠኝነት ያልታከለበት በመሆኑ ሳቢያ ይህ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ሲፈርስ አብሮ የፕሮግራሙ ተፈጻሚነት በፐብሊክ ሰርቪስ ኮሚሽንና በፍትህና ሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት የተወሰኑ ጥረቶች ሲደረጉ የነበረ ቢሆንም የተዳከመ ነበር። በሌላ በኩል በፍትህ ዘርፉ ተቋማት የሚታየው የአመራር መለዋወጥ የተጀመሩ የለውጥ እና ማሻሻያ ሂደቶች ቀጣይ እንዳይሆኑ እና ዳር እንዳይደርሱ የራሱን የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል። ይህም ሆኖ ይህ የማሻሻያ ፕሮግራምም ሆነ ሌሎች የማሻሻያ ሙከራዎች በፍትህ ዘርፉ

[3] የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም ጥናት ሪፖርት፣ የአቅም ግንባታ ሚኒስቴር- የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም ጽ/ቤት፣ መጋቢት 1997

በተለይ ደግሞ በሕግ ትምህርት የካሪኩለም ለውጥ እና በሕግ ትምህርት ቤት መምህራን አቅም መጎልበት ላይ ያመጣው አዎንታዊ ለውጥ የሚካድ አይደለም[4]። በአጠቃላይ ሲታይ ግን ሁሉ-አቀፍ መሻሻልን ለማምጣት ታስቦ የተጠናው ሁሉ-አቀፍ የሁኔታዎች መነሻ ጥናት እና ከዚህ ጥናት የመነጩት አብዛኞቹ ምክረ-ሀሳቦች በታለሙበት አግባብ እና ደረጃ ተፈጻሚ ሳይሆኑ የቀሩ ስለመሆኑ ግንዛቤ መውሰድ ያስፈልጋል[5]።

2.5 ድህረ-2010 የሕግ እና ፍትህ ማሻሻያ

ድህረ-2010 የተደረጉት የሕግ ማሻሻያ ጥረቶች እንደ ድህረ 1966 እና 1983 የሕግ ማሻሻያ ጥረቶች ሁሉ በሀገሪቱ በተፈጠረ የፖለቲካ ምህዳር ለውጥ አማካኝነት የመጡ ናቸው። ሰፊ እና ተከታታይነት የነበራቸው ህዝባዊ ተቃውሞዎች እና የመብት ጥያቄዎችን ተከትሎ በ2010 ዓ.ም በኢትዮጵያ የመንግስት ለውጥ የተደረገ መሆኑ ይታወሳል። ይህ የለውጥ መንግስት በቅድሚያ ለህዝቡ ከገባቸው ቃሎች መካከል በዴሞክራሲ ግንባታ ረገድ ሰፊ ማሻሻያዎችን የሚያደርግ መሆኑ ዋነኛው ነው። በዚህም መሰረት መንግስትን የሚያማክር የሕግ እና ፍትህ ጉዳዮች አማካሪ ምክር ቤት የተቋቋመ ሲሆን ይህ ምክር ቤት በተለይ በሕግ እና ፍትህ ዘርፍ ሊከናወኑ የሚገባቸው የማሻሻያ ስራዎችን አስመልክቶ መንግስትን እንዲያማክር የተቋቋመ ነው። የአማካሪ ምክር ቤቱ የስራ ፍኖተ ካርታ በማዘጋጀት ሊከናወኑ የሚገባቸው የሕግ ማሻሻያ ስራዎችን በመለየት በተለይ አፋኝ እና ገዳቢ የነበሩ እና ለአገዛዝ አላማ ታስበው የወጡ ሕጎች በመለየት የማሻሻያ ስራዎችን ሰርቷል። ምክር ቤቱ ለረጅም ጊዜ የማሻሻል ሂደታቸው ተጓትቶ የነበሩ እንደ የወንጀል ስነስርዓት እና የማስረጃ ሕግ እና የንግድ ሕግ መድብል ያሉትን የማጠናቀቅ ሀላፊነት ወስዶ ለመስራት ችሏል። ከዚህ በተጨማሪ አማካሪ ምክር ቤቱ የምርጫ ቦርድን እንደገና ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ በማስጸደቅ ረገድ የመሪነት ሚናን ተጫውቷል። እነኚህ የሕግ ማሻሻያ ስራዎች ሀገሪቱ በአለም አቀፍ የሰብኣዊ መብት ስምምነቶች ከገባችባቸው ግዴታዎች ጋር የተጣጣሙ ሕጎች እንዲኖራት፣ የብሔራዊ የምርጫ አስተዳዳሪ አካል ዲሞክራሲዊ ተኣማኒነቱ እንዲጨምር እና ለረጅም ጊዜ በስራ ላይ የነበረው የንግድ ሕግን በማሻሻል ዘመኑን የዋጀ ህግ እንዲሆን በማድረግ ረገድ አዎንታዊ ውጤቶችን አምጥቷል። ከዚህም ባሻገር ዜጎች ከአሰተዳደራዊ ጉዳይ የሚመነጩ ቅሬታዎቻቸውና አቤቱታዎች ላይ የመንግስት አሰራር በግልጽነትና ተጠያቂነት ባለው መልኩ እንዲፈታና እነዚህ ማዕቀፎች መፍትሔ መስጠት በማይችልበት ጊዜ በማናቸውም አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ላይ የፍ/ቤት ክለሣን ያስተዋወቀ የፌደራል ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ወደስራ እንዲገባ ማድረግ ተችሏል። በተጨማሪም የፍርድ ቤቶች አደረጃጀት እና አስተዳደር በተመለከተ የወጡ ስር ነቀል ሕጎች ፍርድ ቤቶች ከምንጊዜውም በተሻለ ነጻ እና ገለልተኛ እንዲሆኑ አድርገዋል።

በፍ/ቤቶች ለውጡን ተከትሎ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በሚመራው የዘርፉ አብይ ኮሚቴ አማካይነት የወንጀል ፍትህ የ3 ዓመታት ፍኖተ ካርታ ተዘጋጅቷል፣ የተለያዩ ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ ሰፋፊ ጥናቶች ተካሂደዋል፣ የዳኞችን ብቃትና አፈጻጸም ለማሳደግ በተከናወኑ ሥራዎች የአፈፃፀም መሻሻል አምጥተዋል፣ የዳኞች የስነ-ምግባር እና

[4] Ethiopia, Legal and Judicial Sector Assessment, The World Bank, 2004, p. 34-35
[5] የፍትህና ሕግ አማካሪ ካዉንስል ጥናት፣

የዲሲፕሊን ኮሚቴ አሳታፊ በሆነ መልክ እንደገና በመደራጀትና ከአስፈጻሚው ተጽእኖ በመላቀቅ ስራውን ጀምሯል፣ የዳኞች ምልመላ፣ ምደባና ዝውውር አፈፃፀም በተመለከተ ከለውጡ በፊት በዝምድና እና በብሄር ምልመላ የነበረዉ ተቀይሮ አሁን ግን ጥሩ ነጥብ፣ ጥሩ ስነ-ምግባር፣ ጥሩ ብቃት ካለው ያልፋል፣ ዳኞች ስራቸውን በነፃነት እንዲሰሩ ተደርጓል፣ ውዝፍ መዝገብ እንዲቀንስ ተደርጓል፣ እንዲሁም ለእያንዳንዱ ጉዳይ የጊዜ ገደብ እንዲቀመጥ ተደርጓል፣ በተጨማሪም የአንድ መስኮት አገልግሎት እንዲተዋወቅ ተደርጓል፣ የጉዳዮች መዘግየት ሙሉ ለሙሉ ባይጠፋም ቀንሷል፣ ለጉዳዮች አጫጭር ቀጠሮ መስጠት ተጀምሯል፣ የዳኞች ብቃት ከማሳደግ ጋር በተያያዘ በጣም በተለያዩ ርእሶች ላይ ስልጠና መስጠት ተችሏል፣ የጉዳዮች ፍሰትን በተመለከተ የማስተግበሪያ ማኑዋል ወጥቷል፣ በህግ ማሻሻያው ሁለት አዋጆች ተዘጋጅተው ለፓርላማ ቀርበው ፀድቀዋል፣ በእነዚህ አዋጆች ላይ ተመስርቶ 29 የሚሆኑ ደንቦችና መመሪያዎች ተዘጋጅተው ከዚህ ወስጥ 10 የሚሆኑ ደንቦችና መመሪያዎች በጠቅላይ ፍርድ ቤት እና በዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ፀድቀዋል፣ የዳኞች የስነ-ምግባር ደንብ እና የክስ ስነ-ስርዓት ደንብ እንዲሻሻል ተደርጓል፣ የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር አዳዲስ አሰራሮች ተግባሪዊ ሆነዋል፣ የፍ/ቤት መር አስማሚነት መመሪያ ወጥቶ ተግባራዊ ተደርጓል፣ የፍ/ቤቶችን የሥልጣን ድልድል በማሻሻል ግልጽ ተደርጓል፣ በጀትም በፍ/ቤቱ በኩል ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ቀርቦ እንዲፀድቅ ተደርጓል። የፌደራል ፍ/ቤቶችን አገልግሎት ተደራሽነት ለማስፋት አዋሳና አካባቢው እንዲሁም ሌሎች ቦታዎች ላይ ምድብ ችሎት እንዲደራጅ መደረጉ፣ በአዲስ አበባ አዲስ እንዲገነቡ በተደረጉ ህንጻዎች የዳኝነት አገልግሎት መስጠት መጀመሩም ተጠቃሽ ናቸዉ። ይህ ሁሉ ሆኖም ከተገልጋይ እርካታና የህዝብ አመኔታ ላይ ገና አልተደረሰም። ከላይ የተገለጹት የለውጡ ውጤቶች ቢኖሩም የፌደራል ፍርድ ቤቶችን አገልግሎት ለማሻሻል በመከናወን ላይ ያሉ የማሻሻያ ሥራዎችን ተከትሎ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የታዩ ለውጦችን በተመለከተ ከሌሎች በበለጠ በተገልጋዮች በተደጋጋሚ የተመረጠው የታየው ለውጥ መካከለኛ ደረጃ ላይ ይገኛል የሚል ነው። በሌላ በኩል የተሰጡ ምላሾች አማካይ (mean) ሲታይ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያረፈ ሲሆን ምላሽ ከሰጡት 66.3 በመቶ የሚሆኑት ደረጃው የተለያየ ቢሆንም ለውጥ መኖሩን የገለጹ ሲሆን 23.5 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ የታየ ለውጥ የለም ብለዋል[6]።

በፍትህ ሚኒስቴር ለውጡን ተከትሎ ተቋሙን በብዙ መንገድ ለማሻሻል ሙከራ እየተደረገ እንደሆነ በተለይም የዜጎች የዕለት ተዕለት ኑሮ እና የሰብዓዊ መብት ላይ ተጽዕኖ ያላቸው ሕጎች በማሻሻል ረገድ ትልቅ ስራ ስለመሰራቱ፣ የሕግ ማውጣት ሂደቱ የዜጎችን ተሳትፎ እንዲያረጋግጥ ጥረት ስለመደረጉ፣ ተቋሙ የሕግ ማስከበር ኃላፊነቱን ከመወጣት አንጻርም አይኔኬ የተባሉና የሀገር ሀብት የመዘበሩ ግለሰቦችን በሕግ ፊት የማቅረብ ስራ ስለመስራቱ፣ የዓቃቢያነ ሕግን ብቃት ለማሳደግ ቁልፉ ትምህርት እና ስልጠና በመሆኑ ለዚህ

[6] የፌዴራል ፍትህና ሕግ ኢንስቲትዩት፣ የፌዴራል ፍትሕ ዘርፍ ተቋማት መልካም አስተዳደር /አገልግሎት አሰጣጥ/ ጥናት አጭር ማጠቃለያ ፣ ነሐሴ 2014 ዓ.ም. አዲስ አበባ፣ ገጽ 16

ትኩረት በመስጠት እራሱን የቻለ መዋቅር እንዲኖረውና በዕቅድ እንዲመራ መደረጉን፣ የሲቨክ ማህበራት ሕግ መሻሻሉ፣ የወንጀል ፖሊሲ መውጣቱ፣ የጥብቅና አገልግሎት ሕግ መሻሻሉ፣ የኢትዮጵያ አገራዊ ሰብአዊ መብቶች የ5 ዓመት ዕቅድ መዘጋጀቱ፣ የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ህግ ማሻሻያ ጥረት ተደርጓል[7]። እነዚህ አዎንታዊ የሆኑ ውጤቶች የተመዘገቡ ቢሆንም አሁንም በተገልጋዩ ሕብረተሰብ ዘንድ በፍትህ ሚኒስቴር አገራዊ ለውጡን /ማሻሻያ/ ተከትሎ በተቋሙ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ በታዩ ለውጦች የተገልጋዮች የእርካታ ደረጃን በተመለከተ ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ለመረዳት እንደሚቻለው አብዛኞቹ ተገልጋዮች በተቋሙ አገልግሎት ስላላቸው እርካታ መካከለኛ ደረጃ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል[8]። በተመሳሳይ ጥናት እንደተደረሰበት በተቋሙ ከሥነ-ምግባርና ዲስፕሊን ጋር የተያያዘ ሰፊ ክፍተት መኖሩ ሁኔታዉን ለመቀየር ከተቋሙ ከፍተኛ ጥረትና ቁርጠኝነት የሚጠይቅ መሆኑን ያመላክታል።

በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽንም *አንደኛ* ከሰብዓዊ መብቶች አያያዝ አንፃር አወንታዊ የሚባሉ ለውጦች በተለይም የሰብዓዊ መብቶች አያያዝ የፖሊስ የሥራ መርህ መደረጉ፣ ገዳይ ያልሆኑ (Non-lethal) መሳሪያዎች ሥራ ላይ እየዋሉ መሆናቸው፣ ድብደባን ሊያስቀሩ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎች እንደ የደህንነት ካሜራዎች መገጠማቸው፣ የፎርጅድ ሰነድ ምርመራ መሳሪያ ቪሲ 8ሺ መገዛቱ እና የ(DNA) መሳሪያ ተከላ መደረጉ፣ ተጠርጣሪዎች ከቤተሰቦቻቸው ወይም ከጠበቆቻቸው እንዲገናኙ ሁኔታዎች መመቻቸቱ፣ እና የተጠርጣሪዎች አያያዝ ለሶስተኛ ወገን ለጉብኝት ክፍት መደረጉ ተለይተዋል። ***ሁለተኛ፡*** ሪፎርሙ በፖሊስ አባላት የአመለካከት ለውጥ እያመጣ መሆኑን በተለይም አንድ ፖሊስ ከወንጀል ጋር ተያይዞ መረጃን ለማግኘት ቴክኒክና ታክቲክ በመጠቀም እንጂ ተጠርጣሪን በመደብደብ እንዳልሆነና የወንጀል ምርመራ ሥራ ሙያና ሳይንስ መሆኑ ግንዛቤ እያደገ መሆኑ፤ ምንም እንኳን የሚቀረው ቢኖርም በንጽጽርና በተወሰነ መልኩ ፖሊስ ሥራውን የሚያከናውነው ከፖለቲካ ወገንተኝነት ነፃ ሆኖ ሙያዊ የሆነ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑ፤ ተቋሙ ግን ሙሉ በሙሉ ከፖለቲካው ነጻና ገለልተኛ እንዳልሆነ በጥናቱ ተለይተዋል። ***ሦስተኛ፡*** በሪፎርሙ አማካኝነት የቴክኖሎጂ ግብዓቶችን በመጠቀም ስራዎች እየተሰሩ መሆናቸው በተለይም የፖሊስ የፎሬንሲክ ዲፓርትመንት በማሳደግና በቴክኖሎጂ በማደራጀት የወንጀል ምርመራ ሂደትን ሊደግፉ የሚችሉ የተለያዩ አገልግሎቶችን መስጠት መጀመራቸው፣ የደህንነት ካሜራዎች ቅድሚያ በተሰጣቸው አካባቢዎች መገጠማቸው፣ የፎርጅድ ሰነድ ምርመራ መሳሪያ ቪሲ 8ሺ መገዛቱ እና የዘረመል (DNA) መመርመሪያ መሳሪያ ተከላ መደረጉ በጥናቱ በግኝት ተለይተዋል። ***አራተኛ፡*** ሪፎርሙ ከተቋማዊና ገጽታዊ ግንባታ አንፃር ሲታይ የፖሊስ ኮሌጅ ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ማለትም ወደ ዩኒቨርሲቲ እንዲያድግ መደረጉ፣ የፖሊስ ባለሙያዎችን በፖሊስ ዩኒቨርሲቲው ለማፍራት እየተቻለ መሆኑ፣ ከዚህ በፊት ሰብዓዊ መብቶች ሲጣስባቸው የነበሩ ማእከላት እንዲዘጉ መደረጋቸው፣ የፖሊስ ማእረግ ስሞች ወደ ሀገርኛ

[7] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 20
[8] ዝኒ ከማሁ

ቋንቋ ተቀይሯል፤ የፖሊስ ዶክትሪን ተዘጋጅቷል[9]። ከነዚህ ሁሉ በተጨማሪም በሀገሪቱ ሲካሄድ በነበረዉ የሕግ ማስከበር ተግባር ላይ ፖሊስ በከፍተኛ ደረጃ በሕይወት መስዋእትነት ከፍሎ የተሠራዉ ሥራ፣ በብዙ ቢሊየን የሚቆጠር የሕዝብና የሐገር ሀብት የመዘበሩትን ለሕግ ለማቅረብ የተሠሩ ሥራዎችም ጎልተዉ የሚታዩ ናቸዉ።

በማረሚያ ቤቶች ኮሚሽንም ኮሚሽኑ የሠራተኞቹን ሥነ-ምግባርና ዲስፕሊን ለማሻሻል የተለያዩ ጥረቶችን በማድረግ ውጤት የታየበት መሆኑ፣ ማረሚያ በኮሚሽኑ በርካታ የለውጥ ሥራዎች በመሰራታቸው የኮሚሽኑ አገልግሎት አሰጣጥ ታራሚ ተኮር እንዲሆን እንዲሁም የተሻለ የታራሚዎች ሰብዓዊ መብቶች አከባበር እንዲኖር አስችሏል። በአጠቃላይ በፌዴራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን የተከናወኑ የለውጥ ሥራዎችን ውጤታማነትን ለመለካት እንደተሞከረው፤ የፌዴራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን አደረጃጀት ተልዕኮውን በብቃት ለማሳካት ማስቻሉን በተመለከተ የተሻለ ደረጃ ላይ ይገኛል። የታራሚዎች ጉብኝት አሰራሩን በተመለከተ የታራሚ ጠያቂዎች ለውጥ ስለመኖሩና የተሸለ ሁኔታ መኖሩን ይገልጻሉ[10]።

ይሁን እንጂ ይህ የለውጥ ሂደት ሊጠቀሱ የሚችሉ ውስንነቶችም ነበሩበት። ከእነኚህ ውስንነቶች መካክል ለውጡን ተከትሎ የተፈጠሩ መነቃቃቶች እና የተስፋ ስሜቶች በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች በተፈጠሩ ግጭቶች ምክንያት አሉታዊ ጥላ እንዲያጠላበቸው ሆኗል። በዚህም ሳቢያ በለውጡ ምክንያት እውን የሆኑ የህግ ማሻሻዎች በታለመላቸው ልክ እንዳይተገበሩ እንቅፋት ሆኗል። ሌላው በውስንነት ሊጠቀስ የሚገባው ጉዳይ በዚህ የሕግ እና ፍትህ ማሻሻያ ስራ ትኩረት ተሰጥቶት የተሰራው የሕግ ማሻሻያ ስራ በመሆኑ ምክንያት ሙያዊ ብቃትን እና ምልዑነትን ከማሳደግ አንጻር ከብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እና የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን በስተቀር በፍትህ አካላት ይህ ነው የሚባል ተቋማዊ ለውጥ ላይ የተገኘ ውጤት አልነበረም። በዚህም ሳቢያ በፍትህ ዘርፉ የሚገኙ ተቋማት በከፍተኛ ደረጃ በሙስና እና ብልሹ አሰራር እንዲፈተኑ ምክንያት ሲሆን በዚህም ሳቢያ እነኚህ ተቋማት የሚሰጡት አገልግሎት በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዳያገኝ የራሱን አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛል። በሌላ በኩል በፍትህ ዘርፉ ሊኖር የሚገባው የተጠያቂነት ደረጃ የዳኝነት (የፍትህ አካላት) ነጻነትን በማሳካት ረገድ ከተገኘው ውጤት አንጻር ሲታይ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። በሌላ በኩል በሀገሪቱ በተፈጠረው የፖሊቲካ ለውጥ የፍትህ ዘርፉን የሚመለከት የጋራ የሆነ ፍኖተ-ካርታ (Road map) ወይም ስትራቴጂ ያልተዘጋጀና በቂ ወይም ሰፊ የሆነ የጋራ መግባባት ያልተፈጠረ በመሆኑ ምክንያት በፍትህ ተቋማት መካከል ያለው መናበብ መቀናጀት ላይ ክፍተት ተስተውሏል[11]።

2.6 ሊወሰዱ የሚገባቸው ትምህርቶች

ከላይ ለማሳየት በተሞከረው አግባብ በተለያዩ ጊዜያት እና አውዶች ተግባራዊ ከተደረጉ የፍትህ ስርዓቱ ማሻሻያ

[9] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 25-26
[10] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 30-33
[11] የፌዴራል ፍትህና ሕግ ኢንስቲትዩት፣ የፌዴራል ፍትሕ ዘርፍ ተቋማት መልካም አስተዳደር /አገልግሎት አሰጣጥ/ ጥናት ሪፖርት፣ ነሐሴ 2014 ዓ.ም. አዲስ አበባ

ጥረቶች ውጤት እና ውስንነት በመነሳት በቀጣይ በዘርፉ ለሚደረጉ የማሻሻያ ስራዎች ትምህርት መውሰድ አስፈላጊ በመሆኑ ከዚህ በታች ዋና ዋና ሊወሰዱ የሚገባቸው ጉዳዮች ተዘርዝረዋል።

- በ1950ዎቹ በጅምላ ከውጭ ሀገራት ሕጎችን በቀጥታ ከመውሰድ ልምድ የምንወስደው ትምህርት ቢኖር በቀጥታ የውጭ ሀገራትን የሕግ ስርዓት መቅዳት የራሱ ውስንነቶች ያሉት መሆኑን እና የሕግ ብዝሀነት አስፈላጊ መሆኑን ነው። በዚህ ወቅት የተደረገው የሕግ ስርዓት ማሻሻያ ሀገር በቀል ለሆኑ የሕግ ስርዓቶች እና ልምዶች ተገቢውን ቦታ ያልሰጠ በመሆኑ ምክንያት ከውጭ የተቀዳው የሕግ ስርዓት በሚፈለገው ደረጃ ውጤታማ ሊሆን አልቻለም። በዚህም ሳቢያ ከውጭ የተቀዳው የሕግ ስርዓት እና ተቋማቶቹ ለአብዛኛው ኢትዮጵያዊ በአካልም ሆነ በባህል ተደራሽ እንዳይሆኑ አድርጓል። ከስድስት አስርት አመታት የትግበራ ጊዜ በኋላም ህዝብን ያገለግላል ተብሎ የታለመው መንግስታዊው እና ዘመናዊው የሕግ ስርዓት በህብረተሱ ዘንድ እንደክፉ፣ የማይጋፉት ከውጭ የተጫነ ነገር ተደርጎ ይወሰዳል። ስለሆነም በቀጣይ የሚወሰድ ማንኛውም ዋና የሕግ ስርዓት ማሻሻያ ጥረት ከዚህ ሁኔታ ትምህርት በመውሰድ በዚህ ረገድ የነበሩ ጉድለቶችን ሊያርም ይገባል። በዚህም መስረት መደበኛው የሕግ ስርዓት በህብረተሰቡ ዘንድ ቅቡል ይሆን ዘንድ በባህላዊው ወይም ልማዳዊው የሕግ ስርዓት እና በመደበኛው ሕግ ስርዓት መካከል መናበብን እና መሰናሰልን መፍጠር ያስፈልጋል።

- ከላይ ለመጠቆም እንደተሞከረው ስኬታማ እና የተጠናከረ የሕግ ስርዓት ማሻሻያ ስራዎች ውጤታማ እንዳይሆኑ እና ስር እንዳይሰዱ ከፍተኛ ሳንካ የሆነው የፖለቲካ አለመረጋጋት እና የደህንነት እጦት ነው። በየጊዜው የነበረው የፖለቲካዊ ርዕዮተ-ዓለም ስር ነቀል ለውጦች እና ከእርሱ ጋር ተያይዘው የተከሰቱት ግጭቶች የዘመናዊት ኢትዮጵያ ታሪክ መገለጫዎች ናቸው። ይህ ሁኔታ ደግሞ በሕግ እና ፍትህ ዘርፉ እድገት ላይ የራሱን የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ ፈጥሯል። በ1966 የተከሰተው አብዮት በፍትህ ዘርፉ እድገት ላይ ጉልህ የሚባል አሉታዊ ተጽዕኖን ፈጥሮ አልፏል። በ1983 የተደረገው የመንግስት ለውጥን ተከትሎ በተለይ በዳኝነት አካሉ ላይ የተደረገው የባለሙያዎች ከስራ መሰናበት በፍትህ ዘርፉ ላይ ከፍተኛ ጉዳትን አስከትሏል። በቅርቡ የተደረገው የመንግስት ለውጥን ተከትሎ የመጡ የፍትህ ዘርፉ ማሻሻያ ጥረቶችም ውጤታማ እንዳይሆኑ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተከሰቱ ማህበረሰባዊ ግጭቶች እና የእርስ በእርስ ጦርነት ከፍተኛ አፍራሽ ሚናን ተጫውተዋል። ስለሆነም በቀጣይ ለሚወሰዱ የፍትህ ስርዓት ማሻሻያ እርምጃዎች ስኬት የሀገር አንጻራዊ ሰላም እና መረጋጋት እጅግ አስፈላጊ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል።

- ሕግ የሚጸድቀው የሰውን ልጅ ጠባይ እና ግንኙነት ለመግዛት እና ለማረቅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ሕግ የአንድ ማህበረሰብን ፍላጎት እና ትልም መግለጫም ሆኖ ያገለግላል። እዚህ ጋር ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ ቢኖር የትኛውም ማህበረሰብ ላወጣው ሕግ ፍጹም ተገዢ ይሆናል ማለት አይቻልም። በመጽሀፍ ላይ ያለው ሕግ እና በተጨባጭ በመሬት ላይ ያለው የሕጉ አተገባበር ሁኔታ መካከል ልዩነት መፈጠሩ

ተፈጥሯዊ እና ተቀባይነት ያለው ነው። ይሁን እንጂ ይህ በጸደቀው ሕግ እና በተግባር ባለው አፈጻጸም መካከል ያለው ልዩነት በእጅጉ የሰፋ ሆኖ በሚገኝ ጊዜ አሳሳቢ ከመሆኑም በላይ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድበት ይገባል። በጸደቀው ሕግ እና በተግባር ባለው አፈጻጸም መካከል ያለው ልዩነት ከፍተኛ በሚሆንበት ጊዜ ህብረተሰቡ ለሕግ እና ፍትህ ስርዓቱ ያለው ተአማኒነት እና ስርዓቱ በህብረተሰቡ ዘንድ የሚኖረው ቅቡልነት አደጋ ላይ ይወድቃል። ባለፉት ጥቂት አስርት አመታት በኢትዮጵያ የጥራት ደረጃቸው እጅግ ከፍተኛ የሆኑ ሕጎች ጸድቀው ወደስራ የገቡ መሆኑ የሚታወቅ እውነታ ነው። ይሁን እንጂ የእነኚህ ሕጎች አፈጻጸም ህጎቹ ሲወጡ በታሰቡበት ደረጃ አይደለም። ስለሆነም በቀጣይ የሕግ ስርዓታችንን ጠንካራ እና ውጤታማ ማድረግ የሚያስፈልገን ከሆነ በሚወጡ ሕጎች እና በአፈጻጸማቸው መካከል ያለውን ልዩነት ማጥበብ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ተግባር መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል።

- የሕግ እና ፍትህ ስርዓት ማሻሻያ ስራ በዘርፉ ከፍተኛ የቴክኒክ እውቀትን እና ሙያዊ አተገባበርን የሚፈልግ መሆኑ የሚታመን ቢሆንም ቅደም ተከተልን በመለየት እና አፈጻጸሙን በመከታተል ረገድ ፖለቲካዊ ድጋፍ እና አመራር ያስፈልገዋል። ስለሆነም ፖለቲካዊ ፍላጎት፣ ባለቤትነት እና ቁርጠኝነት በሕግ እና ፍትህ ዘርፉ ለሚደረግ ማንኛውም የማሻሻያ ጥረት ሂደት የማይተካ ሚናን ይጫወታል። አንድ የሕግ እና ፍትህ ማሻሻያ ስራ ከመነሻው ጀምሮ የፖለቲካ እና ፖሊሲ ውሳኔ በሚያሳልፈው አካል ወይም ተጽዕኖ ፈጣሪዎች ዘንድ ተቀባይነትን ካላገኘ እና ይህ አካል ወይም ተጽዕኖ ፈጣሪዎች የሂደቱ እና ውጤቱ ባለቤት ካልሆኑ አስቀድሞ እንደሚወድቅ ይታመናል። በተወሰኑ የፍትህ እና ሕግ ማሻሻያ ጥረቶች ላይ ሙያዊ የሆኑ ጥረቶች እና ስራዎች ከፖለቲካ እና ፖሊሲ ወሳኞች ጥረት ቀደም ብሎ ሲሄድ የታየባቸው ሁኔታዎች የነበሩ ሲሆን እነኚህ ሂደቶች ፖለቲካው ክንፍ ያን ያክል ድጋፍ ያላገኙ የባለሙያዎች የሙያ ሀሳብ ብቻ ሆነው ተግባራዊ ሳይሆኑ ቀርተዋል። ስለሆነም ማንኛውም አይነት በሕግ እና ፍትህ ዘርፉ የሚደረግ የማሻሻያ ስራ ከንድፉ አንስቶ እስከመጨረሻ አተገባበሩ ድረስ በዋና ዋና የአፈጻጸም ምዕራፎች ፖለቲካዊ ቅቡልነት እና ድጋፍ የሚያስፈልገው እንዲሁም በመደበኛነት ተገቢውን ክትትል ማድረግና የለውጥ ውጤቶችን በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል።

- ቀደም ሲል በሀገራችን የተሞከሩ የሕግ እና ፍትህ ማሻሻያ ስራዎች የተማከሉ እና ህብረተሰቡን እና አካባቢን ከግምት ሳያስገቡ ለሁሉም ወጥ የሆኑ ነበሩ። በዚህም ምክንያት የማሻሻያ ጥረቶቹ ውጤታማ ሳይሆኑ እንደቀሩ ከላይ ለማሳየት ተሞክሯል። ማንኛውም የፍትህ እና ሕግ ማሻሻያ ስራ ሀገራዊ ከሆነው ለውጥ በተጨማሪ በክልል፣ በታችኛው የአስተዳደር መዋቅር እንዲሁም በማህበረሰብ ደረጃ ያሉ ሁኑታዎችን ከግምት ማስገባት ይኖርበታል። የክልል እና የታችኛው የአስተዳደር መዋቅርን ሁኔታ ከግምት የሚያስገባ እና አስፈላጊውን ድጋፍ የሚሰጥ የማሻሻያ ስራ አጠቃላይ የሆነ በጎ ውጤትን እንደሚያመጣ

ይታመናል። በሀገራችን ባሉ ማህበረሰቦች መካከል ያለውን የተለያየ ልዩነቶች እና ብዝሀነት ከግምት በማስገባት የሚደረጉ የማሻሻያ እርምጃዎች በእነኚህ ማህበረሰቦች አውድ የተቃኘ ፈጠራዎችን ጭምር ያካተተ መሆን ይገባዋል። ምንም እንኳን ሀገራዊ የሆነ የማሻሻያ መዋቅሮች እና ስታንዳርዶች እንዲሁም ቅንጅት የሚያስፈልግ መሆኑ የሚታመን ቢሆንም ይህ ደግሞ በተቃራኒው የተዝረከረከ የለውጥ አመራርን ወይም ደግሞ በታችኛው የአስተዳደር መዋቅር ደረጃ ሊደረጉ የሚገባቸውን ፍላጎትን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ የለውጥ ሀሳቦችን እና ፈጠራዎችን የሚጨፈልቅ እንዳይሆን ከፍተኛ ጥንቃቄን ማድረግ ያስፈልጋል። በቀጣይ የሚደረጉ ማናቸውም አይነት የፍትህ ዘርፍ ማሻሻያ ስራዎች ክልሎች እና የታችኛው የአስተዳደር መዋቅር የሚያገለግሉትን ማህበረሰብ የፍትህ ፍላጎት የሚያሟሉ አዳዲስ መፍትሔዎችን እንዲወስዱ የሚያበረታታ መሰረተ-ሰፊ ስምምነት ላይ የተመሰረተ ሀገራዊ ማዕቀፍ እንዲፈጠር በሚያስችል መልኩ ተቀርጾ ተግባራዊ መሆን አለበት።

- ፍትህ የአስተዳደር ተቋማት ለዜጎች የሚሰጡት ተራ አገልግሎት አይደለም። ይልቁንም በመርህ ላይ ተመስርቶ በገለልተኝነት እና በፍትሐዊነት ውሳኔ መስጠትን የሚመለከት ነው። ይህንን ውሳኔ የሚሰጡ አካላት እና ባለሙያዎች ምሉዕ ስብዕና የተላበሱ እና ብቃት ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል። በመሆኑም ባለሙያዎች ከእውቀት፣ ክህሎት እና ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ያላቸው ምሉዕ ስብዕና እና አመለካከት እንዲሁም ለሙያ ስነምግባር ያላቸው ጠንካራ ተገዢነት እጅግ በጣም ወሳኝ እና አስፈላጊ ነው። በሙያው በአግባቡ ያልሰለጠነ እና አላዋቂ ዳኛ፣ ዐቃቤ ሕግ ወይም ፖሊስ ምንም ያህል ቅን-ልቦና ቢኖረው/ቢኖራት በያዘው/በያዘችው ጉዳይ ፍትህን ለማስፈን ወይም ፍትሐዊ ውሳኔ ለመስጠት እንደሚከብደው/እንደሚከብዳት አያጠራጥርም። በተመሳሳይ በሙያው ከፍተኛ ክህሎት እና እውቀት ያለው/ያላት ዳኛ፣ ዐቃቤ ሕግ ወይም ፖሊስ የሥነ-ምግባር ጉድለት ካለበት/ካለባት የፍትህ ጥያቄን ሙያዊ በሆነ እና በተወሳሰበ መልኩ ከማጣመም አልፎ/አልፋ ፍትህን በትክክል ለመስጠት አይችልም/አትችልም። ስለሆነም የፍትህ ዘርፍ ባለሙያዎች ሙያዊ ብቃት እና ምሉዕ ስብዕና ተነጣጥሎ የማይታይ እና በፍትህ ዘርፉ የማሻሻያ ስራዎች የቅድሚያ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራ የሚገባ ጉዳይ ነው። በመዋቅር ማሻሻያ፣ በግብዓት አቅርቦት እና በሕጎች ማሻሻያ የሚሰሩ ስራዎች ምንም ያክል አስፈላጊ እና ጠቃሚ ቢሆኑ ሙያዊ ብቃቱ አነስተኛ የሆነ እና/ወይም በሙስና እና ብልሹ አሰራር የተተበተበ የፍትህ ባለሙያ ባለበት ተቋም እና ሀገር ከፍትህ ዘርፉ አዎንታዊ ውጤትን መጠበቅ አይቻልም።

- ማንኛውም የማሻሻያ ፕሮግራም ሲዘጋጅ እና ተግባራዊ ሲደረግ ሚዛናዊነትን ታሳቢ ያደረገ ሊሆን ይገባል። ሚዛናዊነትን ከግምት ያስገባ ሊሆን ይገባል ሲባል ለምሳሌ በነጻነት እና በደህንነት መካከል፣ በክልል ወይም በዝቅተኛው የአስተዳደር መዋቅር እና በፌዴራል ወይም ማዕከላዊ መንግስት እና ፍላጎቶች ሁኔታዎች መካከል፣ በአጭር እና በረጅም ጊዜ ግቦች መካከል፣ በቴክኒክ እና ፖለቲካዊ

ሁኔታዎች መካከል የሚኖር ሚዛናዊነትን የማስጠበቅ ትኩረትን የሚመለከት ነው። ስለሆነም ለአንድ በፍትህ እና ሕግ ዘርፍ ላይ የሚደረግ የማሻሻያ ፕሮግራም እና ስራ ስኬት የሚመሰረተው ይህ ፕሮግራም እና ስራ በተለያየ ፍላጎቶች እና ሁኔታዎች መካከል የሚኖሩ ተቃርኖዎችን ሚዛን በማስጠበቅ አቅሙ ላይ መሆኑ ትምህርት ሊወሰድበት የሚገባ ጉዳይ ነው። በአንድ አቅጣጫ ያመዘነ የለውጥ ስራ ምንም ያህል ለውጥ እና ውጤትን ቢያመጣ በሚመጡት ለውጦች እና ውጤቶች ላይ በሚኖረው እምነት እና ቅቡልነት ላይ የራሱን አሉታዊ ተጽዕኖ መፍጠሩ አይቀርም። ምንም ያክል በአንድ በተወሰነ አቅጣጫ ስር-ነቀል ለውጥ የሚያመጡ እርምጃዎችን መውሰድ አስፈላጊ ሆኖ ቢገኝም እነኚህን እርምጃዎች ለመውሰድ በበቂ ሁኔታ ምክንያት ያለን ስለመሆኑ እና እነዚህ እርምጃዎች በመወሰዳቸው ምክንያት ሊመጣ የሚችል አደጋ ወይም የጎንዮሽ ጉዳትን ስለመቀነሳችን አስቀድመን ማረጋገጥ ይኖርብናል። እንዲህም ሆኖ ግን በተወዳዳሪ ፍልጎቶች እና ሁኔታዎች መካከል የሚወሰዱ የለውጥ እርምጃዎች በመርህ ደረጃ ሚዛናዊነትን ያስቀደሙ ሊሆኑ የሚገባ ስለመሆኑ ቅድሚያ መስጠት ይኖርብናል።

2.7 ለትራንስፎርሜሽን የፍትህ ዘርፉ የጋራ ፍኖተ ካርታ አስፈላጊነት

የፍትህ ዘርፉ በውስጡ የተለያየ ሀላፊነትና ተግባር ያላቸዉን የተለያዩ ተቋማትን ያቀፈ ነዉ። በዘርፉ ያሉ ተቋማት በህገ-መንግሥቱ እውቅና የተሰጠዉ ነጻነት እና ከጣልቃገብነት ነጻ በመሆን ፍትህ የማስፈን እንዲሁም ከፖለቲካ ተጽዕኖ ውጪ ሆኖ የየራሳቸዉን ተግባርና ሀላፊነት መወጣት የሚጠበቅባቸው ናቸዉ። የዘርፉ ትራንስፎርሜሽን ሲታሰብ በህገ-መንግሥቱ ዕውቅና የተሰጠዉ ነጻነትና ገለልተኝነት በተከበረበትና ባልተጣሰበት ሁኔታ መሆን እንደሚገባ ለሁሉም ግልጽ ነዉ። ይህም እንዳለ ሆኖ የዘርፉ ተቋማት አንደኛው ከሌላው ጋር የተሰናሰሉና የተገናኙ ሆነው የዘርፉ ውጤታማነት በአንደኛው ተቋም ወይም በተወሰኑ ተቋማት ብቻ ሳይሆን በሁሉም ተቋማት ውጤታማነት ላይ የተመሠረተ ነዉ። ይህ ከመሆኑ የተነሳ የዘርፉ ትራንስፎርሜሽን የተሳካ እንዲሆን የተቋማቱ የጋራ መግባባትና ቅንጅት እንዲሁም የጋራ የሆነ የማሻሻያ ፍኖተ-ካርታ መኖር አስፈላጊ መሆኑ ካለፉ ልምዶች ትምህርት የሚወሰድ ይሆናል።

2.8 ያለንበት ነባራዊ ሁኔታ፡ ተግዳሮቶች እና መልካም አጋጣሚዎች

በህብረተሰቡ ዘንድ በፍትህ ዘርፉ ላይ ያለው ከፍተኛ የእርካታ መጓደል፣ አቤቱታ እና ቅሬታ በቀጣይ የፍትህ ዘርፉን ለማሻሻል እና ለማጠናከር የሚደረጉ የማሻሻያ ስራዎች መሰራት እንደሚኖርባቸው ያለጥርጥር የሚያስገድድ ነው። በአሁኑ ወቅት የፍትህ ዘርፉ ያለበት ሁኔታ የእሮሮ ምንጭ የሆነ እና ፍጹም ተቀባይነት የሌለው ነው[12]። ስለሆነም ይህንን ሁኔታ ለመለወጥ ሰፊ የሆነ የማሻሻያ ስራ መስራት ያስፈልጋል። ይህንን ሁኔታ ለመቀየር የሚያስችል የማሻሻያ ስራን ስንነድፍ ደግሞ አስቀድሞ አሁን ያሉ ተግዳሮቶችን እና መልካም አጋጣሚዎችን ለይቶ ማስቀመጥ ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ነው።

[12] በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን ለሥነምግባር ጉድለት የሚያጋልጡ ሁኔታዎችን በተመለከተ የተደረገ ምርምር፣ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ቤት እና የኢፌዲሪ የፍትሕና የሕግ ምርምርና ሥልጠና ኢንስቲትዩት በጋራ የተዘጋጀ ጥናት፣ ባሕር ዳር፣ ነሐሴ 2014 ዓ.ም፣ ገጽ 155-59፣

በአሁኑ ወቅት ካሉ ተግዳሮቶች መካከል አንኳሩ እና በቅድሚያ ሊነሳ የሚገባው ጉዳይ በሀገሪቱ የሚታየው የደህንነት እጦት፣ ኢ-መደበኛ አደረጃጀቶች መፈጠር እና የግጭቶች መበራከት ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ አሁን በሀገሪቱ ያለው አጠቃላይ ፖለቲካዊ እና የጸጥታ ሁኔታ በፍትህ ዘርፉ ላይ ለሚደረግ የማሻሻያ ስራ አመቺ አይደለም። ከአጠቃላይ የፖለቲካ እና የጸጥታ ሁኔታ ጋር ተያይዞ የተፈጠረው የስጋት እና የተገማችነት አለመኖር ስሜት ለፍትህ ስርዓት ማሻሻያ የሚሰጠውን ትኩረት ከመበተኑ ባለፈ ተግባራዊ እንዳይሆን ትልቅ ጋሬጣን ይፈጥራል። ከዚህ በተጨማሪም ባለፈው አስር አመት ብቻ በርካታ የለውጥ ስራዎች በፍትህ ዘርፉ የተሞከሩ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በዘርፉ ውስጥ ባሉ ተቋማት እና ባለሙያዎች እንዲሁም በአጠቃላይ በህዝቡ ዘንድ የመሰላቸት እና "የለውጥ አይመጣም" ስሜትን ሊፈጥር ይችላል። ሌላዉ በዘርፉ የሪፎርም ሥራ ተግዳሮትና ሥጋት የሚሆነዉ በሁሉም የዘርፉ ተቋማት በሚባል ደረጃ ከፍተኛ ሆነ የበጀትና የሀብት ችግር መኖሩ ነዉ። አሁን ባለንበት የሐገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በርካታ ኢኮኖሚውን የሚገዳደሩ ፈተናዎች ያሉ ከመሆኑ ጋር ተደምሮ በዘርፉ የሚካሄደዉ የሪፎርም ሥራ ውጤታማ እንዲሆን አስፈላጊዉ ተጨማሪ የሆነ በጀትና ሀብት ካልተመደበ የሪፎርም ሥራዉ ፈተና ሊገጥመዉ ይችላል። ይህ ሁኔታ በመንግስት በኩል በቁርጠኝነት ትኩረት መስጠትን የግድ ይላል። በመሆኑም ምንም እንኳን ያለንበት ሀገራዊ የጸጥታና የደህንነት ሁኔታ በተሟላ ሁኔታ ላይ የሚገኝ ባይሆንም በፍትህ ዘርፉ ያለዉ ሁኔታ ከላይ እንደተገለጸዉ የህብረተሰቡ ሮሮ እና ተአማኒነት መጓደል የሚታይበት መሆኑ የበለጠ ሁኔታዉን እንዳያባብስ በዘርፉ ማሻሻያ አስፈላጊ መሆኑን በቁርጠኝነት በማመን ትራንስፎርም ማድረግ ጠቀሜታዉ የጎላ ይሆናል።

በሌላ በኩል በፍትህ ዘርፉ የሚደረጉ ተጨማሪ የማሻሻያ ስራዎች እንዲሰሩ በመንግስት በኩል ያለው የፖለቲካ ፍላጎት እና ቁርጠኝነት እንዲሁም በፍትህ ዘርፉ የለውጥ ስራዎች መሰራት እንዳለበት የሚያስገድዱ ተጨባጭ ሁኔታዎች መኖር እንደመልካም አጋጣሚ ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ። ምንም እንኳን ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በቀጣይ የሚደረግ የፍትህ ስርዓት ማሻሻያ ስራን ተከትሎ ሊኖር የሚችል መሰላቸት ቢኖርም በአሁኑ ወቅት የማሻሻያ ስራ መስራት አስፈላጊነት መኖሩ እና በመንግስት በኩል ያለው ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት ተግዳሮቱን እንድናልፈው የሚያደርግ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ቀደም ሲል በተሰሩ የማሻሻያ ስራዎች የተገኘው የተከማቸ እውቀት እና ልምድ አሁን ለሚደረግ የማሻሻያ ስራ ትልቅ መሰረት እና አቅም ይሆናል። በዚህም ካለፉ የማሻሻያ ስራዎች እና ጥረቶች የተገኙ ትምህርቶች አሁን ለሚደረግ የማሻሻያ ፕሮግራም ከንድፍ አንስቶ እስከ አፈጻጸም ድረስ ለሚኖር ስኬት በጎ አስተዋጽኦን ያበረክታሉ። ከዚህ በተጨማሪም በተለያዩ ጊዜያት በውስጥ አቅም እና በውጭ አጥኚዎች ጭምር የተሰሩ የፍትህ ስርዓቱን ውጤታማነት፣ ተአማኒነት እና የስነ ምግባር ደረጃ ለማሳየት የሚችሉ ጥናቶች መኖራቸው በቀጣይ በዘርፉ ማሻሻያን ለማምጣት እንደግብዓት ሊወሰዱ ይችላሉ።

ምዕራፍ ሶስት

በፍትህ ዘርፍ ተቋማት ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶች አጭር ዳሰሳ

በፍትህ ሥርዓቱ ላይ ያሉትን ሁኔታዎች፣ ችግሮችና የመፍትሄ ሀሳቦች ለማወቅ እንዲረዳ አምስት የጥናት ሰነዶች ላይ ዳሰሳ ተደርጓል። እነዚህም ጥናቶች የፌደራል ፍትሕ ዘርፍ ተቋማት መልካም አስተዳደር /አገልግሎት አሰጣጥ / ጥናት፣ ፍትሕ ሥርዓት ማሻሻያ ኘሮግራም በፌዴራል ተቋማት ያለበትን ደረጃ ለመለየት የተካሄደ ዳሰሳዊ ጥናት፣ በኢትዮጵያ የፍትህ ፍላጎት እና እርካታ ላይ የተደረገ ጥናት፣ በወንጀል ፍትሕ ሂደቶች መዘግየት ዋና ዋና ማነቆዎች እና ምክንያቶች ልየታ ጥናት እንዲሁም ቅጽበታዊ የፍትሕ ምልከታ በኢትዮጵያ (Justice snapshot In Ethiopia) ናቸው።

የመጀመሪያው ጥናት በፌደራል ፍትሕ ዘርፍ ተቋማት መልካም አስተዳደር /አገልግሎት አሰጣጥ / ላይ የተደረገው ጥናት ነው። በፌደራል የፍትሕና ሕግ ኢንስቲትዩት በአራት የፌደራል ፍትህ ዘርፍ ተቋማት ማለትም ፍርድ ቤቶች፣ ፍትህ ሚኒስቴር፣ ፖሊስ ኮሚሽን እና ማረሚያ ቤቶች ላይ መልካም አስተዳደር ወይም አገልግሎት አሰጣጥ ጋር ተያይዞ ያሉበትን ደረጃ ለማወቅ በ2015 ዓ.ም የተደረገ ጥናት ነው። ጥናቱ በዋናነት ዓላማ አድርጎ የተነሳው ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ በፍርድ ቤቶች እና በሌሎች ፍትህ ዘርፍ ተቋማት ያደረጉትን የሪፎርም ስራዎችና አፈጻጸማቸው፣ የተቋማቱ የአገልግሎት አሰጣጥ ከሕዝብ እርካታ አንጻር እና የተቋማቱ የውስጥ አስተዳደር ከሰራተኞች እርካታ አንጻር ያለበትን ደረጃ መለየት፣ ያጋጠሙ ችግሮችና መንስዔዎቻቸውን መለየት እና ለችግሮቹ የመፍትሄ ሐሳብ መስጠት ነው።

ሁለተኛው ጥናት ፍትሕ ሥርዓት ማሻሻያ ኘሮግራም በፌዴራል ተቋማት ያለበትን ደረጃ ለመለየት የፌዴራል የፍትሕና ሕግ ምርምር እና ስልጠና ኢንስቲትዩት መስከረም 2011 ዓ.ም ያደረገው ዳሰሳዊ ጥናት ነው። በፍትህ ዘርፉ የታዩትን ችግሮች ለመቅረፍ ይቻል ዘንድ በ1998 ዓ.ም በቀድሞው የአቅም ግንባታ ሚኒስቴር አስተባባሪነት የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም (Justice System Reform Program (JSRP)) ይፋ ተደርጎ የነበረና ፕሮግራሙ በሶስት ንዑሳን ፕሮግራሞች የተከፋፈለ ሲሆን እነርሱም የፍርድ ቤቶች ማሻሻያ፣ የሕግ አስከባሪ አካላት ማሻሻያ እና የሕግ ትምህርት ሥልጠናና የምርምር ማጠናከሪያ ንዑስ ፕሮግራም መሆናቸውን በጥናቱ ተገልጿል። በዋናነት ጥናቱ ያተኮረው ከ2003 ዓ.ም እስከ 2010 ዓ.ም የፍትሕ ስርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም በፌደራል ተቋማት (በፍርድ ቤቶች፣ በሕግ አስከባሪው አካላት እና በሕግ ትምህርት እና ስልጠና ተቋማት) በመገምገምና ተግዳሮቶችን በመለየት ለወደፊቱ የሀገሪቱን የፍትህ ሥርዓት ወደ ተሻለ ሁኔታ ሊቀይር የሚችል

ምክረ ሃሳብ ለማቅረብ እና በፍትህ ሥርዓቱ ተይዘው የነበሩትን የማሻሻያ ኘሮግራሞች አፈፃፀምን በመገምገምና ያሉበትን ደረጃ መለየት ላይ መሆኑን ከጥናቱ ዓላማ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ሶስተኛው ጥናት በወንጀል ፍትሕ ሂደቶች መዘግየት ዋና ዋና ማነቆዎች እና ምክንያቶች ለመለየት ዓብይ ኮሚቴ እና ዩኤንዲፒ በመተባበር አማካሪዎች በመመደብ የተደረገ ጥናት ነው፡፡ ጥናቱ ዓላማ አድርጎ ያስቀመጠው በወንጀል ፍትሕ አሰጣጥ በተለይም የወንጀል ጉዳዮች መዘግየት ዙሪያ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶችንና ክፍተቶችን በመፈተሸና በመለየት የተፋጠነ ፍትሕ ለመስጠት የሚያስችሉ የማሻሻያ ምክረ-ሃሳቦችን ማቅረብ ነው፡፡ ጥናቱ በዋናነት ያተኮረው በፌደራል ፍትህ አካላት (ፍርድ ቤቶችን፣ ዐቃቤ ህግን፣ ፖሊስንና የማረሚያ ቤቶች) ከ2009 ዓ.ም እስከ 2013 ዓ.ም ያሉትን ጊዜያት ነው፡፡

አራተኛው ጥናት በኢትዮጵያ የፍትህ ፍላጎት እና እርካታ ላይ እ.ኤ.አ በ2020 በሀገር አቀፍ ደረጃ HiiL በተሰኘ አለም አቀፍ ድርጅት በኔዘርላንድ መንግስት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ድጋፍ፣ በፌደራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ እና በፌደራል ፍትህ ፣ የህግ ምርምር እና ጥናት ኢንስትቲዩት ትብብር የተሰራ ነው፡፡ ጥናቱ የተደረገው ሀገሪቱ ውስጥ ባሉት ስድስት ክልሎች ውስጥ ነው፡፡ ዋና ዓላማውም በኢትዮጵያ ውስጥ የፍትህ ፍላጎት እና እርካታን ከተገልጋዮች እይታ አንጻር መዳሰስ፣ የፍትህ ማግኛ መንገዶችን መለየት እና የፍትህ ክፍተት ደረጃን ማሳየት ነው፡፡

አምስተኛው ጥናት ቅጽበታዊ የፍትሕ ምልከታ በኢትዮጵያ የሚል ሲሆን በኢትዮጵያ የፍትህ አገልግሎት በህጉ ላይ የተቀመጠውና እና በአተገባበሩ መካከል ያለውን ሁኔታ ለመለየት የተደረገ ጥናት ነው፡፡ ጥናቱም በፌደራል፣ በክልልና በሁለቱ የፌደራል ከተሞች ህጉና አተገባበሩ በምን ደረጃ ላይ እንዳለ ለማወቅ ከ2012 እስከ 2013 ዓ.ም የተደረገ ጥናት ነው፡፡ የዚህ ጥናት ዋነኛ አላማ አጠቃላይ የፍትህ ስርዓቱ አሰራር በስራ ላይ ካሉት ህጎች አንፃር ለመገምገምና ክፍተቶችን ለመለየት ታስቦ የተደረገ ጥናት ነው፡፡

3.1 የጥናቶቹ ዋና ዋና ግኝቶች

3.1.1 በአውንታዊ የተጠቀሱ ዋና ዋና ግኝቶች

ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ እንደ ሀገር የለውጥ ስራዎችን በሁሉም የመንግስት መስሪያ ቤቶች ለመተግበር ጥረት ተደርጓል፡፡ እነዚህን የለውጥ ስራዎች ተከትሎ የተለያዩ ህጎችን የማሻሻል፣ አሰራር ስርዓቶችን ማስተካከል፣ ለህዝብ ቅሬታ መነሻ የሆኑ ህጎች እና የአሰራር ስርዓቶች በተቋማቱ እንዲሻሻሉ መደረጋቸውን፤

በፍትህ ዘርፍ ተቋማት ውስጥ ነፃነትና ገለልተኛነትን፣ ሥነ-ምግባር፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት፣ የህግ የበላይነት፣ ቅልጥፍና፣ ውጤታማነት፣ የዜጎች ተሳትፎና ቅንጅታዊ አሰራር እና የለውጥ ስራን በተመለከተ ካለፉት ሶስት አመት

ወዲህ የታዩ የተለያዩ መሻሻሎች መኖራቸውን፤

ከፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም አንፃር በኢ- ፋይሊንግ በተደገፈ የክስና ውሳኔ ልውውጥ እና በቪዲዮ ኮንፍረንስ ክርክር ተገልጋዮችን ተደራሽ መሆን መቻሉ እንደ ስኬት የሚታይ መሆኑን አመላክቷል። ከህግ አስከባሪ አካላት ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም አንፃር እንደ ስኬት የተወሰዱት የመሠረታዊ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት መዘርጊያ ኘሮጀክት እና የበጎ አድራጐት ድርጅቶች፣ የሲቪክ ማህበራትና የግል የጥበቃ ድርጅቶችን የመከታተልና የመደገፍ ሥርዓት ምዝገባ ሥራዎች ተግባራዊ መሆናቸው ጥናቱ ያሳያል። በተጨማሪም የሕግ ትምህርትና ስልጠና ማሻሻያ ፕሮግራም ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እየተደረገ ያለው የሕግ ትምህርት የመውጫ ፈተና ወደ ፍትህ ሥርዓቱ ለሚቀላቀሉ ባለሙያዎች ስርዓቱ የሚፈልገውን ዝቅተኛ ክህሎት የሚፈትሽ ስርዓት መዘርጋቱ፤

የፍትህ ጉዞ አውንታዊ ውጤት የሚለካው በቤተሰብ መካከል ሰላም መፍጠሩን፣ መብቶችን ፍትሃዊ በሆነ መልኩ መተግበርን፣ ተበዳዩ አካል ይቅርታ መቀበሉን እና ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት ያለውን ምቹ ሁኔታ መኖሩን በማየት ይሆናል። በዚህ መመዘኛ በኢትዮጵያ ውስጥ በሶስተኛ ወገን መስማማት የሚሰጠው ፍትህ ከመደበኛ እና በሽማግሌዎች ከሚሰጠው የተሻለ አዎንታዊ ውጤት ያለው ስለመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ውስጥ ሰፊ የሆነ ፍትህ ማግኛ መንገዶች እንዳሉ፣ባህላዊ የፍትህ አሰጣጥ በገጠር ሽማግሌዎች የሚፈጸመው በብዛት ተግባራዊ የሚደረግመሆኑ፣ 43% የሚሆኑት ባላጉዳዮች ይሄንን መንገድ እንደሚመርጡ በማረጋገት ጥናቱ በመልካም ጎን ለይቷል። በተጨማሪም እነዚህ መንገዶች ማለትም በመደበኛው እና ኢ-መደበኞች ከሚሰጡት የፍትህ አገልግሎት በተሻለ ጥራት እና ብዛት የፍትህ አገልግሎት እንደሚሰጡ፤

ሽምግልና በማህበረሰቡ ውስጥ በስፋት የሚተገበር ሲሆን በማህበራዊ ፍርድ ቤቶችም ባለጉዳዮች ወደ መደበኛ ክርክሮች ከመግባታቸው በፊት በዚህ መንገድ ጉዳዮቻቸውን እንዲጨርሱ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ። የገጠር ሽማግሌዎች የመሬት ጉዳዮች እና የቤተሰብ ጉዳዮች ላይ በብዛት ጣልቃ በመግባት የህግ ጉዳዮችን ይፈታሉ። በመሬት ጉዳይ አፈታት ላይ በሽምግልና፣ በምክር እና ውክልና የሚፈቱት በፍርድ ከሚፈቱት የተሻለ የፍትህ ሂደት ጥራት እንዳላቸው፤

አብዛኞቹ ፍርድ ቤቶች በቂ ብርሀን፣ አደረጃጀት፣ ጥበቃ፣ የሕዝብ መፀዳጃ፣ በጊዜያዊነት ቢሆንም በፌደራል ፍ/ቤቶች አስተርጓሚ ያላቸው መሆኑ፣በ35 ዩኒቨርስቲዎችየሕግ ድጋፍ (legal Aid clinic) ክሊኒክ አገልገሎት የመስጠት ሂደቶች፣ከወጣት ጥፋተኞች ጋር ተያይዞ በአዲስ አበባ ደረጃ አንድ ማገገሚያ ጣቢያ እና አንድ ማቆያ ጣቢያ ያለ መሆኑን፤

በተጨማሪም የፎረንሲክ መሰረተ ልማት (Forensic Infrastructure) የፌደራል ፖሊስ ኮምሽን የDNA ቴክኖሎጂ ፤ፎርጀሪ አናሊስስ ማሽን (VC-8000) እና ቪድዮ መቅጃ በማዕከላዊ ምርመራ ቢሮ በማስገባት

የምርመራ ስራዎችን እያገዘ እንደሚገኝ ጥናቶቹ በመልካምነት ጠቁሟል።

3.1.2 በአሉታዊ የተጠቀሱ ዋና ዋና ግኝቶች

የሪፎርም ስራዎች በሚገባው መጠን እንዳይተገበሩ ካደረጉ ምክንያቶች ውስጥ ከግልፀኝነትና ተጠያቂነት፣ ከአገልግሎት ተደራሽነት፣ ከሰው ኃይል ጥራትና ቁጥር፣ ከሀገሪቱ የፖለቲካና ጸጥታ ሁኔታ እና በጀት በዋናነት የሚጠቀሱ ችግሮች መሆናቸውን በተጨማሪም በማሻሻያው ወቅት ከቀደመው አሰራር ልማድ ሙሉ ለሙሉ ለመላቀቅ አለመቻል የተጀመሩ የሪፎርም ስራዎች በበቂ ሁኔታ ተግባራዊ እንዳይደረጉ አንዱ ምክንያት መሆኑ፤

ከውስጥ እና ከውጭ ተገልጋዮች እርካታ አንጻር የደሞዝና የጥቅማጥቅም፣ የውስጥ አሰራር ለምሳሌ ዝውውር፣ ሹመት እና ሌሎች ተያያዥ ገዳዮች ጋር በተያያዘ ቅሬታ መኖሩን እና በተለይም ለውስጥ ተገልጋዮች የእርካታ ማነስ መንስዔዎች መሆናቸውን፤

የውጪ ተገልጋዮችን በተመለከተ የአገልግሎት ተደራሽነት፣ ቅልጥፍና፣ ውጤታማነት፣ ተጠያቂነት፣ የህግ የበላይነት፣ ተቋማዊ ነፃነት እና ቅንጅታዊ አሰራር ላይ የሚታዩ ችግሮች የህብረተሰቡን የእርካታ ደረጃ ዝቅ እንዲል ማድረጉን፤

ከአገልግሎት ተደራሽነት ጋር በተያያዘ ተቋማቱ ለተገልጋዮች (ለአካል ጉዳተኞች፣ ሴቶች፣ ሕጻናት እና አረጋውያንን ጨምሮ) በቂ ማረፊያ ቦታ፣ መጸዳጃ ቤት፣ አገልግሎት የሚሰጥበት ክፍሎች አንጻር ችግር መኖሩን፤

ለአካል ጉዳተኞች አመቺ የሆነ ቢሮ አለመኖሩ፣ መስማት የተሳናቸው ባለጉዳዮች ጉዳያቸውን በትክክል ማስረዳት የማይችሉ በመሆኑ ከሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች ጋር እኩል እየተስተናገዱ አይደለም። ተደራሽነትን ከማጎልበት አንፃር በቂ የሆነ በጀት ከመመደብ ጋር ተያይዞ ችግሮች መኖራቸውና በፍርድ ቤት የጠበቃ ውክልናን በተመለከተ የዚህ ጥቅም ተጠቃሚ የሚሆነው ገንዘብ ያለው ብቻ መሆኑ ደሀው የህብረተሰብ ክፍል በቂ የህግ ድጋፍ እያገኘ ባለመሆኑ ፍትህ እየተጓደለ መሆኑን፤

በፍትህ ተቋማቱ የሚወጡ ደንብና መመሪያዎች ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍል በእኩልነት አለመድረሳቸው፣ ተገልጋዮችን በክብርና እኩልነትን ባከበረ መልኩ አለማስተናገድ፣ ምልጃ ጉቦ እና የተለያዩ መደለያዎችን በመቀበል አገልግሎት መስጠት በተለይም ከማረሚያ ቤት እና እስረኛ አያያዝ ጋር ተያይዞ ከምግብ፣ በቂ መኖሪያና መጸዳጃ ቤት፣ አየር መውሰጃ ቦታ፣ የህክምና አገልግሎት፣ የመድሀኒት አቅርቦት፣ በቂ የንጽህና መጠበቂያ እጥረቶች

መኖራቸውን፤

ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ የፍትህ ዘርፍ ተቋማት መካከል ተናቦ መስራት የሚያስችል ሥርዓት መኖሩ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል በተለይም ከፍርድ ቤቶችና ዐቃብያነ ህግ ጋር አለመግባባት መኖሩን፤

ከመረጃዎች ትንተና መረዳት የሚቻለው ከሌሎች የመልካም አስተዳደር መርሆዎች በተለየ መልኩ የተቋማት ተግባብቶና ተቀናጅቶ አገልግሎት የመስጠት ሁኔታ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን ይህም የተቋማቱን ተደጋጋፊነትና የአንዱ ሚና ያለ አንዱ በሚገባ ማረጋገጥ የማይቻል መሆኑን ከግምት ስናስገባ የፍትህ ዘርፉን ውጤታማነትን በእጅጉ የሚጎዳ መሆኑን፤

ከቴክኖሎጂ አጠቃቀም እና አቅርቦት አንጻር የተወሰኑ መሻሻሎች ቢኖሩም አሁንም መሻሻል የሚገባውና ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራበት የሚገባ ጉዳይ መሆኑን፣ ሰነዶችን በቴክኖሎጂ ተደግፎ መያዝና ለተገልጋይ ተደራሽ ማድረግ ትኩረት ሊሰጣቸው ከሚገቡ ጉዳዮች ውስጥ አንዱ መሆኑን፤

አላግባብ የመበልጸግ ፍላጎት መኖር፣ ስልጣንን አላግባብ መገልገል፣ በራስ አስተያየት የመወሰን ስልጣንን አላግባብ መጠቀም፣ ሰራተኞች ተገልጋዮችን በቅንነት የማገልገል ሁኔታ (ጎቦ፣ ምልጃ ወይም ሌላ ጥቅም ሳይጠይቁ) ዝቅተኛ መሆን፣ የሙስና ችግር፣ በዝምድና መዝገቦች ላይ መስራት፣ ያለአግባብ መዝገብ መዝጋት፣ ያለአግባብ ክስ ማቅረብ፣ በአግባቡ መረጃ ባልተጠራባቸው ጉዳዮች ላይ ክስ መመስረትና ተጠርጣሪዎች ለረጅም ጊዜ በፈጀ ጉዳይ ክስ ማቋረጥ፣ ስራን በተጠያቂነት መንፈስ አለመስራት፤

ከፍትህ ሚኒስቴር አንጻር በተደጋጋሚ ከሚፈጠሩ የስነ-ምግባር ግድፈቶች መካከል በስራ ሰዓት አለመገኘት እና ያለፈቃድ ከስራ መቅረት ዋነኞቹ እንደሆኑ፣ በአብዛኛው የወንጀል ምርመራዎች ስታንዳርድ በተቀመጠው የሚከናወን ቢሆንም የአገር ሰላምና ጸጥታ ላይ ከፍተኛ አደጋ የጣሉ፤ ሕዝቡ በጉጉት የሚጠብቃቸው ጉዳዮች ለረጅም ጊዜ በተለዋጭ ቀጠሮ የሚጎተትበት በመጨረሻም እስከ ይቅርታ የሚደረስበት አሰራር ጎብረተሰቡን የሚያስቆጣ መሆኑን፤

ውጤታማነትን በተመለከተ ተቋሙ በመካከለኛ ደረጃ የሚገኝ መሆኑን፤ ዓቃብያነ ህጎች በበኩላቸው አመራሩ በአብዛኛው ዲሞክራሲያዊ አለመሆኑ፣ መዝገብ እንደፈለገ ማንሳቱ፣ ክስ ማቋረጡና ለሰራተኛ ክብር በአግባቡ

አለመስጠቱ ሰራተኛው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድር መሆኑን፤

በአብዛኛው ቅልጥፍና ላይ ተጽዕኖ ያሳደረው የባለሞያዎች የስራ ሰዓት አለማክበር ስራ በተገቢው ሰዓት እንዳይጀመር ማድረጉ አንዱ ተጠቃሽ ምክንያት ሲሆን የሕግ የበላይነትን አስመልክቶ የፍ/ቤቶች ሕግ እና ሥርዓትን ተከትሎ አገልግሎት የመስጠት ሁኔታ ደረጃ መካከኛ መሆኑን፣ ተጠያቂነትን ከማስፈር አንፃር ችግሮች መኖራቸውን በዚህም ተገልጋዮች እርካታ አሉታዊ መሆኑን፤

የተቋማቱ ግልጽኝነት፣ ገለልተኝነት እና የሙያ ነጻነት በተመለከተ ችግር ያለበት ስለመሆኑ፣ ለዚህም እንደ ምክንያት ከተነሱት ሀሳቦች መሃል በፍትህ ሚኒስትር በኩል ወንጀል ተፈጽሞ እየተጣሩ ነው የሚባሉ በርካታ ጉዳዮች ክስ ይመስረት አይመስረት ለህዝብ ይፋ ሳይደረጉ መቅረታቸው እና ሀገርን የረበሹ ሕዝብና ህዝብን ያጋደሉ ግለሰቦች በይቅርታ ሲለቀቁ ለህዝቡ በአግባቡ አለመገለጹ፣ ተቋሙ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን ለሰራተኞች ግልጽ በሆነ ሁኔታ የሚወስን አለመሆኑ፣

ዜጎች በተቋሙ አገልገሎት ላይ ሃሳብ እንዲሰጡ የሚያስችል ስርዓት ማዳበር መቻልን እና የሚሰጡ አስተያየቶችን ወስዶ ጥቅም ላይ የማዋል ሁኔታን አስመልክቶ የተሳትፎ መድረኮች መደበኛ አለመሆንና የተለያዩ የቴክኖሎጂ አማራጮችን የተጠቀመ አለመሆኑን መረዳት ይቻላል በዚህም የዜጎች ተሳትፎ በመካከለኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን፤

የሚዘጋጁ የትምህርትና ስልጠናዎች ከስራው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው እና የሙያ ብቃትን እና ሌሎች ተያያዥ ነገሮችን ለማሻሻል የሚረዱ አለመሆናቸው፤

አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎችን መጠቀምን በተመለከተ መካከለኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ በመሆኑ የስራ ጫናን በተለይም ከፍርድ ቤቶች አንፃር መቀነስ የሚያስችል በመሆኑ በዚህ ረገድ ችግሮች ሊስተካከሉ እንደሚገባ፤

ከፍርድቤቶች ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም አንፃር ፕሮጀክቶቹ በአብዛኛው ትኩረት ያደረጉት የፋይናንስ ድጎማዎችን በማድረግ ላይ መሆኑን፣ በዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ተገልጋዩ ሕብረተሰብ የሚያነሳቸውን የአገልግሎት

አሰጣጥ መልካም አስተዳደር ችግሮችን በሚፈለገው ደረጃ መፍታትም ሆነ የተገልጋዮችን ቅሬታ እንዲቀንስ ማድረግ አለመቻል፣ የዳኝነት ነጻነትና ገለልተኝነት ሥርዓት በሚፈለገው ደረጃ ተጠናክሮ አለመገኘት፣ የዳኞችን ተጠያቂነት ለማስፈን የሚረዳ ሥርዓት በሚፈለገው ደረጃ ተጠናክሮ አለመገኘት፣ የፍርድ ቤቶችን የአገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋና ተደራሽነት ማነስ፣ የፍትህ ማሻሻያ ፕሮግራም ሥራን የሚመራና የሚያስተባብር የስራ ክፍል ራሱን ችሎ እንዲደራጅ አለመደረጉ፣ አማራጭ የሙግት መፍቻ ስልቶችን ወጥ በሆነ መልኩ አለመጠቀም፣ በፍትህ ተቋማት ውጤታማ የሆነ ቅንጅታዊ አሰራር አለመኖር፤

ከሕግ አስከባሪ አካላት ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም አንፃር የሕግ ማርቀቅ ስራዎችን በሚመለከት የታቀደውን ያህል አለመሰራቱ፣ የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕጉን ለማሻሻል ረጅም ጊዜ መውሰዱ፣ በወንጀል ፍትሕ ስርዓቱ ላይ ያሉ ችግሮችን መፍታት አለመቻሉ፣ አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎችን በሚመለከት ወጥ የሆነ ሥርዓት አለመዘርጋቱ፣ የሚመሰረቱ ክሶች ጥራት መጓደል እና የዐቃቤ ሕጎች የክርክር ብቃትና ክህሎት ክፍተት መኖር፣ በፍትሐብሔር ጉዳዮች ወደ ክርክር ከመገባቱ በፊት ጉዳዩ በድርድር የሚያልቅበት ሥርዓት አለመኖሩ እና ፍርዶችን ማስፈጸም ላይ ክፍተት መኖር፣ በፖሊስና ዐቃቤ ሕግ መካከል መኖር ስላለበት ቅንጅታዊ አሰራር የሕግ ማዕቀፍ አለመኖር፣ የህብረተሰብ ንቃተ ሕግ የማሳደግ ስራ የየአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ በማገናዘብ በፍላጎት ዳሰሳ ላይ የተመሰረተ አለመሆኑ፣ የፌዴራልና የክልል አካላት በዋይድ ኤሪያ ኔትዎርክ አለመገናኘታቸው፣ በዘርፉ የኢንፎርሜሽንን ቴክኖሎጂ ባለሙያዎች እጥረት ያለ መሆኑ፣ የዐቃቤ ሕግ የመረጃ ሥርዓት (Prosecution Information system) ውጤታማነቱ ተረጋግጦ ወደ ክልሎች አለመውረዱ፤

ከሕግ ትምህርት፣ ስልጠናና ምርምር ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም አንጻር የትምህርት እና ስልጠናው ዘርፍ ከፍትህ ዘርፉ ጋር በቅንጅት የሚሰራበት ስርዓት አለመዘርጋት፣ በየወቅቱ የስርዓተ ትምህርት ክለሳ አለመደረጉ፣ የህግ ትምህርት ቤት መምህራን የፍትሕ ዘርፉ አሰራር ላይ ተግባራዊ ልምምድ የሚያደርጉበት ሁኔታ አለመኖር እና አዳዲስ መምህራን የማስተማር ስነ-ዘዴ ላይ ስልጠና አለመውሰዳቸው፣ የህግ ትምህርት ጥራት ማነስ እና የማስተማሪያ መፃህፍት ወቅቱን ያልጠበቁ መሆን፣ ከውጭ አገራት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የተገኙ የትምህርት እድሎችን በአግባቡ አለመጠቀም እና ተጨማሪ እድሎችን አለመፍጠር እና የፍትህ ተቋማት የተግባር ልምምድ ለሚወጡ ተማሪዎች አስፈላጊ የስራ ልምምድ እንዲያገኙ ለማድረግ አለመቻሉ፤

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ጥናቱ በዋናነት ያተኮረው ፍትህ ስርዓቱ ተይዘው የነበሩ የማሻሻያ ፕሮግራሞች አፈፃፀምን መገምገም ሲሆን በእያንዳንዱ ፕሮግራሞች ስር የተለያዩ ፕሮጀክቶች መያዛቸውን ጥናቱ ያሳያል። ለፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም 16 ፕሮጀክቶች፣ ለሕግ አስከባሪ አካላቱን አሰራር የማሻሻልና አቅም የማሣደግ ንዑስ ኘሮግራም 30 ፕሮጀክቶች እና ለሕግ ትምህርት፣ ስልጠናና ምርምር ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም 8 ፕሮጀክቶች ተይዘው እንደነበር፤

ለፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም ከተያዙት ፕሮጀክቶች ውስጥ ለረጅም ጊዜ የተጠራቀሙ ሰነዶችና መዝገቦች መጠበቂያና ማስወገጃ ፕሮጀክት፣ የዳኝነት ምዘና ሥርዓት መዘርጊያ ፕሮጀክት እና የከተማ ነክ ፍ/ቤቶች፣ ሸሪያ ፍ/ቤት፣ ወታደራዊና አስተዳደራዊ ፍትህ የሚሰጡ አካላት ማጠናከሪያ ኘሮጀክት፤ ከሕግ አስከባሪ አካላቱን አሰራር የማሻሻልና አቅም የማሣደግ ንዑስ ኘሮግራም ከተያዙት ፕሮጀክቶች አማራጭ የሙግት መፍቻና ግጭት ማስወገጃ ሥርዓት ማስፈጸሚያ ኘሮጀክት፣ ነጻ የሕግ ምክር አገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ኘሮጀክት፣ ለረጅም ጊዜ የተጠራቀሙ ሰነዶችና መዝገቦችን ማስወገጃ ፕሮጀክት፣ የምስክሮችና ወንጀል ተጐጂዎች ሥርዓት መመስረቻና ማጠናከሪያ ኘሮጀክት፣ ህብረተሰቡ የፍትህ አካላትን የሚመዝንበት አሰራር መዘርጊያ ፕሮጀክት፣ የሕግ ሙያተኞች ማህበራትን ማጠናከሪያ ፕሮጀክት እና የፍትህ ተቋማት የተቀናጀ የመረጃ ማዕከል ማቋቋሚያ ፕሮጀክት፤ ከሕግ ትምህርትና ስልጠና ማሻሻያ ፕሮግራም የትምህርትና ስልጠና ተቋማት ውጤታማነት የሚመዘንበት አሰራር መዘርጊያ ፕሮጀክት እና የሕንፃና ሌሎች ፋሲሊቲዎች ማሟያ ፕሮጀክት ያልተከናወኑ ፕሮጀክቶች መሆናቸውን፤

በኢትዮጵያ ውስጥ በሂደት ላይ ካሉትና ካልተፈቱት የህግ ጉዳዮች አብዛኞቹ ከባድ ጉዳዮች መሆናቸውን፣ የተፈቱት የህግ ጉዳዮችም ቢሆኑም አብዛኞቹ ፍትሃዊ በሆነ መልኩ እንዳልሆነ፣ ይሄም የፍትህ ክፍተትን በማስፋት የፍትህ መጓደል ማብዛቱን፤

በሽምግልና የሚፈቱ ጉዳዮች እንደ መደበኛ የፍትህ አሰጣጥ ገዢነት ስለሌላቸው ውሳኔያቸው ላይከበር ከመቻሉም ባሻገር ወደ ሽምግልና ጉዳያቸውን የሚወስዱ ሰዎች ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰቡ ክፍሎች፣ ትምህርት የሌላቸው፣ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ እና በገጠሩ የሀገሪቱ ክፍል ውስጥ ያሉ መሆናቸው፣ ከሌሎች ሀገራት ጋር ሲነጻጸር በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት የህግ ጉዳዮች በብዛት (17%) የሚሆኑት ወደ መደበኛ ፍርድቤቶች/ የማህበራዊ ፍርድ ቤቶችን ጨምሮ/ የምቀርብ መሆኑን፤

በመደበኛ ፍርቤቶች እና ማህበራዊ ፍርድቤቶች በሚደረጉ የህገ ጉዳዮች ላይ የህግ ባለሙያዎች ተሳትፎ ጥቂት ማለትም /1%/ ብቻ መሆኑን፣ ከማህበረሰቡ 68% የሚሆኑት መረጃ እና የህግ ምክርን የሚፈልጉ ቢሆንም አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል የህግ ጉዳዮች ሲያጋጥማቸው ወደ ቤተሰቦቻው፣ ጓደኞቻቸው እና ወደ ጎረቤቶቻቸው ለምክር የሚሄዱ መሆኑን፤

ምንም እንኳን ጊዜውን የጠበቀ መረጃ እና የህግ ምክር ለፍትህ አቅርቦት ወሳኙ ነገር ቢሆንም በሰለጠኑት የህግ ባለሙያዎች የሚሰጠው አገልግሎት የፍትህ መጓደልን ለመቀነስ ያለመ እንዳልሆነ፣ በገጠር አከባቢ የሚኖሩት እና ትምህርት ያላገኙ ሰዎች የህግ ጉዳዮቻቸው ላይ የሚወስዱትን እርምጃ እንደማያውቁ፣የኢትዮጵያ ህዝብ የህግ ጉዳዮቻቸው ላይ 2/3 የሚሆኑት የህግ ምክርን የሚሹ መሆኑን፣ የመንግስት ተቋማት የህግ ምክርን እና መረጃ መስጠት ላይ ብዙም የማይታዩ መሆኑን፤

የህግ ችግሮች የተለያዩ አሉታዊ ተጽዕኖ በማህበረሰቡ ላይ ያመጣሉ፤ገንዘብና ጊዜን መጨረስ፣ በጭንቀት ለሚመጣ ህመም መዳረግ፣ የቤተሰብ ግንኙነትን ማሻከር እና የመሳሰሉት እንደሆኑና ተጋለጭ የማህበረሰቡ ክፍሎች/ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው/ በህግ ችግሮች የሚመጣበቸው አሉታዊ ውጤት ከሌሎች የሚያንስ ቢሆንም በማህበረሰቡ ወይም በቤተሰቦቻቸው ላይ መልካም ግንኙነት እንዳይኖራቸው ማድረጉን፣ ከአጠቃላይ 7.4 ሚሊዮን የህግ ችግሮች 2.2 ሚሊዮን ብቻ ፍትሃዊ መፍትኤ ያገኙ መሆናቸውን፣ የተቀሩት ወይ መፍትሄ ያላገኙ ወይም ደግሞ ፍትሃዊ መፍትሄ ማግኘቱን ማህበረሰቡ ያላመነበት መሆኑን፣ ከባድ የህግ ጉዳዮች አብዛኛውን ጊዜ በሂደት ላይ የሚዘገዩ ወይም የሚንጠባጠቡ መሆናቸውን፤

ወደ ከተሞች የሚደረግ ፍልሰት፣ የትምህርት ደረጃ፣ የማንነት መታወቂያን የማግኘት፣ ከፖሊስ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች፣ መሰረታዊ ልማቶችን ያለማግኘት፣ እና የከተሞች መስፋፋት የፍትህ ፍላጎትን ካሁኑ በላይ መጨመሩ አይቀሬ መሆኑን፣ ይህ ደግሞ የፍትህ ክፍተት ደረጃን ከፍ ማድረጉ ስለማይቀር ያሁኑ እና የወደፊት ስትራቴጂዎች፣ ፖሊሲዎች እና አገልግሎቶች ይሄን ከግምት ያስገቡ መሆን እንዳለባቸው፤

የፖለቲካ አለመረጋጋት እና የፀጥታ ሁኔታ በፈጠሩት ተግዳሮቶች ምክንያት መደበኛ የህግ ማስከበር ስራ መስራት ያለመቻል፤ ተደጋጋሚ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጆች በስራ ላይ እንዲውሉ መደረጉ፣ መደበኛዉ የወንጀል ፍትሕ በወቅታዊ ጉዳዮች አቅሙ እንዲበተን በማድረግ ውዝፍ መዝገቦች መጨመራቸው፣ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ደግሞ የችግሮች ስፋት በህብረተሰቡ ውስጥ የነበረውን ለወንጀል ፍትሕ ስርዓቱ መሰረታዊውን የህግ ተገዥነት ስነ-ልቦና እስከማጥፋት እና በደቦ እና በአደባባይ ፍርዶች የመስጠት ልምምድ ውስጥ ያስገባ ክስተት መሆኑ፣ የመንግስት አካላት የስልጣን ክፍፍል እና ቁጥጥር ስርዓት ደካማ መሆኑ፤

የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ሥርዓቱ የሚመራባቸዉ የፖሊሲ እና የህግ ማዕቀፎች በሚገባው ልክ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ፍትሕን ለመስጠት በሚያስችል ሁኔታ የማይገኝ መሆኑ፣ በምርመራ ሂደት በወንጀል የተጠረጠረውን ሰው ሊጠቅም የሚችል የምርመራ ስልት (defense investigation) በህጋችን ውስጥ አለመካተት፣ አንድ በፍርድ ቤት በመታየት ላይ ያለ የወንጀል ጉዳይ የጊዜ ድንጋጌዎች ወይም ማቀፎች አለመኖሩ፣ ግልፅነት የጎደላቸውና ለአፈፃፀም አስቸጋሪ የሆኑ የህግ ድንጋጌዎች፣ የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕጉ አንዳንድ ድንጋጌዎች የግልጽነት ችግር በወንጀል ምርመራ ሂደት የሚያልፍ ክስ ለመሆን ማስረጃ የተሟላባቸዉ ጉዳዮች ሁሉ የመጨረሻ እልባት የግድ ከፍርድ ቤት ብቻ እንዲጠብቁ መሆናቸው፣ የጥፋተኝነት ድርድር (plea bargaining) የሚመራበት ህግ ያለመኖሩ፣

በፍትሕ አካላት ከክልሎች ጋር እና በፌዴራል መካከል እንዲሁም በፌደራል የፍትህ ዘርፍ ተቋማት መካከል ጠንካራ ቅንጅትና ትብብር አለመኖሩ እንዲሁም ግልጽ ፖሊሲ፣ ህግ፣ አሰራር እና አደረጃጀት ያለመኖሩ፣

ከምስክሮች አቀራረብ ጋር በተያያዘ የፍርድ ቤት መጥሪያ አወጣጥ እና አደራረስ ተገቢው ሥርዓት ያልተበጀለት መሆኑ ከዚህ ጋር ተያይዞ ፍርድ ቤት ለዐቃቤ ህግ፤ ዐቃቤ ህግ ለፖሊስ፤ ፖሊስ ደግሞ ለምስክሮች ከዚህ

በተጨማሪም ምስክሮችን በተገቢው ጊዜ ሊያቀርብ የሚችል ወይም ለዚህ የሚመች አደረጃጀት አለመኖር ሌላው ለወንጀል ፍትህ መጓተት መንስኤ መሆኑን፤

የሰው ሀብት አቅም ክፍተቶች (የዕውቀት፣ የክህሎት፣ የልምድ)፣ የበጀት እና ሎጂስትክስ ችግሮች፣ የቴክኖሎጂ አቅም ውስንነት፣ የህግ አፈጻጸም ችግሮች፣ የሙስናና የሥነ ምግባር ችግሮች እና የጉዳዮች ውስብስብነትና የተከሳሾችና ምስክሮች መብዛት የወንጀል ጉዳዮች መዘግየት ምክንያት መሆኑን፣

በጊዜ ቀጠሮ ሂደት እና ከቀዳሚ ምርመራ መዘግየት ጋር ተያይዞ የሚነሱ ዋና ዋና ምክንያቶች ለአንድ የፍትህ ተቋም ብቻ የሚሰጥ ሳይሆን ከሁሉም ተቋማት ጋር ማለትም ፍርድ ቤቶች፣ ፖሊስ፣ ዓቃቤ ህግ፣ ከማረሚያ ቤት፣ ከተከላካይ ጠበቆች ጸ/ቤት፣ ከጠበቆች፣ ከተከሳሾች፣ ከግል ተበዳዮችና ከሌሎች ተቋማት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ችግሮች መሆናቸውን፤

የውጪ አካል ጣልቃ ገብነት (External interference)፣ የፖሊቲካ ጣልቃ ገብነት፣ በመንግስት ባለስልጣን የሚመጣ ግፊት፣ ፍትህን ፖለቲሳይዝ ማድረግ፣ የፍትህ አካል ፈፃሚዎች (practitioner) የሙያ ብቃት(ፐሮፌሽናሊዝም) ማነስ፣ ስነ-ምግባር ችግሮች፣ ጥራት ያለው አገልግሎት አለመስጠት፣ ሰራተኞች ተገቢው ስልጠና የሌላቸው መሆኑ እና ህጉን ያለ አግባብ መተርጎም፤

አስፈላጊ የስራ መሳሪዎች (IT and Communication) ኢንተርኔት፣ የምስክር ቃል መቅረጫ ፣ የትራንስፖርት፣ የደህንነት፣ ምቹ የስራ ቦታ፣ የስራ ጫና፣ የመኪና እጥረት፣ በሀገሪቱ ያለው አለመረጋጋት፣ ደካማ የህግ የበላይነት፣ ፍትህ ከፍርድ ቤቶች መጥፋት፣ በህግ ፊት እኩልነት አለመኖር፣ የፍርድ ጉዳዮች መዘግየት፣ የዘገየ ፍርድ፣ የዳኝነት ብቃት ማነስ፣ የተጠራቀመ ጉዳዮች መብዛት፤

ነፃ የሕግ ድጋፍ (legal Aid) ለመስጠት በግልፅ የተመደበ በጀት እንደሌለ፣ በመሆኑ በዩኒቨርስቲዎች የሚሰጠው legal Aid Clinic እና በጋምቤላ ክልል የሚከናወነው የተንቀሳቃሽ ችሎት በበጀት እጥረት ምክንያት አገልግሎቱ እየቀነሰ እንደሚገኝ፣

የ2019 የኢትዮጵያ የስደተኞች አዋጅ ከዜጎች እኩል የፍትህ ተደራሽነት ያገኘሉ ቢልም የፌደራል ፍርድ ቤት አዋጅ የውጭ ዜጎች ፍርድ ቤት ጉዳይ የሚታየው በከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው ስለሚል አንዳንድ ክልል ወረዳ ፍ/ቤቶች እና የዞን ፍ/ቤቶች የስደተኞችን ጉዳይ አለመቀበል፣ በዚህ ምክንያት ስደተኞች ከካምፓቸው በመራቅ ወደ የክልል ከተሞች ለመሄድ ከመገደዳቸውም ባሻገር የስደተኞች ካምፓች ከመሃል ወጣ ያሉ ጠረፍ አካባቢ በመሆናቸው የመንቀሳቀስ መብት፣ የቋንቋ ችግር፣ ምስክር ማጣት እና የሕግ ድጋፍ (legal Aid) የሌላቸው መሆኑ፤

የሰው ሀይልን በተመለከተ የተጠናከረ መረጃ ባይኖርም ያሉት የፌደራል ፖሊስ ኮምሽን የሰው ሀይል በደንብ ያልሰለጠነ እና በቂ ያልሆነ፣ በተለይም የፖሊስ ምርመራ ክፍልና እና ፎረንሲክ ስራ ላይ ብቁ እና ፕሮፌሽናል ባለሙያ

እጥረት እንዳለ፤

በፖለስ ተቋም ውስጥ ለወንጀል ተጠቂም ሆነ ምስክር ለደህንነታቸው አስተማማኝ አለመኖር፣ ለህፃን ምስክሮችና ለወጣት ጥፋተኞች የተለየ ክፍል የሌለ መሆኑን እና ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ አለመሆኑን፣ የፌደራል ፖሊስ ተቋም የቢሮ፣ የቢሮ እቃ ፣የጤና ተቋም፣ የተሸከርካሪ እጥረት እንዳለበት፤

ተጠቂ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች የተለያዩ ተግዳሮቶች እንደሚያጋጥማቸው፣ እነዚህም የተግባቦት /ምልክት ቋንቋ ፤የአካል ጉዳተኞች አመቺ ሆነ መውጫ እና መውረጃ አለመኖር፤ፖሊሶች በየአካል ጉዳተኞች መብት ዙርያ ስልጠናና ግንዛቤ አለመኖር፤ ተጠቂ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች የደረሰባቸውን ጥቃት ሪፖረት ለማድረግ ወደ ፖሊስ ሲመጡ የተዛባ አመለካከት(Biased) መያዝ እንዲሁም የተጠቂ ማህበረሰብ ክፍሎችን ኬዝ አያያዝ ዙርያ እውቀትና ክህሎት አለመኖር ፤ የሳኮሎጂስት እና ማህበራዊ ሰራተኛ እርዳታ እንዲገኙ አለማድረግ ችግር መኖሩን፤

ቴክኖሎጂና የቴክኖሎጂ መሳሪያዎች ለምሳሌ ሲሲ ቲቪ፣ በሰውነት ላይ የሚተከሉ ካሜራዎች፣ አርተፊሻል ኢንተለጀንስ እና ባዮሜትሪክስ እጥረት ያለ በመሆኑ የወንጀል መከላከልና የወንጀል ኢንተለጀንስ ስራን በተገቢው ለመወጣት ተግዳሮት ሲሆኑ ይህ ችግር ደግሞ በክልሎች የበለጠ ጎልቶ እንደሚታይ መሆኑን፤

የፌደራሉ ፎረንሲክ ላብራቶሪ ለመላ ሀገሪቱ ብቸኛ ሲሆን ዘመናዊ የጣት አሻራ ትንተና እና ማጠራቀሚያ ዲጂታል ቴክኖሎጂ የለውም እንዲሁም በቂ በጀትና የሰለጠነ የሰው ሃይል እጥረት መኖሩን እና ማዕከላዊ ምርመራ ቢሮ ዲንኤ ላብ ኪት እጥረት መኖሩን ከላይ የተጠቀሱት ጥናቶች ያሳያሉ።።

3.2 የመፍትሄ ሀሳቦች

ከላይ በጥናቶቹ ለተጠቀሱት ዋና ዋና አሉታዊ ግኝቶች ተከታዮቹ የመፍትሄ ሀሳቦችን ጥናቶቹ አስቀምጠዋል።።

- በተቋማቱ በሪፎርም የታቀዱ እና የተጀመሩ የሪፎርም ስራዎችን ከአገሪቱ የለውጥ እቅድ አንጻር መፈተሸና መስማማታቸውን ማረጋገጥ፣ መገምገም፣ ማስተካከልና በተገቢው መልኩ መጨረስና ወደ ስራ እንዲገቡ ማስቻል፤
- የተጠያቂነት ስርዓትን ለማጎልበት የሚያስችሉ አስተማሪ እርምጃዎችን መውሰድ (አመራሩንም ይጨምራል)፣ ተከታታይነት ያለው ስነ-ምግባር የማነፅና የማጎልበት ስራ ላይ ማተኮር፣ የአመራሩ ቁርጠኝነት፣ ጠንካራ የተጠያቂነት ስርዓት መዘርጋት፣ ብልሹ አሰራሮችን ሊያርም የሚችል የግልጸኝነት እና የተጠያቂነት አሰራር ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ፣ የቁጥጥር፣ ክትትል እና ግምገማ ስርዓት ማጠናከር፣ የአሰራር ስርዓትን ማሻሻል፤
- አርአያ ለሆኑ ሰራተኞች እውቅና የሚሰጥበት አሰራር ስርዓት መዘርጋት፣ ደሞዝና ጥቅማጥቅም ጊዜውን

በሚመጥን መልኩ ማስተካከል፤

- ከአመራር ጋር በተያያዘ ተቋሙን የሚያውቁ ባለሞያዎችን መመደብና ቶሎ ቶሎ አለመቀያየር። በቅጥር ወቅት የተሻሉ ሰራተኞችን ለማግኘት የቅጥር መስፈርቱን ከፍ ማድረግ፣ ከአድሎ በጸዳ መልኩ በትክክለኛው ቦታ ትክክለኛ የሆኑ ሰራተኞችን በመመደብ ስራዎችን በትክክለኛው መንገድ እንዲሰሩ ማድረግ፤
- የፍትህ ዘርፍ ተቋማት በክልሎች ላይ ያላቸውን ተደራሽነት በጥናት ላይ ተመስርቶ ማረጋገጥ ከዚህ ጋር ተያይዞ ከአካል ጉዳተኞችና አቅመ ደካሞች አንፃር የፍትህ ተቋማትን ምቹ ማድረግ፤
- ዳኞች ጉዳዮችን በገለልተኝነት ማስተናገድ እንዲችሉ ቀጣይነት ያለው የስልጠና ስራዎች ማከናወን፣ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም የችሎት ስራ ክትትል፣ የመዝገብ ስራ ኦዲት፣ ዘመናዊ የፋይል አያያዝና የቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት፤
- የፌደራል የፍትህ ዘርፍ ተቋማት ግልፅነት ለማረጋገጥ የተቋማቱን አሰራር የሚመለከቱ ሕጎች፣ ውሳኔዎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች እና ተያያዥ መረጃዎችን ተገልጋዮች በቀላሉ እንዲያገኙ ማስቻል፣ አገልግሎት ለማግኘት ተገልጋዮች አሟልተው መቅረብ የሚገባቸውን ሰነዶችና ተያያዥ መረጃዎችን አስቀድሞ እንዲያውቁ ማድረግ፣ ጉዳዮችን በግልጽ ችሎት ማስቻል፤
- ሥነ-ምግባርና ዲሲፕሊን፣ ቅንጅታዊ አሰራር (ራሱን የቻለ ህግና ደንብ ወጥቶለት ወጥነት ባለው መልኩ ቢተገበር)፣ የዜጎች ተሳትፎ፣ ተጠያቂነት እና ቅልጥፍና፣ እንዲሁም በፍርድ ቤት የሚሰጡ ውሳኔዎች ተፈፃሚነታቸውን ማረጋገጥ፤
- የተቋማቱን የሞያ ነጻነት ማክበር፣ ከኃላፊዎች፣ ከመንግስት አካላት፣ ከህዝብ፣ ከሚዲያ እና ከራስ ፍላጎትና ተጽዕኖ ነጻ ሆኖ የመወሰን ሁኔታን እና ሌሎች የማሻሻያ እርምጃዎችን በየደረጃው መውሰድ፤
- የውስጥ እና የውጭ ተገልጋዮች ቅሬታን በተመለከተ የቅሬታ አፈታት ሥርዓቱን ማሻሻል፣ የቅሬታ መቀበያ ክፍሎችን ማጠናከር፣ ተደራሽ ማድረግና በተደጋጋሚ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን እየለዩ በዘላቂነት መፍትሄ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤
- በፍትህ ዘርፍ ስር ያሉት ተቋማትን ቅንጅታዊ አሰራር ለማጎልበት የሚረዱ የውይይት መድረኮች፣ የአሰራር ስርዓቶችን እና በትብብር የመስራት ባህልን ማጎልበት፤
- ስታንዳርድ ላልወጣላቸው የተለያዩ ስራዎች ስታንዳርድ በማውጣት ስራዎችን መስራት፤
- ሙስናን እና ብልሹ አሰራርን ለመቀነስ ብሎም ለማስወገድ የችግሩ ባለቤት የሆኑትን በመለየት የተጠናከረና ህጋዊ እርምጃዎችን መውሰድ፣ ጠንካራና ግልፅነትን የተላበሰ አሰራር ሥርዓት መዘርጋት፣ ለዳኞች አስተዳደር

ጉባዔ (ወይም በሌሎች የፍትህ ዘርፍ ተቋማት የሚገኙ የዲሲፕሊን ኮሚቴ) የቀረቡ የሥነ-ምግባር ጉዳዮችን በአጭር ጊዜ ውስጥ አጣርቶ ውሳኔ መስጠትና ለህዝብ ይፋ ማድረግ፤

- የተቋም አመራሮች እርስ በእርስ ተቀናጅተው መስራትና ለአንድ አላማ እንደሚሰሩ ማስገንዘብ፣ የውስጥ መልካም አስዳደርን ችግሮችን ለመቅረፉ የሰው ሀይል፣ በጀት፣ መሰረተ ልማት እና ሌሎች የግብዓት እጥረቶችን ያለውን ሀብት ተገቢ በሆነ አሰራር ሥርዓትን በመዘርጋት በፍትሀዊነት መጠቀም፤

- አሠራሮችን የሚያሻሽሉ ጥናቶችን በማሰባሰብ ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን ቀምሮ በማስፋፋት ወደ ተግባር መግባት፤

- የዳኞች አስተዳደር ጉባኤን እና የፍርድ ምርመራ ስራ አደረጃጀትን ፈትሾ ጠንካራ የዳኝነት ነጻነትና ገለልተኝነት እንዲሁም ተጠያቂነት ሥርዓት መዘርጋት፤

- የለውጥና የምዘና መሳሪያዎችን (መሠረታዊ የሥራ ሒደት ለውጥ፣ ሚዛናዊ የውጤት ተኮር ምዘና ሥርዓት) ከዳኝነት ሥራዎች ጋር አጣጥሞ መጠቀም፤

- ለሁሉም የወንጀል ጉዳዮች የቅጣት አወሳሰን መመሪያ በተመሳሳይ ጊዜ በማዘጋጀት ወጥና ተገማች የሆነ የቅጣት አወሳሰን ሥርዓት መዘርጋት፤

- አማራጭ የሙግት መፍቻ ስልቶችን ወጥ በሆነ መልኩ ለመተግበር የስራ መመሪያ በማዘጋጀት ወደ ስራ መግባት፤ መደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ የፍትህ ማግኛ መንገዶችን በመስተሳሰር በማህበረሰብ ደረጃ ፍትህ የማግኘት እድልን በማስፋት መደበኛ የፍትህ አገልግሎት አሰጣጥ አቅርቦት አማራጭ በሚሆንበት ጊዜ በቀላሉ እንዲያገኙ ማድረግ፤

- የፍትሕ ዘርፉን ውጤታማነት ለማጎልበት እና ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት የፍትህና የሕግ ነክ መረጃ ማዕከል ማቋቋም፤

- የንቃተ ሕግና ነጻ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት የሚሰጥበትን ሥርዓት ወጥነትና ተጠያቂነት ባለው መልኩ መምራት፣ ጠበቆችና የሕግ ትምህርት ቤቶች በፌዴራልና በክልል ነጻ የሕግ ድጋፍ መስጠት የሚችሉበትን ቅንጅታዊ አሰራር መፍጠር፤

- የትምህርትና ስልጠናው ዘርፍ ከፍትህ ዘርፉ ጋር በቅንጅት መስራት የሚችልበት ሥርዓት መዘርጋት፣ በየወቅቱ የሥርዓተ ትምህርት ክለሳ ማድረግ፤

- የፍትሕ ዘርፉን አቅም ለማጎልበት የሚያስችሉ የትምህርት እድሎችን ፕሮጀክት በመቅረጽ ማፈላለግ፤

- የህዝቡ የፍትህ ፍላጎት እና ልምዶች ላይ ዳታዎች መሰብሰብን፣ መተንተንና እና በተሰበሰቡ መረጃዎች መሰረት እርምጃ መውሰድን ማስቀጠል፤
- ከባድ የህግ ጉዳዮች፣ ብዙ ግብዓትና ትኩረት የሚሹትን ለመለየት የሚያስችሉ ስልቶችን ማዳበር፤ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎችን (ህጻናት፣ ሴቶች፣ ትምህርት ያላገኙና አቅመ-ደካሞች፣ ስደተኞች እና ከሀገር ውስጥ የተፈናቀሉ) ከግምት ውስጥ ማስገባት፤
- ተከታታይነት ያላቸውን ጥናቶች በማድረግ ከሁለቱም የመደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑት የፍትህ አገልግሎት አሰጣጥ የተሻለ ውጤት የሚያስገኙ ልምዶችን መለየትና ማስፋት፤
- የፖሊሲና ህግ ማሻሻያዎች ማድረግ፣ አግባብነት ያላቸውን አደረጃጀትና አሰራር ስርዓት መዘረጋት/ማጠናከር፣ የተቋማቱን የበጀትና የሎጅስቲክ አቅም ማሳደግ እና ምቹ ሥራ ቦታን ማመቻቸት እና የህብረተሰቡን ተሳትፎ መጨመር ፤
- ጠበቆች ነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎት የሚሰጡበትን ሁኔታ አጠናክሮ ማስቀጠል፤
- ፍትህ አካላት በተለይ ዳኖችና ዐቃቤያነ ህጎች ያለባቸውን የደህንነት ስጋት ለመቀነስ ሲሲቲቪ ካሜራና የተሸከርካሪ አቅርቦት እንዲኖራቸው ማድረግ የሚሉ ናቸው::

ምዕራፍ አራት

የፍትህ ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን፤ ለፍትህ ዘርፍ ማሻሻያ አዲስ አቅጣጫ

4.1 ትንስፎርሜሽን ወይስ ማሻሻያ፤ ከቃላት ጨዋታ በላይ

ማሻሻል ማለት የተወሰኑ ለውጦችን በአንድ ተቋም ወይም ስርዓት በማስተዋወቅ የተወሰነ መሻሻልን ማምጣትን የሚመለከት ሲሆን ትራንሰፎርሜሽን ግን የታወቀ እና መሰረታዊ ለውጥን በአንድ ተቋም ወይም ስርዓት ማምጣትን የሚመለከት ነው። ምንም እንኳን ሁለቱም ቃላቶች ለውጥን የሚመለከቱ ቢሆንም በሚያመጡት የለውጥ ጥልቀት እና ስፋት መጠን ግን ልዩነት አላቸው። በትራንስፎርሜሽን ውስጥ ያለው ለውጥ በጣም መሰረታዊ እና ተጨባጭ የይዘት ወይም የተፈጥሮ ለውጥን እስከማስከተል የሚደርስ ሲሆን በማሻሻያ ውስጥ ያለው ለውጥ ግን በአንድ ነገር ላይ መጠነኛ የሆነ ጭማሪን ማምጣት ይበቃዋል። ሲጠቃለል በማያቋርጠው ተፈጥሯዊ የለውጥ ሂደት ውስጥ ትራንስፎረሜሽን ከማሻሻል የበለጠ ጥልቅ እና ስር ነቀል ለውጥን የማምጣት ሂደትን የሚመለከት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

በዚህ አግባብ የኢትዮጵያ የፍትህ ዘርፍን አሁናዊ ሁኔታን ስንመለከት በተለይም ከላይ ባለው ምዕራፍ ያየናቸው ጥናቶች የለዩትን ችግሮች ስናይ የፍትህ ዘርፍ ማሻሻያ ስራ ሳይሆን የፍትህ ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን እንደሚያስፈልግ አጠያያቂ አይሆንም። በዘርፉ የሚታዩ ክፍተቶች እና እጥረቶች እንዲሁም በዘርፉ ላይ ህዝቡ ያለው የእርካታ ማጣት በዘርፉ ላይ በሚደረጉ ማሻሻያዎች በበቂ ሁኔታ ሊስተካከል እና ሊታረም አይችልም። በዘርፉ ላይ የሚያስፈልገው ለውጥ ሊመጣ የሚችለው ተጨባጭ ስር ነቀል ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ ትራንስፎርሜሽናል መፍትሔዎችን እና እርምጃዎችን በመውሰድ ነው። ስለሆነም በዘርፉ ላይ ለውጥ ለማምጣት የምንከተለው አካሄድም ሆነ ንድፍ በዘርፉ ላይ የተለመደ ማሻሻያን ለማምጣት ሳይሆን ዘርፉን ትራንስፎርም ከማድረግ አንጻር የተቃኘ እንዲሆን ያስፈልጋል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ሰነድ ላይ “ማሻሻያ” እና “ትራንስፎርሜሽን” የሚሉትን አገላለጾች በተመሳሳይ ትርጉም በተለያዩ ገለጻዎች በማለዋወጥ የሚጠቀም ሲሆን “ማሻሻያ” የሚለው ቃል የገባበት አውድ ከላይ ለማመላከት እንደተሞከረው ስር ነቀል የሆነ እና ተጨባጭ ለውጥን የተመለከተ ስለመሆኑ መገንዘብ ያስፈልጋል። በመሆኑም ከዚህ በታች የተዘረዘሩ የለውጥ አጀንዳዎች ትራንስፎርሜሽናል ለውጥን ሊያመጡ የሚችሉ መሆናቸውን ልብ ይሏል። ይህም ሲባል ከአጠቃላይ ሀገራዊ የሪፎርም ሥራዎች ጋር በሚጣጣምና በሚናበብ መልኩ ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል።

4.2 የተለዩ ማሻሻያ እርምጃዎች እና የትራንስፎርሜሽን አምዶች

4.2.1 የመሰረተ-ማህበረሰብ የፍትህ አገልግሎት

ከላይ ለማየት እንደሞከርነው እ.ኤ.አ. 2020 ዓ.ም በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የፍትህ ፍላጎት እና እርካታ የዳሰሳ ጥናት ተከናውኗል። ይህ የዳሰሳ ጥናት በስድስት ክልሎች 5400 የሚሆኑ በዘፈቀደ የተመረጡ መረጃ ሰጪ ግለሰቦችን በመጠየቅ የተከናወነ ጥናት ነው። በዚህ የዳሰሳ ጥናት ከተሳተፉ ግለሰቦች እና ባለሙያዎች ጋር በተደረጉ ጥልቅ ቃለ መጠይቅ እና የቡድን ውይይቶች አማካኝነት መረጃዎች የተሰበሰቡ ሲሆን በጥናቱም በኢትዮጵያ የፍትህ ፍላጎት እና እርካታን በተመለከተ በጣም በርካታ እና እጅግ አስፈላጊ የሆኑ ጥልቅ ግኝቶች ተገኝተዋል። ይህ የዳሰሳ ጥናት ካገኛቸው ግኝቶች መካከል፡-

- ከኢትዮጵያ አጠቃላይ ህዝብ 40% የሚሆነው በየአራት አመቱ አንድ እና ከዚያ በላይ ከባድ እና ለመፍታት አስቸጋሪ የሆነ የሕግ ችግሮች ወይም ግጭቶች ያጋጥሙታል። በሌላ አነጋገር አማካኝ በየአመቱ 7.4 ሚሊየን ከባድ የሕግ ችግሮች ወይም ግጭቶች በኢትዮጵያ ያጋጥማሉ።

- ከላይ ከተጠቀሱት የሕግ ችግሮች ወይም ግጭቶች መካከል በዚህ በተደረገው የዳሰሳ ጥናት መሰረት 5.2 ሚሊየን የሚሆኑት ችግሮች ወይም ግጭቶች መፍትሔ አያገኙም ወይም ፍትሀዊ የሆነ መፍትሔ አይሰጣቸውም።

- በዚህ ጥናት የተለዩት በጣም የተለመዱ የሕግ ነክ ችግሮች ወይም ግጭቶች ውስጥ በቀዳሚነት ከመሬት ጋር የተያያዘ (34%)፣ ወንጀል (20%)፣ ከጎረቤቶች ጋር ያለ አለመግባባት ወይም ግጭት (11%)፣ የቤተሰብ ጉዳይ (11%)፣ የቤት ውስጥ ጥቃት (6%)፣ ከገንዘብ ጋር የተያያዙ አለመግባባቶች (4%) እንዲሁም ከአሰሪ እና ሰራተኛ ጋር የተያያዙ (4%) እንደቅደም ተከተላቸው ናቸው።

- እነኚህ የሕግ ችግሮች ወይም ግጭቶች ግለሰቦች ላይ የሚያስከትሉት ተጽዕኖ በጾታ፣ በትምህርት ደረጃ እንዲሁም በከተማ ወይም በገጠር በመኖር ምክንያት የተለያየ ነው።

- በኢትዮጵያ በአብዛኛው ግጭቶችን ለመፍታት በስራ ላይ ከሚውሉ የግጭት መፍቻ መንገዶች መካከል ድርድር ወይም በአካባቢ ሽማግሌዎች የሚከናወን የግልግል ዳኝነት ቅድሚያውን በ45% የሚይዝ ሲሆን በመደበኛ እና በማህበራዊ ፍርድ ቤቶች የሚከናወን ዳኝነት ደግሞ በ18% ተከታዩን ደረጃ ይይዛል። ሌላው ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ በአካባቢ ሽማግሌዎች የሚከናወነው የግጭት አፈታት ሂደት ከሁሉም ሌሎች የግጭት መፍቻ ስርዓቶች በህብረተሰቡ ዘንድ ከፍትሐዊነት እና ጥራት አንጻር የተሻለ ተቀባይነት ያለው መሆኑ ነው።

ይህ የዳሰሳ ጥናት እና በዚህ ጥናት የተለዩት ግኝቶች የሚያረጋግጡት ነገር ቢኖር ህዝብን ማዕከል ያደረገ

ማህበረሰብ አቀፍ የፍትህ አገልግሎት ከመደበኛው የፍትህ አገልግሎት ጋር በአማራጭ እና በደጋፊነት አጣጥሞ ማስኬድ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ መሆኑን ነው። ምንም እንኳን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ-መንግስት ለባህላዊ እና ልማዳዊ የሕግ ስርዓቶች አውቅና ስለመስጠት የሕግ መሰረት ቢያስቀምጥም በዚህ ረገድ በተጨባጭ በተግባር የተከናወነው ስራ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። በቅርቡ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አማካኝነት በክልሉ ለሚገኙ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓቶች እውቅና ለመሰጠት ከተደረገው ጥረት ባሻገር በዘመናዊው እና በልማዳዊው የሕግ ስርአቶች መካከል የማጣጣም እና የማግባባት ስራ ለመስራት የተሄደበት ርቀት በእጅጉ ውስን ነው። በመሆኑም ከዚህ በታች የተዘረዘሩ እርምጃዎችን በመውሰድ ይህንን እጥረት ማስተካከል ያስፈልጋል፤

- በየአካባቢው በማህበረሰቡ ውስጥ በየእለቱ የሚከሰቱ ግጭቶችን የሚፈቱ የአካባቢ ሽማግሌዎችን መለየት፣ እዉቅና መስጠት እና መመዝገብ፣
- የእነኚህን ሽማግሌዎች አቅም ለማጎልበት እና የሚሰጧቸው ውሳኔዎችም ሆነ ግጭት የሚፈቱበት መንገድ ከመሰረታዊ የህገ-መንገስቱ እሴቶች ጋር የተጣጣሙ እንዲሆኑ አጫጭር ስልጠናዎችን እንዲያገኙ ማድረግ፣
- ሁሉም ክልል እና አስተዳደር በአካባቢ ሽማግሌዎች የሚሰጠውን ፍትህ ነጻነት በማይጋፋ እና በማያንኳስስ አግባብ ለማህበረሰብ አቀፍ የፍትህ አገልግሎት እውቅና የሚሰጥ፣ የሚደግፍ እና የአፈጻጸም ክትትል የሚደረግበትን ስርዓት የሚገዛ ህግ እንዲያወጣ ማድረግ።

4.2.2 የፍትህ ዘርፍ አመራሮችና ባለሙያዎችን ማጥራት

በፍትህ ዘርፉ አገልግሎት ላይ ህብረተሰቡ እርካታ እንዳይኖረው እና የምሬት ምንጭ እንዲሆን ከሚያደርጉ ምክንያቶች መካከል በዘርፉ ያሉ ባለሙያዎች የሙያ ብቃት እና የሥነ-ምግባር ጥራት መጓደል አንዱ እና ዋነኛው ነው[13]። በተለይ በፍትህ ዘርፉ ያሉ ባለሙያዎች በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሚሰጠው ትምህርት ወይም ስልጠና ላይ ባለ የጥራት መጓደል ምክንያት እንዲሁም በዘርፉ ተቋማት በሚደረግ የሰራተኛ ወይም ባለሙያ ምልመላ እና ሹመት ሂደት በሚስተዋል ክፍተት ምክንያት አብዛኞቹ ዳኞች፣ ዐቃብያነ ህግ ወይም ፖሊሶች ከቴክኒካዊ እና ሙያዊ ብቃት አንጻር ከዝቅተኛው መስፈርት ወይም ደረጃ በታች ናቸው ብሎ ለመደምደም ይቻላል። ምንም እንኳን ቀደም ሲል ከነበሩ ጊዜያት አንጻር ሲታይ በፍትህ ዘርፉ የሚገኙ ባለሙያዎች በሕግ የመጀመሪያ ዲግሪ እና ከዚያ በላይ ያላቸው ቁጥራቸው ከፍተኛ ቢሆንም በተወሰኑ አጋጣሚዎች ግን እነኚህ የትምህርት ማስረጃዎች የተገኙባቸው ትምህርት ቤቶች ዲግሪን የሚያድሉ እንጂ ጥራት ያለው ትምህርትን የሚሰጡ አለመሆናቸውን መታዘብ ይቻላል። በዚህም ምክንያት እነኚህ የትምህርት ማስረጃዎች በመርህ ደረጃ የሚያረጋግጡትን የትምህርት እና የእውቀት ደረጃ በተጨባጭ ላይመሰክሩ የሚችሉበት አጋጣሚ ሰፊ ነው።

[13] ከላይ ማስታወሻ ቁጥር 9፣ ገጽ 332

ከዚህ በተጨማሪ በፍትህ ዘርፉ በስፋት የሚታየው ሙስና እና የተጠያቂነት አለመኖር በሙስና ተዘፍቀው ፍትህን በማዛባት ላይ የሚገኙ ባለሙያዎች በአድራጎታቸው እንዲቀጥሉ የልብ ልብ የሚሰጣቸው ሁኔታ ተከስቷል[14]። ለዚህም ማሳያ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው በዳኞች ላይ ለዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የቀረቡ አቤቱታዎች እንዲሁም በቅርብ ጊዜ የቀረቡ የዳኞችን፣ ዐቃብያነ ህግን እና ፖሊሶችን በሙስና መዘፈቅ የሚያሳዩ አስደንጋጭ የወንጀል ምርመራ እና ክስ ሂደቶች ዘርፉ በምን ያህል ደረጃ እና ጥልቀት ለሙስና የተጋለጠ መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው።

ይህንን ችግር ለመቅረፍ የተደራጀ እና የተጠቃለለ የፍትህ ዘርፉ አመራሮችና ባለሙያዎችን የማጥራት ፕሮግራምን ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል። ይህ የማጥራት ፕሮግራም የአመራሩንና ባለሙያዉን ምሉዕ የስብዕና ደረጃ፣ ሙያዊ ብቃት እና አጠቃላይ ለስራው ያለውን ተስማሚነት የመገምገም ወይም የመመዘን ሂደትን የሚመለከት ነው። ምንም እንኳን የተለያዩ የፍትህ ዘርፉን አመራሮችና ባለሙያዎች ለማጥራት ልንከተላቸው የሚገባቸው መንገዶች እና ዘዴዎች የተለያዩ ቢሆንም የሀብት ማጣራት፣ የስነ-ምግባር ሁኔታን ማጣራት እና በሙያው ያለውን እውቀት እና ክህሎት አቅም እና ብቃት መመዘን አሁን ለያዝነው ጉዳይ በእጅጉ ተስማሚ ይሆናል። ዳኞችን፣ ዐቃብያነ ህግን እና ፖሊሶችን ለማጥራት የሚጠቅሙ በአለም ላይ ተቀባይነት ያላቸው ደረጃዎች እና አሰራሮች ያሉ ሲሆን እነኚህ ደረጃዎች እና አሰራሮችን በእኛ ሀገር ተግባራዊ ለሚደረገው የሕግ እና ፍትህ ስርዓት ማሻሻያ ስራ ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል። በዚህ ረገድ ተቀባይነት ካላቸው የማጥራት ዘዴዎች መካከል ተመራጭ የሆነው ዘዴ ገለልተኛ ጊዜያዊ አጣሪ ኮሚሽን በማቋቋም የሚከናወነው የአሰራር ዘዴ ነው። በሌላ በኩል በስራ ላይ ያሉ ተቋማትን እና መድረኮችን በመጠቀምም ይህንን የማጥራት ስራ ለመስራት ይቻላል። በመጨረሻም ይህንን የማጥራት ሂደት ከመምራት አንጻር ሁለት አማራጭ መንገዶች ያሉ ሲሆን እነኚህም “የዳግም ምደባ/ሹመት ሂደት” እና “የክለሳ/ግምገማ ሂደት” ሲሆኑ እኛ ልንከተለው የሚገባው አማራጭ “የክለሳ/ግምገማ ሂደትን” ሊሆን ይገባል። በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት ስንመለከት በመጀመሪያው መንገድ ይህ ማጥራት በሚከናወንበት ተቋም ወይም ዘርፍ ያሉ ሁሉም የስራ መደቦች ባዶ እንደሆኑ ተቆጥሮ ቀደም ሲል በስራ መደቦቹ ተመድበው የነበሩ ባለሙያዎች ዳግም ለስራ መደቡ እንደ አዲስ እንዲያመለክቱ በመጋበዝ እና እንዲወዳደሩ በማድረግ በማጣሪያው መስፈርት መሰረት ብቁ የሆኑትን በስራ መደቡ መመደብ ወይም መሾምን የሚመለከት ነው። ይህ መንገድ እጅግ ስር ነቀል የሆነ አካሄድ ሲሆን ለመተግበርም በእጅጉ አስቸጋሪ ነው። ሁለተኛው አካሄድ ማለትም “የክለሳ/ግምገማ አካሄድ” በአንድ የማጥራት ስራ የሚከናወንበት ተቋም ወይም ዘርፍ ውስጥ በተለያዩ የስራ መደቦች በማገልገል ላይ የሚገኙ ባለሙያዎች የስራ መደባቸውን ሳይለቁ እና በስራ ላይ እያሉ ለያዙት የስራ መደብ የሚመጥኑ መሆኑን በመገምገም እና በማጥናት የሚመጥኑ ሆነው ተገኙትን በስራ መደቡ እንዲቀጥሉ የማድረግ የሚመጥኑ ሆነው ያልተገኙትን ብቻ ደግሞ የማሰናበት ሂደት ነው።

ይህ የማጥራት ስራ በተለያዩ ምዕራፎች ከፋፍሎ መፈጸም የሚቻል ሲሆን ለዚህ አላማም በቀዳሚው ምዕራፍ

[14] ከላይ ማስታወሻ ቁጥር 10፣ ገጽ 156

በአመራር ደረጃ ሊካሄድ ይችላል። በዚህ ሂደት የአመራር ብቃት ፣ ተቋማዊ ግንባታ፣ የውጤታማነት ምዘና እንዲሁም ተጠያቂነትን ማዕከል ባደረገ ሁኔታ የማጥራት ሥራ በማካሄድ ጠንካራና ቁርጠኛ የአመራር ሥርዓት መፍጠር ያስችላል። በመቀጠልም በሁለተኛዉ በከፍተኛው መዋቅር ላይ ከሚገኙት ዳኞች፣ ዐቃብያነ ህግ እና ፖሊሶች በመጀመር እስከታችኛው ፈጻሚ ድረስ የማጥራት ስራውን ማስቀጠል ይቻላል። በዚህ መንገድ የሚመራ ተአማኒነት ያለው የማጥራት ሂደት በህዝብ ዘንድ በዘርፉ የሚገኙ ተቋማት ተቀባይነታቸው እና ተአማኒነታቸው እንዲጨምር የሚያደርግ በመሆኑ በቀጣይ በፍትህ ዘርፉ በሚደረግ የማሻሻያ ስራ የዘርፉን ባለሙያዎች በብቃት እና በአግባብነት የማጥራት ተግባር ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

4.2.3 ያደገ እና ውጤታማ የኢንፎርሜሽን ኮሚውኒኬሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም

በአሁኑ ወቅት በዘርፉ የኢንፎርሜሽን ኮሚውኒኬሽን ቴክኖሎጂን በመጠቀም ረገድ ያለው ልምድ እጅግ አነስተኛ እና የተበታተነ ነው። ምንም እንኳን ባለፉት ጊዜያት ዘርፉን በኢንፎርሜሽን ኮሚውኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ኢ.ኮ.ቴ) ለመደገፍ የሚያስችል የተቀናጁ ጥናቶች እና የመፍትሔ እርምጃዎች የተሞከሩ ቢሆንም መሬት ላይ የተተገበረ ተጨባጭ ስርዓት ግን የለም። በዚህም ሳቢያ ኢ.ኮ.ቴን በአግባቡ በመጠቀም የፍትህ ዘርፉ ውጤታማ እና ተጠያቂነት የሰፈነበት እንዲሆን ለማድረግ ይቻል የነበረውን መልካም አጋጣሚ ለመጠቀም አልተቻለም። ይልቁንም በዘርፉ ያለው ያልዳበረ የኢ.ኮ.ቴ አጠቃቀም የፈጠራቸው ክፍተቶች በዘርፉ ለሚስተዋለው የመልካም አስተዳደር እጦት እና ሙስና በር ከፋች ሆኗል ለማለት ይቻላል[15]። ከዚህ በተጨማሪ በዘርፉ ያለው ዝቅተኛ እና ውጤታማ ያልሆነ የኢ.ኮ.ቴ አጠቃቀም ከዘርፉ በሚመነጭ ተጨባጭ የሆነ መረጃን መሰረት ያደረገ የፖሊሲ ውሳኔ በመንግስት በኩል ለማስተላለፍ እንዳይቻል አድርጓል። ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው በዘርፉ የሚታየው ዝቅተኛ እና ያልዳበረ የኢ.ኮ.ቴ አጠቃቀም በዘርፉ ውጤታማነት ላይ ያስከተለው አሉታዊ ተጽዕኖ ሲታይ ውጤታማ የሆነ የኢ.ኮ.ቴ. አጠቃቀም ቢኖር ኖሮ ዘርፉ ሊኖረው የሚችለውን አዎንታዊ ውጤት ማየት ያስችለናል። ስለሆነም በዘርፉ የሚገኙ የኢ.ኮ.ቴ የስራ ክፍሎችን እንደ ደጋፊ የስራ ክፍሎች አድርጎ የመውሰድ አመለካከት ሊቀየር የሚገባ ሲሆን በቀጣይም በሚኖር የፍትህ ዘርፉ የማሻሻያ ፕሮግራም የስራ ክፍሎቹ እንደዋና የስራ ሂደት አካል ተደርገው የሚወሰዱበት አረዳድ ሊፈጠር ይገባል። ይህ ደግሞ በተለይ የዘርፉ ዋና ባለሙያ የሆኑት ዳኞች፣ ዐቃብያነ ሕግ እና ፖሊስ አባላት በኢ.ኮ.ቴ ላይ ያላቸውን ግንዛቤ ከፍ በማድረግ የማላመድ ስራን የሚጠይቅ ሲሆን ይህም ስራ እነኚህ ባለሙያዎች በቀላሉ እና በብቃት ኢ.ኮ.ቴን መጠቀም የሚችሉበት ደረጃ ላይ እንዲደርሱ በማድረግ የሚለካ ይሆናል።

4.2.4 የወንጀል፣ የአስተዳደርና ፍትሐብሔር ፍትህ ስርዓት ፕሮግራም፡ በአዲስ አስተሳሰብ

አሁን በኢትዮጵያ በስራ ላይ ያለው የወንጀል ፍትህ አስተዳደር የሚመራው ከስድስት አስርት አመታት በፊት በወጣ የወንጀለኛ መቅጫ እና የፍትሐብሔር ሕግ ሥነ-ሥርዓት መድብል ነው። በዚህም ምክንያት መድብሎቹ እና

[15] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 165

እነርሱን ተከትሎ በተግባር የሚከናወኑት ሂደቶች ከዘመኑ ጋር የማይሄዱ ኋላቀር በመሆናቸው ምክንያት የፍትህ ስርዓቱ ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖን አሳድሯል። በአጭሩ አሁን በስራ ላይ የሚገኙት የወንጀለኛ መቅጫ እና የፍትሐብሔር ሕግ ሥነ ሥርዓት መድብሎች ጊዜው ያለፈባቸዉ እና ለ21ኛው ክፍለ ዘመን የማይመጥኑ ናቸው ቢባል ማጋነን አይሆንም። በሌላ በኩል በአንዳንድ መሠረታዊ ጉዳዮች የፍትሐብሔር ህጉ ድንጋጌዎችም ከወቅቱ ጋር የማይጣጣም ድንጋጌዎችን በመያዛቸዉ በተለያዩ ጊዜያት በወጡ አዋጆች አማካይነት እየተሸራረፉ ማሻሻያ የተደረገባቸዉ ቢሆንም አንዳንዶቹ አሁንም ባሉበት ሁኔታ የቀጠሉ ናቸዉ። ከዚህም የተነሳ ለማሻሻያ የሚያግዝ የጥናት ሥራ በፌዴራል ፍትህና ሕግ አንስቲትዩት ተደርጎ ምክረ-ሐሳብን የያዘ ሪፖርት ለፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መቅረቡ የሚታወስ ነዉ[16]። ይህንንም እውነታ ከግምት በማስገባት ጊዜውን የዋጀ ረቂቅ የወንጀል ሕግ ሥነ-ስርዓት እና የማስረጃ ህግ መድብል ተዘጋጅቶ እንዲጸድቅ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቧል። በተጨማሪም ለዘመኑ የሚመጥን የፍትሐብሔር እና የፍትሐብሔር ሕግ ሥነ-ሥርዓት ረቂቅ ማዘጋጀትና በሚመለከተዉ አካል በማስጸደቅ ተግባር ላይ ማዋል ያስፈልጋል። በአዲስ መልክ የተዘጋጀዉም ሆነ የሚዘጋጀዉ የሥነ-ሥርዓት ሕጎች መድብሎች የወንጀልና የፍትሐብሔር ፍትህ አስተዳደሩን ከስሩ አንስቶ ለማደስ እና ለማዘመን እጅግ ጠቃሚ እንደሚሆን ይታመናል። ወደፊት የሚዘጋጀዉ የፍትሐብሔር ሕግና የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ረቂቅም ሆነ አሁን የተዘጋጀዉ የወንጀል ሕግ ሥነ-ሥርዓት መድብል ለዘርፉ ያመጣሉ ተብሎ ከሚጠበቁት መሻሻሎች መካከል ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ይገኙበታል።

- ከህገ-መንግስት እና ከፌዴራል ስርዓቱ ጋር የተጣጣመ የወንጀል እና የፍትሀብሔር ፍትህ አስተዳደር እንዲኖር ያደርጋሉ፣
- በቀድሞው የሥነ ሥርዓት ህግ እና በተግባር የነበሩ የግልጽነት ችግሮች እና ክፍፈቶችን በመለየት በእነኚህ ሳቢያ ሊከሰቱ የሚችል የመሰረታዊ መብቶች ጥሰቶችን እንዳይፈጸሙ ይከላከላሉ፣
- ለልዩ ወንጀል ምርመራ ቴክኒኮች እውቅና ይሰጣል፣ የአፈጻጸም ገደብ ስርዓትን ያስቀምጣል፣
- በኢትዮጵያ የህግ ስርዓት ያልነበረን እና እንደክፍተት ይታይ የነበረውን በወንጀል ምርመራ እና ክርክር ጉዳዮች የማስረጃ ህግን ያስቀምጣል፣
- በወንጀል ጉዳይ የተሰጠ ፍርድ ዳግም ዳኝነት እንዲታይ የሚቻልባቸውን ውስን ሁኔታዎች ይለያል፣
- እርቅን፣ ባህላዊ የግጭት መፍቻ መንገዶችን እና የጥፋተኝነት ድርድርን ጨምሮ የወንጀል ጉዳይ

[16] የሰዎች ሕግ፣ የንብረት ሕግ፣ የዉል ሕግ፣ ... ለማሻሻያ የሚያግዙ ጥናቶች ሪፖርት፣ 2012 ዓ.ም.

ውሳኔ የሚሰጥባቸው አማራጭ መንገዶችና መፍትሔዎች አውቅና በመስጠት የአፈጻጸም ዝርዝር ድንጋጌዎችን አስቀምጧል፣

- ከእስር ውጪ ላሉ ሌሎች አማራጭ ወይም ምትክ ቅጣቶች እውቅና ሰጥቷል፣
- በወንጀል ጉዳይ ለሚደረግ አለምአቀፍ የህግ ትብብር አስፈላጊ የሆነ የህግ ማዕቀፍን ይዟል።

ሲጠቃለል አሁን የተዘጋጀዉን ተራማጅ ረቂቅ የወንጀል ህግ ስነ-ስርዓት እና የማስረጃ ህግ እንዲሁም በቀጣይ የሚዘጋጀዉን የፍትሐብሐር ሕግ እና የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ መድብል ማጽደቅ እና ተግባራዊ ማድረግ ዘርፉን በማዘመን እና በማሻሻል ረገድ ጉልህ ሚናን የሚጫወት እንደሆነ ይታመንበታል።

ዜጎች በብዛት ቅሬታ ከሚያቀርቡባቸዉ ጉዳዮች ከአስተዳደራዊ በደል ጋር የተያያዙት በቀላሉ የሚገመቱ አይደሉም። በተለያዩ ጊዜያት ከመንግሥታዊ የአስተዳደር ተቋማት ከሚደርስ አስተዳደራዊ በደል የመነጩ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች በሰፊዉ የሚነሱበት ሁኔታ አለ። በ2012 ወደ ስራ የገባው የፌደራል አስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ የመንግስት አሰራር ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው እንዲሆን፤ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍንና የዜጎች መብትና ጥቅም ሳይሸራረፍ እንዲከበር ለማድረግ አብዛኛው መስሪያ ቤቶች እንደ አዋጁ ድንጋጌ ባለመፈጸማቸው የሚደርስ የመብት ጥሰት እንዳይኖር በሕጉ መሠረት መጎትጎት፣ መደገፍ እና የቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋትና ፍ/ቤቶችም ለክለሣ ሒደት ያቋቋሟቸው ችሎቶች የዳኞች ዝውውር እና ከሌሎች ጉዳዮች ጋር ደርቦ እንዳይሰሩ ማድረግ ያስፈልጋል። እነዚህንና ሌሎች እርምጃዎችን በመዉሰድ አስተዳደራዊ ፍትህ እንዲሰፍን ማድረግ ይጠበቃል።

4.2.5 የተጠናከረ ንቃተ-ሕግ እና የሕግ ድጋፍ

በህብረተሰቡ ዘንድ ያለው ሕግን እና የዳኝነት አካላትን ተግባር እና ኃላፊነት ያለመረዳት እንዲሁም የግለሰቦችን መብት እና ግዴታን ያለማወቅ ክፍተት ዜጎች በፍትህ ስርዓቱ ላይ እምነት እንዲያጡ ካደረጋቸው ምክንያቶች መካከል ይገኙበታል። የፍትህ ስርዓቱ እንዴት እንደሚሰራ እና እጅግ የተወሳሰበውን የፍትህ ስርዓቱ ጉዳይ የማስተናገጃ መንገድን በአግባቡ አለመረዳት በሂደቱ በተከራካሪነት፣ በምስክርነት ወይም በወንጀል ተጎጂነት በሚሳተፉ ዜጎች ላይ የመሰላቸት፣ ተስፋ የመቁረጥ እና የእርካታ ማጣት ስሜትን በስርዓቱ ላይ እንዲያዳብሩ ያደርጋቸዋል። ምንም እንኳን የተሻለ የተማሩ እና የተሻለ የገንዘብ አቅም ያላቸው ዜጎች ብቃት ያለው የሕግ ባለሙያን በመቅጠር ውስብሰብ የሆነውን የፍትህ አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ለመወጣት የሚችሉበት እድል ቢኖርም ይህ አማራጭ ግን በተለይ መሰረታዊ የሕግ እውቀት እና የሕግ ባለሙያ ለመቅጠር የገንዘብ አቅም ለሌላቸው ዜጎች እጅግ አስቸጋሪ እና የማይቻል ነው። ስለሆነም በቅድሚያ ውጤታማ በሆነ የሕግ ትምህርት እና የንቃተ ሕግ ዘመቻ የዜጎችን መሰረታዊ የንቃተ-ሕግ ደረጃ ማሳደግ አስፈላጊ ይሆናል። ይህ አይነት ዘመቻ በትክክለኛው አቅጣጫ እና አግባብ የሚከናወን ከሆነ ዜጎችን ላልተፈለገ የሕግ ክርክር እና ችግር የሚዳርጉ

እጅግ ቀላል እና የተለመዱ ስህተቶች እንዳይፈጸሙ ወይም ወዲያው እልባት እንዲያገኙ ያስችላል። ከዚህ በተጨማሪ በወንጀል እና በፍትሐብሔር ጉዳይ በፍትሕ አካላት ጉዳይ ያላቸው ዜጎች መሰረታዊ አገልግሎት እንዲያገኙ እና መሰረታዊ መብቶቻቸው እንዲጠበቅ ለማድረግ የሕግ ድጋፍ ተደራሽነትን ማጎልበት ያስፈልጋል። በተለይ ገንዘብ ከፍለው የሕግ ድጋፍ አገልግሎት ለማግኘት የማይችሉ አቅመ ደካማ ዜጎች የፍትህ መዛባት እና እጦት እንዳይፈጠር በሚያስችል አግባብ የሕግ ድጋፍ የሚያገኙበትን እድል ማመቻቸት እጅግ አስፈላጊ ነው። ይህንን ለማድረግ የሕግ ድጋፍ ስትረቴጂን መቅረጽ እና ተግባራዊ ማድረግ የሚያስፈልግ ሲሆን ይህ ስትራቴጂ ፈቃድ ያላቸው ጠበቆች በነጻ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት የሚሰጡበትን አማራጭ፣ በሕግ ትምህርት ቤቶች የሚሰጥ የሕግ ድጋፍ፣ በሲቪል ማህበረሰቦች የሚሰጥ የሕግ ድጋፍ እና በተከላካይ ጠበቆች የሚሰጥ የሕግ ድጋፍን አቀናጅቶ የሚመራ ሊሆን ይገባል።

4.2.6 ዘመናዊ አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓቶችን ማስፋፋት

እንደ የግልግል ዳኝነት፣ ዕርቅ፣ እና ማደራደር ያሉ በግል ዘርፉ፣ ወይም ጊዜያዊ በሆነ ስርዓት አልያም ከፍርድ ቤቶች ጋር በተያያዘ አግባብ የሚሰጡ አማራጭ የሙግት መፍቻ ማዕከላት የሚሰጡ አገልግሎቶች በፍትሐብሔራዊ እና ገንዘብ ነክ በሆኑ አለመግባባቶች ረገድ የፍትህ ስርዓቱን ውጤታማነት እና ቅልጥፍና በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ አዎንታዊ አስተዋጽኦን ያበረክታሉ። አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓት በመደበኛ ፍርድ ቤት የሚታየውን የመዛግብት መጨናነቅ እና የውሳኔ መዘግየት በመቀነስ ረገድ አይነተኛ ሚና አለው። እነኚህ የሙግት መፍቻ መንገዶች ለሙስና የመጋለጥ ዕድላቸው አነስተኛ ሲሆን ለጉዳይ እልባት ለመስጠትም የሚወስዱት ጊዜ ከመደበኛ ፍርድ ቤት አንጻር ሲታይ አጭር ነው። ከዚህ በተጨማሪ የሙግቱ ተካፋይ የሆኑት ወገኖች ለሙግቱ ምክንያት የሆነው ጉዳይ በተለያዩ ሙያዎች ባለቤት በሆኑ ባለሙያዎች እንዲታይላቸው እና አሳማኝ እና ትክክለኛ ፍትህ እንዲያገኙ እድል ያገኙበታል። በተለይ የሙግቱ ምክንያት የሆነው ጉዳይ እጅግ ውስብስብ እና የልዩ ሙያ እውቀትን የሚፈልግ ጉዳይ በሚሆን ጊዜ አማራጭ ሙግት መፍቻ ስርዓት ለጉዳዩ ቅርበት ባላቸው ባለሙያዎች ጉዳዩ እንዲታይ እና እልባት እንዲያገኝ የሚያስችል እድልን የሚፈጥር በመሆኑ በዚህ መንገድ የሚደረስበት እልባት ፍትሐዊ እና አሳማኝ እንዲሆን ያደርገዋል። በቅርብ ጊዜ እነኚህን የአማራጭ ሙግት መፍቻ ስርዓቶችን እና ከፍርድ ቤቶች ጋር የተያያዘ ማደራደርን አስመልክቶ የወጡ የህግ ማዕቀፎች ከላይ የተመላከቱትን መልካም እድሎች ለመጠቀም በእጅጉ ያግዛሉ። ስለሆነም በቀጣይ የሚደረጉ የፍትህ ስርዓት ማሻሻያ ስራዎች እነኚህን አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓቶች በማስፋፋት እና በማስተዋወቅ ላይ ትኩረት ማድረግ ይኖርባቸዋል።

4.2.7 የተሻለ የተዋረድ እና የጎንዮሽ ቅንጅት፣ መማማርና የጋራ ፍኖተ ካርታ

በፍትህ ዘርፉ ከሚስተዋሉ አንኳር ችግሮች መካክል አንዱ በፍትህ ዘርፉ ውስጥ ባሉ ተቋማት መካከል ያለው ውጤታማ የተዋረድ እና የጎንዮሽ ቅንጅት መጓደል ነው። ከዚህም በተጨማሪ የተቋማቱ ገለልተኝነትና ነጻነት ተጠብቆ የጋራ በሆኑ ጉዳዮች ዙሪያ የጋራ የሆነ ፍኖተ ካርታ ያለመኖርም ሌላዉ ችግር ነዉ። በፌዴራል እና በክልል

የፍትህ አካላት መካካል ያለው ቅንጅት እና መናበብ እጅግ በጣም ውስን እና ለይምሰል የሚደረግ ነው። ይህ ሁኔታም በተመሳሳይ የመንግስት ደረጃ ውስጥ በሚገኙ የፍትህ አካላት መካከልም የሚስተዋል እውነታ ነው። በዳኝነት ነጻነት እና ተቋማዊ ነጻነት ዙሪያ ያለ የግንዛቤ እና አረዳድ ዝንፈት ለዚህ አይነቱ ሁኔታ መፈጠር አይነተኛ ምክንያት እንደሆነ ለመረዳት ይቻላል። ይህ አይነት የቅንጅት መጓደል የፍትህ ዘርፉ ፍትህን ለህብረተሰቡ መስጠት የማይችልበት ከባቢን እንዲፈጥር አድርጎታል። በዚህ አይነት ከባቢ በተቋማት መካከል ባለ ከንቱ ፉክክር እና የክብር ግጭት ምክንያት ለህብረተሰቡ መሰጠት የሚገባው ፍትህ እንዲጓደል አድርጎታል። የቅንጅት መጓደል፣ የጋራ አላማ እና መድረክ አለመኖር የፍትህ ዘርፉን ውጤታማነት ብቻ ሳይሆን የተቋማቱን ምሉዕነት እና በህዝብ ዘንድ ያላቸውን አመኔታ እንዲሸረሸር አድርጎታል። በተለይ ደግሞ በፍትህ ዘርፉ ውስጥ የሚገኙ ተቋማት የፍትህ ዘርፉን አስመልክቶ ጠቅለል ያለ እይታ እና ሀገራዊ ትርጉም ሰጥቶ ጉዳዮችን የመገንዘብ እጥረት መኖሩ ለችግሩ መባባስ ምክንያት ሆኗል። ስለሆነም በቀጣይ የሚደረግ የፍትህ ስርዓት ማሻሻያ ስራ ቁልፍ ትኩረት ሊሆን የሚገባው በየደረጃው ያሉ የፌዴራልና የክልል መንግስታት የግንኙነት ስርዓትን በማጠናከርና በፌደራላዊ ሥርዓተ-መንግስት ውስጥ በመንግስታት መካከል የሚካሔዱ እርስ በርስ ምክክሮችና የሚደረጉ የትብብር ስምምነቶች ከሥርዓቱ ባህሪ የሚመነጭ መሆኑን በመረዳት ለሥርዓቱ ዘለቄታ ተፈላጊ የሆኑ የጋራ አስተሣሰቦችን በመያዝና በማጠናከር ሥርዓቱ ዘላቂ ሰላምን ለማስፈንና ዋስትና ያለው ዲሞክራሲን ለማረጋገጥ የየእርከኑ አካላት አቅሞችን በተገቢው መንገድ አቀናጅቶና አዋህዶ ዘርፈ-ብዙ የፍትህ ዘርፉን ተግባራት ለማከናወን በቀጣይ ሊሰራ ይገባል። በተጓዳኝም በፍትህ ዘርፉ ውስጥ ባሉ ተቋማትም መካከል የጋራ በሆኑ ጉዳዮች ፍኖተ ካርታ እንዲኖር በማድረግ ውጤታማ የሆነ የተዋረድ እና የጎንዮሽ ቅንጅትን በመፍጠር እና በማጠናከር ላይ ነው።

4.2.8 የፌዴራል የፍትህ አካላት ተቋማት በክልሎች ያላቸው ተደራሽነትን ማሳደግ

የፍትህ ዘርፉን አሁናዊ ሁኔታ ስንገመግም ከምናገኛቸው ዋነኛ ክፍተቶች መካከል የፌዴራል የፍትህ አካላት ተቋማት በክልሎች ውስጥ የማይገኙ መሆኑ ነው። አሁን ባለው ሁኔታ የፌዴራል መንግስቱ የዳኝነት ስልጣን ወጥነት እና ተገማችነት በጎደለው መልኩ በተወሰኑ ክልሎች በውክልና ተሰጠቶ እየተሰራ ሲሆን በሌሎች ደግሞ ይህ ውክልና ተነስቶ ይገኛል። ከዚህ በተጨማሪ ይህ ውክልና በተነሳባቸው ክልሎች የፌዴራል የዳኝነት አካል ምንም አይነት ቋሚ የአገልግሎት መስጫ ተቋም የሌለው በመሆኑ በተዘዋዋሪ ፍርድ ቤቶች አገልግሎት መስጠትን ቀጥሏል። የፌዴራል ፍርድ ቤቶች እና ዐቃቤ ህግ በአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች ብቻ ተከማችቶ የሚገኝ ሲሆን በሌላው የሀገሪቱ ክፍል ግን እዚህ ግባ የሚባል ተደራሽነት የለውም። ምንም እንኳን ለክልል ፍርድ ቤቶች እና የዐቃቤ ሕግ ተቋማት የፌዴራል ስልጣን የሆኑ ጉዳዮችን በውክልና ለክልል ተመሳሳይ ተቋማት መስጠቱ ከወጪ አንጻር ምክንያታዊ እርምጃ ተደርጎ የሚወሰድ ቢሆንም በተወሰኑ የፌዴራል መንግስቱ ዋነኛ ጥቅሞቹ እና ትኩረቱ ባለባቸው ጉዳዮች አያያዝ ላይ ግን ይህ እርምጃ ተገቢ ውጤትን ሲያመጣ አልታየም። ገለልተኛ እና ፍትሐዊ የጉዳዮች አያያዝን እና የፌዴራል መንግስቱን ህገመንግስታዊ ግዴታ በአግባቡ ለመወጣት

የፌዴራል መንግስቱ የፍትህ ዘርፍ ተቋማት በክልል ቋሚ ቅርንጫፍ ኖሯቸው ተደራሽነታቸውን ማስፋት የሚኖርባቸው በመሆኑ በዚህ ረገድ በቀጣይ የሚደረገው የፍትህ ስርዓት ማሻሻያ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

4.2.9 ተገቢና ዉጤታማ የኅብረተሰብ ተሳትፎ

የፍትህ ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን ሊሳካ ከሚችልባቸዉ አንዱ ውጤታማ የሆነ የኅብረተሰቡ ተሳትፎ በሚኖርበት ጊዜ ነዉ። ውጤታማና ተገቢው የኅብረተሰብ ተሳትፎ በሚታቀዱ የዘርፉ ዕቅዶች፣ የአፈጻጸም ግምገማዎች፣ ነጻ የሆነ የህብረተሰብ አስተያየት መስጫ ሥርዓት፣ በወንጀል ጉዳዮች ምስክርነት እንዲሁም የአካባቢውን ሠላምና ጸጥታ በማስከበርና በመደገፍ፣ የሚከሰቱ አለመግባባቶችን በባህላዊ የግጭት መፍቻ መንገዶች አማካነት ፍትህ በመስጠት እንዲሁም በሌሎች የተለያዩ መንገዶች ሊገለጽ ይችላል። ይህ የኅብረተሰብ ተሳትፎ በታቀደና በተቀናጀ ሥርዓት በየተቋማቱ የሚፈጸምበት ሁኔታ ሊኖር ይገባል።

4.2.10 የፍትህ ዘርፍ ተቋማት አደረጃጀትን ማስተካከልና ዘርፉን ሳቢና ታማኝነት የተቸረዉ ማድረግ

የፍትህ ዘርፍ ተቋማትን ትራንስፎርሜሽን ውጤታማ ለማድረግ አንዱ ሊታይ የሚገባዉ አስፈላጊዉን የአደረጃጀት ማስተካከያ ማድረግ ነዉ። እስካሁን በነበሩ ሂደቶች ለዘርፉ ወይም ለተቋማት በተናጠል ውጤታማነት ማነቆ የሆኑ የአደረጃጀት ጉዳዮችን በመለየት ማስተካከያ ማድረግን ይጠይቃል። የአደረጃጀት ጉዳይ በአንድ ተቋም ውስጥ ያለዉን ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ተቋማት ጋር በሚኖር ግንኙነትም ማነቆ የሚሆኑትን የሚጨምር ይሆናል።

የፍትህ ዘርፉ ካለዉ የሥራ ውስብስብነትና ክብደት እንዲሁም የተለየ ባህሪ አንጻር በውስጡ ላሉትም ሆነ ከውጪ ለሚቀላቀሉ አመራሮችም ሆነ ባለሙያዎችና ሠራተኞች የሚስብና ለመሥራት የሚያነሳሳ ሊሆን ይገባል። በዘርፉ ውስጥ ያለም ሆነ ከውጪ ወደ ዘርፉ ለመቀላቀል የሚያስብ ባለሙያም ሆነ ሠራተኛ ከጥቅማ ጥቅም፤ ክብር ወይም አቅርቦት አንጻር ሳቢ ባልሆነበት ሁኔታ በዘርፉ ለመቆየትም ሆነ ውጤታማ ሥራ ለማከናወን የመነሳሳት ዕድሉ ጠባብ ይሆናል። አመራሩ፣ ባለሙያውም ሆነ ሠራተኛው የተጣለበትን ሀላፊነት እንዲሁም ሥራውን በታማኝነት እንዲያከናውን አስቻይና አበረታች ማዕቀፍ ያስፈልጋል። ይህ በአጠቃላይ በሀገሪቱ የኢኮኖሚ አቅም የሚወሰን ሆኖ ነገር ግን ተገቢዉን ትኩረት በመስጠት በዘርፉ ላሉ ችግሮች ብቸኛ መፍትሔ ባይሆንም ነገር ግን ለማስተካከል የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ የሚኖረዉ ይሆናል።

በፍትህ ሥርዓቱ ውስጥ የሚገኙ ሰራተኞች ከሥራው ባህሪ ከሚጠይቀው ከፍተኛ በሥነ-ምግባር ማገልገልን፤ ዜጎችም የሚያነሷቸው የፍትህ ጉዳይ በቀጥታ ወሣኝ ሚና ያላቸው እና ሥራው ድግግሞሽ ያለበትና ጉልበትን እንዲሁም አመዛዛኝነትን የሚጠይቅ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ከቅጥር ጀምሮ የሰው ሀብቱን ማሟላት አስቸጋሪና ወደ ፍትህ ተቋማቱ የገቡ ሰራተኞችም በመሰላቸትና በሌሎች አካባቢ በተሻለ ገንዘብ ትንሽ ጉልበት አውጥቶ መስራት ከመፈለግ አንጻር የማይቆዩና የሚኮበልሉ በመሆኑ ይህ የፍትህ ዘርፍ ማሻሻያ በቀጣይ ትኩረት ከሚያደርግባቸው አንዱ ከሰራተኞች ከምደባ፣ ተመጣጣኝ ክፍያና ጥቅማ ጥቅም፣ ክብር አንጻር የሚያበረታቱና ዕውቅና የሚሰጡ ማድረግ ይጠይቃል።

4.3 የአፈጻጸም አቅጣጫዎች

- የታሰበዉ የሪፎርም ሥራ ከግብ እንዲደርስና ዉጤታማ እንዲሆን የየተቋማት የበላይ አመራራ የሚመራዉና ሀላፊነት የሚወስድበት ይሆናል። የየተቋማቱ የሪፎርም ሥራ በዋናነት የሚመለከተዉም ሆነ መመራት ያለበት በየተቋሙ ባለ የበላይ አመራር (ተሹዋሚ አመራር) መሆን አለበት። በየተቋሙ የታሰበዉ ሪፎርም መሳካትም ሆነ ያለመሳካት ሚወሰነዉ በዚያዉ ተቋም ባሌ አመራር ይሆናል። በመሆኑም የአመራር ቁርጠኝነት እና ትኩረት በጣም ወሳኝ ይሆናል።

- የፍትህ ዘርፍ ተቋማት አንዱ ከሌላዉ ጋር የተያያዙና በጋራ ለአንድ ዓላማ (የኅብረተሰቡን የፍትህ ፍላጎት ለማርካት) የሚሠሩ ተቋማት ናቸዉ። ከዚህም በተጨማሪ ካላቸዉ ተቀራራቢ ባህሪ የተነሳ እነዚህ ተቋማት የሚጋሯቸዉ የጋራ ችግሮች አሉ (የሰዉ ኃይል፣ የበጀት፣ ..ወዘተ)። ስለሆነም ተቋማቱ በዉስጣቸዉም ሆነ አንዱ ከሌላዉ ጋር ስለሚሰራዉ የሪፎርም ሥራና ስለሚደረስበት ዉጤት መግባባትና የጋራ አቋም መያዝ ይጠበቅበቸዋል። በፌዴራል ደረጃ ያሉት አርስ በራሳቸዉ እንዲሁም የክልል የዘርፉም ተቋማት በተመሳሳይ እንዲሁም የፌዴራሉ ተቋማት ከክልል አቻ ተቋማት ጋር አስፈላጊዉን የዉይይት መድረኮች በመፍጠር መግባባት ላይ መድረስ ይጠበቅባቸዋል። ይህ ባልሆነበት ሁኔታ የተለያየ ግንዛቤ ተይዞ የዘርፉን ሪፎርም ማሳካት አይቻልም።

- የዘርፉ ተቋማት የአንዱ ብቻ መሻሻል የዘርፉን መሻሻል ስለማያመጣ በጋራ በቅንጅት የሪፎርም ሥራዉን ማሳካት ይጠበቃል። የዘርፉ ተቋማት በፌዴራልና በክልል እርስ በራሳቸዉ የህገ-መንግሥቱን የነጻነትና የገለልተኝነት መርህ በጠበቀ ሁኔታ ሊቀናጁ ካልተቻለ ሪፎርሙን ዉጤታማ ማድረግ አይቻልም። ቅንጅታዊ አሠራር ሲታሰብ በዘርፉ ተቋማት መካከል ብቻ ሳይሆን ከዚያ ዉጪ ካሉ ሌሎች የፍትህ ባለድርሻ አካላት ጋር ጨምር ሊሆን ይገባል።

- የሪፎርም ሥራዉ በአጭር፣ በመካከለኛና በረጅም ጊዜ ሥራዎች በመከፋፈል በሁሉም ደረጃ በጊዜ የለንም መንፈስ ሊሠራ ይገባል። የሪፎርም ሥራዉ በዘገየ ቁጥር ኅብረተሰቡ በዘርፉ ተቋማት አገልግሎት ላይ ያለዉ እምነት እየወደቀና እየተሸረሸረ የሚሄድ ይሆናል። ስለዚህም ይህን ታሳቢ ያደረገ እያንዳንዱን ሥራና ተልዕኮ በጊዜ የለንም መንፈስ መፈጸምና ማሳካት

ያስፈልጋል።

- የፍትህ ዘርፍ ተቋማት ሪፎርም በባህሪዉ ዉስብስብና ትንቃቄን የሚጠይቅ መሆኑ ለማናችንም ግልጽ ነዉ። ሆኖም ግን የማይቻል ነገር ባለመሆኑ እያንዳንዱ ተቋም በተለይም የተቋሙ የበላይ አመራር ተገቢዉን ትኩረት በመስጠት ከተሠራ ብቻ የታሰበዉ ሪፎርም የተሳካ ይሆናል።

- የፍትህ ዘርፍ ተቋማት ሪፎርም በዘርፉ ባሉ ተቋማት ጥረት ብቻ ሊሳካ አይችልም። ለሪፎርሙ መሳካት ሌሎች የሚመለከታቸዉን ባለድርሻ አካላት እንዲሁም ኅብረተሰቡን በሚከገባ ማሳተፍ ያስፈልጋል።

- ሪፎርሙን በታሰበዉ መንገድ ለማሳካትና ዉጤታማ ለማድረግ በየደረጃዉ ተገቢዉ የክትትልና ድጋፍ እንዲሁም ግምገማ ሥራ ሊሠራ ይገባል። በየጊዜዉ እየተከታተሉ ከላይ እስከታች ድረስ በተናበበና በተቃነጀ መንገድ ሊመራ የሚችለዉ ተገቢ የሆነ ወቅታዊ ግምገማ፣ ክትትልና ድጋፍ ሲኖር ነዉ።

- የፍትህ ዘርፍ ተቋማት ሪፎርምን ለማካሄድ የሀገሪቱ አቅም በፈቀደ መጠን ተገቢዉ ሀብት ሊመደብ ይገባል። የሀብት ፍላጎትና ያለዉ የሐገሪቱ አቅም የማመጣጠን ቢሆንም የፍትህ ዘርፉ ሪፎርም መሳካት ለሐገሪቱ በአጠቃላይ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚዊና ማህበራዊ መረጋጋትና ዕድገት አስተዋጽኦዉ በቀላሉ የሚገመት አይሆንም። በመሆኑም ለዘርፉ ሪፎርም ትኩረት በመስጠት አስፈላጊዉ ሐብት አቅም በፈቀደ መጠን የሚመደብበት መንግድ ይፈጠራል።

----------///////----------